የስያሜ ችግር በስነ-ቃል፣ ናሙናዊ ጥናት

መስፍን መሰለ

1. መግቢያ

ለአንድ የሙያ ቃል ወይም ፅንሰ ሀሳብ ስያሜ መስጠት የመግባባትን ሂደት ቀላልና ቀልጣፋ ያደርገዋል። ምንም እንኳ በሰያሚው ቃልና በተሰያሚው መካከል ያለው ግንኙነት የባህርይ አይሁን እንጂ አንድ ስያሜ ለአንድ ነገር ወይም እሳቤ ድምፃዊ ምልክት በመሆኑ መስያው፣ መታወቂያው ነው ማለት ይቻላል (በይፋ መታፈሪያ፣1973)። አንድ ቃል ወይም ፅንሰ ሀሳብ ሲሰየም በመሰየሚያው ቋንቋ የሚገኘው ቃል ይዘት የቆየውን ትርጉም በማስፋት፣ በማጥበብ ወይም ሁለትና ከዚያም በላይ ቃሎችን በማጣመር...ወዘተ ሊከናወን ይችላል። በመሰየሚያው ቋንቋ ይህን ማድረግ ካልተቻለ በቅርብ ከሚገኝ ሌላ ቋንቋ በመዋስ መሰየም ይቻላል። እንዲህም ሆኖ በመሰየሚያው ቋንቋ አቻ ቃል ካልተገኘለት ወይም ለመሰየም የተፈለገው ቃል አለምአቀፋዊ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ እንዳለ መዋስ ይቻላል። ከሁሉም በላይ ግን ባለሙያን ማማከር አስፈላጊ ነው።

አንድ ስያሜ ወደ ህብረተሰቡ ዘልቆ ከገባ በሁዋላ በሌላ ለመተካት እጅግ ከባድ ይሆናል። በሀገራችን በአንድ ወቅት 'ዞን' (Zone) ወይም 'ሪጅን' (Region) ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል "ቀጠና" የሚል ስያሜ በመስጠት አገልግሎት ላይ እንዲውል መደረጉ ይታወቃል። ይኸው ቃል በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን በስፋት ለህዝብ ጆሮ እንዲደርስ ከተደረገ በኋላ ቃሉ ቀድሞ ይዞት የቆየውን "ረሀብ" የሚለውን ፍቺ የሚነግር ሆኖ በመገኘቱ "ቀጣና" በሚል ቃል እንዲተካ ተደረገ። ነገር ግን "ቀጠና" የሚለው ቃል በህዝቡ ዘንድ በመለመዱ ተክቶት የገባውን ቃል"ቀጣና"ን ለመልመድና ለመገልገል አልተቻለም። በጭነት መኪናዎች ጎን ላይ ቀድሞ የተፃፈው "ቀጠና" የሚለው ቃል በ"ቀጣና" ቢተካም ብዙውን ጊዜ ሰዎች የሚያነቡት የለመዱትን "ቀጠና"ን እንጂ ተፅፎ የሚታየውን "ቀጣና"ን አይደለም። ከዚህ ሌላ በአዲስ አበባ የአንድ አካባቢ መጠሪያ

ሆኖ ቀርቷል። ጦር ሃይሎች ሆስፒታልን አለፍ ብሎ ለመሄድ የታክሲ ወያላዎች "ቀጠና ሁለት" እያሉ ሲጠሩ ይሰማሉ። በዚህም ጠሪና ተጠሪ ወይም አገልጋይና ተገልጋይ ይግባቡበታል። እንደ ታክሲ ወያላዎች ሁሉ የአዲስ አበባ ሕዝብም "ቀጠና ሁለት" በማለት አካባቢውን ሲጠራ ይሰማል። በመሆኑም የግዕዙ ቃል የእንግሊዝኛውን ቃል እንዲሰይም ከመደረጉ በፊት ይዞት ከቆየው ፍቺ በተጨማሪ በቦታ ስምነት እያገለገለ ነው ። ሆኖም ሌላ ጊዜ ቃሉ ለሌላ አገልግሎት ሲውል መደናገር መፍጠሩ አይቀርም። ይህም መጀመሪያውኑ የእንግሊዝኛውን ቃል በአቻነት እንዲሰይም ሲደረግ ትክክለኛ ሰያሚ መሆን አለመሆኑ ወይም ለመሰየሚያው ቃል ጥንቃቄ ያለማድረግ ያስከተለው ችግር ነው።

በአሁኑ ጊዜ "ቀጠና"ም ሆነ "ቀጣና" የሚለው ስያሜ ትክክል ነው ወይም አይደለም ማለት ቀርቶ 'ዞን' (Zone) የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል በስፋት አገልግሎት ሲሰጥ ይስተዋላል። በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በጋዜጣና በመጽሔት ስለክልላዊ መንግስታት ሲነገር 'ዞን' የሚለው ቃል በስፋት ይደመጣል። "ቀጣና" የሚለው ስያሜ በእንግሊዝኛው 'ዞን' የሚለውን ቃል ሳለመጠቀም የተመረጠ ሆኖ እያለና "ቀጣና" ከሚለው ቃል ጋር የተፈጠረው ችግር ሳይፈታ እንደገና ወደ እንግሊዝኛው መመለስ ያስመግባባቱን ችግር ያባብሰዋል፤ ውሰቱም አሳስፈላጊ ይሆናል።

የውጭውን ቃል ስያሜ በመስጠት ሂደት ተመሳሳዩ ቃል በአማርኛ አለመኖር በተገቢው መንገድ ሳይመረመር ከሌላ ቋንቋ በመዋስ የመሰየም ስህተትም ይታያል። ለምሳሌ "ኮራፕሽን" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል "ሙስና" የሚል ፍቺ እንደተሰጠው ከመገናኛ ብዙሃን ይደመጣል። "ሙስና" የሚለው ቃል በግእዝና በአማርኛ የተለያዩ ፅንሰ ሀሳቦችን ይወክላል። "ሙስና" በግእዝ "ጥፋት" ማለት ሲሆን በአማርኛ ግን "ሬጋሬ የመልክ ውበት" ማለት ነው። የአማርኛውን ፍቺ መሠረት በማድረግም፦

የከንፈሯ ለዛ የጉንጯ ሙስና፣
ዓርብ ሮብ ያስከዳል እንኳን ሐሙስና።

እየተባለ ይዘፈናል (ደስታ ተክለወልድ፤ 1962፤ 822)። ስለዚህ የውጭን ቃል ለመሰየም ከግእዝ ቋንቋ የተደረገው ውሰት አላስፈላጊ ከመሆኑም በላይ ቃሉ በአማርኛ ያለውን አገልግሎት ያዛባል፤ ያደናግራል።

አንዳንድ ጊዜ ስያሜ የሚያስፈልገውና የሚከናወነው በአንድ ቋንቋ ውስጥ መደበኛ የቃላት አጠቃቀም እንዲኖር በማስፈለጉ ሊሆን ይችላል። ይህም በቋንቋው ተናጋሪ ሕብረተሰብ የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ በተለያየ ስያሜ የሚጠራን ነገር ወይም ፅንሰ-ሀሳብ በአንድ ወጥ ስያሜ ለመጠቀም ታስቦ የሚከናወን ነው። ይህ ፅሁፍ ትኩረት ያደረገበትን ጉዳይ ዓይነት ማለት ነው። እንዲህ አይነቱ ስራ የመሰየሚያውን ቃልና የሚሰየመውን ነገር ወይም ፅንሰ ሀሳብ በትክክል ማወቅንና ማገናዘብን ይጠይቃል። እንዲህ አይነቱ አካሄድም የቋንቋ ዘፈቀዳዊ ባህርይን የሚጋፋ ይመስላል።

ቃላት ከሚጠሩት ጥሬ ነገር ወይም ሀሳብ ጋር የሚያሳዩት ዝምድና-አልባ ልጥፍነት፣ ወይም እንደተባለው ጠላ-እንኮላ አይነት ዝምድና አጠቃላይነቱ አብዛኛውን ጊዜ ለለት ተለት ንግግር እንጂ ለሙያ ነክ ቃላት መድረሱ በመጠኑ ነው። ከሙያ ነክ ቃላት ብዙዎቹ ከአእምሮ ብስለትና ከጥበብ ማወቅ በኋላ የሚመጡ ስለሆኑ ሞያ ነክ ቃሉና ቃሉ የሚገልፀው ጥሬ ነገር፣ ወይም ሃሳብ ቢያንስ ቢያንስ የነሳጭ ተገላጭነት ዝምድና ያሳያሉ (ሰይፉ፡ 1973፡ 12)።

ስለዚህ በሕብረተሰቡ የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ለረጅም ጊዜ የነበረንና ያለን ጉዳይ በአንድ ስያሜ ለመጥራት ወይም ከውጭ የተዋስነውን ፅንሰ ሀሳብ በራስ ቋንቋ ተገቢውን ስያሜ በመስጠት እንዲለመድና እንዲሰራበት ለማድረግ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። ይህ ሲደረግም የመግባባትን ሂደት ቀልጣፋና የተስተካከለ፣ ቋንቋንም ካላስፈላጊ ውሰት ነፃ ያደርገዋል።

በየሙያ መስኩ የስያሜ ችግር ሊያጋጥም ይችላል። ይህ ችግርም የእኛ ብቻ አይደለም። "ስነ-ቃል" የሚባለውን የሙያ መስክ "አቅፎ" የያዘው "ፎክሎር" የሚለው ቃል በእንግሊዝኛ ቋንቋ ከመለመዱ በፊት 'ፖፑላር አንቲኩቲስ' (popular antiquities) በሚል ለረጅም ጊዜያት ሲጠራ ቆይቷል። የቃሉን "ቀርፋፋነት" የተገነዘበውና በመስኩ ጥናት የተሰማራው ዊልያም ጆንቶምስ እ.ኤ.አ. በ1846 ዓ.ም. አዲሱን ቃል በጋዜጣ ላይ አስተዋውቆ ተቀባይነት ያገኘለት ቢመስልም ስያሜው በተመራማሪዎች ዘንድ ክርክር ማስነሳቱ አልቀረም። በአሁኑ ጊዜ የሙያ መስኩ በይዘታው ሰፍቷል በማለት "ፎክሎር" ከሚለው "ፎክላይፍ" የሚለውን ስያሜ የሚመርጡ የሙያው ሰዎች አሉ (ሰይፉ፡ 1973)። የተሰጠው ስያሜ ዛሬም በለውጥ ሂደት ላይ መሆኑን እንገነዘባለን። ከዚህ ሌላ "ፎክሎር" የሚለው ቃል ሃያ አንድ የተለያዩ ፍቺዎች በተለያዩ ሰዎች ተሰጥተውት ይገኛል (Maria፤ 1949፤ 398-403)። ይህም በሙያ መስኩ ላይ ያለውን የጠራ የዕሳቤና የግንዛቤ ችግር ይጠቁማል።

በጀርመንኛ የሙያ መስኩን በትክክል ይሰይማል የተባለው ቃል መጀመሪያ ተነገረ የተባለበትንና ተቀባይነት አግኝቶ ስራ ላይ የዋለበትን ጊዜ ስናይ ቢያንስ ሰላሳ ስድስት ዓመታትን እንዳስቆጠረ እንረዳለን። በፈረንሳይኛም የመስኩን መጥሪያ ቃል በመሰየም በህዝብ ዘንድ እንዲለመድ ለማድረግ ብዙ ዓመታትን ወስዷል (ሰይፉ፤ 1973)። "ፎክሎር" በሚለው የሙያ መስክ የሚታየው የስያሜ ውዝግብ በስነ-ቃል ላይም አለ። በዚሁ የሙያ መስክ ላይ "በእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥናትና ምርምር ያደረጉ ሰዎች "folklore," "orature," " orality, " "oral literature" የመሳሰሉትን ስያሜዎች በአማራጭነት ተጠቅመዋል" (አሰፋ፡ 1976፡2)። እንዲሁም የሙያ መስኩ "popular literature," " Unwritten literature," "Traditional literature,""verbal art" እየተባለ እንደሚጠራ ፈቃደ (1996፤67) ገልጸዋል።

በአማርኛ ቋንቋም በስፋት ስነ-ቃል በሚል ለሚታወቀው የጥበብ ዘርፍ የተለያዩ ስዎች የተለያዩ ስያሜዎች የሰጡ መሆኑን አሰፋ ከላይ በተመለከተው ጽሑፋቸው፣ "በአማርኛ ቋንቋም ለስነ-ቃል ብዙ አማራጭ ስያሜዎች በልዩ ልዩ ምሁራን ተሰንዝረዋል። ከነዚህም ውስጥ 'አፋዊ ስነ-ፅሁፍ፣ አፋዊ ቅርስ፣ አፋዊ ድርሰት፣ ኪነ-ቃል፣ ኪነተ-ቃል፣ አፋዊ ኪነተ-ቃል፣ ቃላዊ ስነ ፅሁፍ፣ ስነ-አንደበት፣ ትውፊት፣ ስነ-ቃል፣...' የመሳሰሉትን ለመጥቀስ ይቻላል።" በማለት ገልፀዋል (አሰፋ፣1976፣2)። ፊቃደ (1996) በበኩላቸው አስራ ሶስት የተለያዩ ስያሜዎች ያሉ መሆኑን ገልጸዋል። ሆኖም አንዳንዶቹ ስያሜዎች በአሰፋ ከተጠቀሱት ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ይህም በአንድ ወጥ ስያሜ ለመጠቀም አለመቻል በስነ-ቃል ጥናትና ምርምር የተሰማሩ የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ ባለሙያዎች ሁሉ ችግር ሆኖ መቆየቱን ያስረዳል።

ይኸው የስያሜ ችግር በብዙዎች የስነ-ቃል አይነቶች ላይም ይታያል። በዚህ ፅሁፍ "ምሳሌያዊ ንግግር" በሚል የተጠራው (ምክንያቱን በመጨረሻ ገፆች ላይ ይመለከቷል) የስነ-ቃል አይነትም የስያሜ ችግር ከሚታይባቸው መካከል አንዱ ነው። "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" የሚልን የስነ-ቃል ዓይነት ለተለያዩ ሰዎች አቅርበን ስያሜው ምን እንደሚባል ብንጠይቅ የምናገኘው መልስ የተለያየ እንደሚሆን እስከዛሬ በተለያዩ ፅሁፎችና የመገናኛ ብዙሃን የተሰጡት ስያሜዎች ይጠቁማሉ። ከዚህም በላይ አንድ ሰው በአንድ ጽሁፍ ውስጥ ወይም በተለያዩ ስራዎች ላይ ስለ ስነ-ቃሉ ዓይነት የተለያዩ ስያሜዎች እየለዋወጠ ሲገለገል ይታያል (አባሪውን ይመለከቷል)። ይህን የስነ-ቃል ዓይነት መሰብሰብና ራሱን ችሎ በመጽሀፍ መልክ ማሳተም የተጀመረው ከ1940ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት አንስቶ ነው። ለዚህ የሐጂ ዩሱፍ አብዱረህማን (1942) ምሳሌና ተረት (1942) ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀልና ሞገስ ዕቁባጊዮርጊስ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ሰብስበው በማሳተም በኩል ከሐጂ ዩሱፍ ጋር በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሱ ናቸው። በተለያዩ ሰዎች በተለያዩ ጊዜያት ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ተብለው በተዘጋጁ መፃሕፍት ውስጥ የስነ-ቃሉ ዓይነት ቢሰበሰብና ቢጠቀስም የተሰጠው ስያሜ የተለያየ ሆኖ እናገኘዋለን።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ክፍል ለዲግሪ ማሟያ ተብለው ከቀረቡት ፅሁፎች መካከል አንዳንዶቹ በተለያዩ ቋንቋዎች በሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ላይ ያተኩሩ ናቸው። የእነዚህ ጥናቶች አብዛኛው ርዕስ "ተረትና ምሳሌ" የሚል ነው። ሆኖም በውስጣቸው ባለው ፅሁፍ በተለያዩ ገፆች የተለያዩ አማራጭ ስያሜዎችን ተጠቅመዋል (በአባሪው ላይ ለአብነት የተጠቀሱትን ይመለከቷል)። ይህም ጥናት አቅራቢዎቹ ለሙያው ቃል አንድ ስያሜ ብቻ አለመጠቀማቸውን ያመለክታል።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ በስነ-ቃል ላይ ጥናትና ምርምር ማድረግ የጀመረው ከ1971 (አሰፋ ፣1976፣ 12) ዓ.ም. ወዲህ ቢሆንም የሙያ ቃሉን በአንድ

ስያሜ ሲጠራው እንዳልቆየ ዜና ልሳን ተብሎ በሚታወቀው የአካደሚው መጽሔት የቀረቡ በተለያዩ ጊዜያት በስነ-ቃሉ ዓይነት ላይ ያተኮሩ ጽሁፎች ያመለክታሉ። አካደሚው "*የቃል ትውፊት፣ ምሳሌ ፣ ኪነ ቃል፣ ተረትና ምሳሌ፣ ምሳሌያዊ አነጋገርና ምሳሌያዊ ንግግር* " የሚሉትን ስያሜዎች በመለዋወጥ ሲገለገል ቆይቶ ነበር። አሁን ግን "ምሳሌያዊ ንግግር" በሚለው ስያሜ የጠና ይመስላል።

በተለያዩ ጊዜያት በስነ-ቃል መስክ ጥናት ያደረጉ ሰዎች ለስነ-ቃሉ አይነት የሰጡት ስያሜ አንድ ወጥ አይደለም። የወቅቱ አዋቂዎችም እንደቀደምቶቹ ሁሉ በአንድ ፅሁፍ ውስጥ የተለያዩ ስያሜዎችን ሲጠቀሙ ይታያሉ። የሙያ ቃሉ በጋዜጦችና መጽሔቶች፣ በሬዲዮና ቴሌቪዥን በተለያየ ስያሜ ይጠራል። በአንድ የመገናኛ ብዙሃን ክፍል ወይም በአንድ ጋዜጠኛ አማካይነት የሚሰጠው ስያሜ የተለያየ ነው። ይህም የስነ-ቃል ጥናትና ምርምር በሙያ መስክነት ለሀገራችን አዲስ መሆንና ተገቢውን ትኩረት አለማግኘትን ለመረዳት አንድ ፍንጭ ይሆናል። በሌላ አባባል በመስኩ የሙያ ቃል የሚታየውን የስያሜ ችግር ለማስወገድ ሆን ተብሎና ታስቦበት አንድ ስያሜ በመስጠት በህብረተሰባችን ዘንድ እንዲለመድ አለመደረጉን ያስገነዝበናል። ይህ ሲባል ግን እስከዛሬ በዘፈቀደ የተሰጡ ስነ-ቃል ነክ ስያሜዎች ሁሉ ስህተት ናቸው ማለት አይደለም። ለአንዳንድ የስነ-ቃል ዓይነቶች በዘፈቀደ የተሰጣቸው መጠሪያ የስያሜ ችግር አላስከተለም። ለምሳሌ "እንቆቅልሽ" የምንለውን የስነ-ቃል ዓይነት ሁሉም ሰው በዚሁ ስያሜ ያውቀዋል፣ ይጠራዋል። የስነ-ቃሉን ዓይነት በወረቀት ላይ ፅፈን ወይም ጥያቄና መልሱን በቃል ነግረን የስነ-ቃሉ ዓይነት የሚጠራበትን ስም እንዲናገሩ የተለያዩ ሰዎችን ብንጠይቅ ሁሉም የሚሰጡት መልስ አንድ አይነት ይሆናል የሚለው ግምታዊ መደምደሚያ እውነት ይሆናል። ከዚህ ሌላ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጦች እንዲሁም በተለያዩ መጣጥፎችና መፃህፍት ላይ የተለያዩ ሰዎች ይህንኑ የስነ-ቃል ዓይነት የጠሩበት ስም አንድ ዓይነት መሆኑ የስያሜ ችግር አለመኖሩን ያረጋግጣል።'

ይህ ፅሁፍ ትኩረት ያደረገበት የስነ-ቃል ዓይነት በባህላዊ ጥሪትነት ይዞት የቆየው አንድ ስያሜ እንዳለ ሰይፉ (1993፣ 137) "የፎክሎር ዓይነቶችን የሚሰይሙ ካልኩዋቸው ውስጥ፣ በነባር ባህላዊ ጥሪትነት አማርኛ ሲጠቀምባቸው የኖሩ አሉ። ከእነዚህም ለምሳሌ እንቆቅልሽ፣ ዘፈን፣ ሽለላ፣ ተረት፣ ተረትና ምሳሌ የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል" በማለት ይገልጻሉ (ሰረዝ የራሴ)። በሰይፉ መታፈሪያ (1993፣ 101) መጣጥፍ ላይ "ተረትና ምሳሌ" የሚለው ስያሜ "ፕሮቨርብ" ለሚለው የእንግሊዘኛ ቃል የተሰጠ መሆኑ በግልጽ ተመልክቷል። ይህም በስነ-ቃሉ ዓይነት ላይ የስያሜ ችግር የሌለ መሆኑን ይገልጻል። ነገር ግን በስነ-ቃሉ አይነት ላይ የስያሜ ችግር አለ። ይህንንም ቀጥለን እንመለከታለን።

የአማርኛ ቋንቋ "ተረትና ምሳሌ"ን በባህላዊ ጥሬትነት ሲጠቀምበት ቢቆይም፣ ለስነ-ቃሉ ዓይነት መሰየሚያ በመሆን የሚታወቀው ይህ ብቻ አይደለም። ወደፊት እንደምናየው ለዚሁ የስነ-ቃል ዓይነት የተለያዩ ስያሜዎች ተሰጥተውት እናገኛለን። "ተረትና ምሳሌ" የሚለው ስያሜ በስነ-ቃል በተለይም በስነ-ቃሉ ዓይነት ጥናትና ምርምር ለማድረግ በሞከሩ ባለሙያዎች በሁሉም ዘንድ የተለመደ አይደለም። ይህም እስከዛሬ የተሰጡትን ስያሜዎች በመመርመር ውይይት ማድረግንና አንድ ወጥ ስያሜ ላይ ለመድረስ የሚያስገድድ ሁኔታን ፈጥሯል። አንዳንድ ሰዎች ለስያሜያቸው መነሻ አድርገው ያቀረቡዋቸውን ምክንያቶች ትክክለኛ መሆን አለመሆናቸውን መመርመርና ማጤን አስፈላጊ ይሆናል። ስለዚህ እስከዛሬ ለስነ-ቃሉ ዓይነት ከተሰጡት የተለያዩ ስያሜዎች መካከል በመረጃ ምንጭነት በተዘረዘሩት ስራዎች ውስጥ የተገኙትን በመዘርዘር ትክክለኛ ነው ተብሎ የታመነበትን ስያሜ ለመጠቆም ይሞከራል።

2. ለአንድ የስነ-ቃል ዓይነት ከየአቅጣጫው የተሰጡ ስያሜዎች

ይህ ፅሁፍ ትኩረት ያደረገበት የስነ-ቃል ዓይነት በአማርኛ ረጅም ዕድሜ የኖረ ነው። ይሁን እንጂ ከየአቅጣጫው የተሰጠው ስያሜ የተለያየ ሆኖ ይገኛል። ለዚሁ የስነ-ቃል ዓይነት ስያሜ በመስጠት የተገለገሉበትን ሰዎች ስራዎች ስንመለከት በአንድ ፅሁፍ እንኳ ከአንድ በላይ ስያሜ ተሰጥቶት እናገኛለን። ይህን ለማረጋገጥ በተለያዩ ጊዜያት ይህንኑ የስነ-ቃል አይነት በስብስብነት የያዙ መጻህፍት በመቅድሞቻቸው ወይም በመግቢያዎቻቸው ላይ ያስፈሩአቸውን ጽሁፎች፣ የመዝገበ ቃላትና የሰዋሰው መጻህፍት፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም መጽሄት፣ ከባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር <u>ዜና ባህል</u> ና <u>ዜና ልሳን</u>፣ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍል በአራተኛ አመት ተማሪዎች ለዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሁፎች፣ በተለያዩ ሴሚናሮች የቀረቡ ስነ-ቃል ነክ ጥናታዊ ወረቀቶች፣ <u>አዲስ ዘመን</u>፣ "አድማስ አምድ"ና <u>የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ</u>፣ "ቅምሻ አምድ" (ከ1985-1988 ዓ.ም.) ትኩረት ከተደረገባቸው የመረጃ መገኛዎች መካከል በምሳሌነት ይጠቀሳሉ። እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሬዲዮ አገልግሎትንና በተለይ ደግሞ የ1988 ዓ.ም. የትምህርት ቤቶችን የውድድር ፕሮግራም ለመከታተል ተሞክሯል። በነዚህ ምንጮች ውስጥ "ፕሮቨርብ" ለሚለው የስነ-ቃል አይነት የሚከተሉት ስያሜዎች ተሰጥተዋል።

---

* ጸለታ ጸፈሮ (1956)፣ <u>ዜና ባህል</u> (1972) ቅጽ 2፣ ቁጥር 9፣ አክፓክ (1987) <u>ኩኩሉ</u>

ምሳሌ	ተረት/ምሳሌ/	ፈሊጣዊ አነጋገር
ተረት	ምሳሌ /ተረት/	ምሳሌያዊ ተረት
ዘይቤ	ምሳሌና ተረት	አፈ-ታሪክ
ንግግር	የምሳሌ ንግግር	ልማዳዊ አባባል
አባባል	ምሳሌያዊ ንግግር	ጥንታዊ የአነጋገር ብሂሎች
	የቃል ትውፊት	አሌጎሪ ተረትና ምሳሌዎች
	ኪነ-ቃል	ብሂል /ከሬዲዮ የተደመጠ/
	ምሳሌያዊ አባባል	
	ተረታዊ አነጋገር	
	ታሪክና ምሳሌ	
	ጥንታዊ ምሳሌ	
	ተረትና ምሳሌ	

ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ስያሜዎች መካከል በዐቢይነት ምሳሌ እና ምሳሌያዊ ንግግር የሚሉትን በማስቀደም የአንዳንዶቹው ስያሜዎች ምንነት ቀጥለን እንመለከታለን።

3. የምሳሌ ፍቺና ልዩ ልዩ አገልግሎቶች

"ምሳሌ" ለሚለው ቃል በአማርኛ የመዝገበ ቃላት መጻሕፍት ውስጥ የተለያዩ ፍቺዎች ተሰጥቶት እናገኛለን። ደስታ ተክለወልድ (1962፣820) "ምሳሌ (1) በቁሙ፣ የነገር አንጻር ተረት። ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ እንዲሉ (2) ምስል ... (3) የመጽሐፍ ስም፣ ሰሎሞን በምሳሌ እየተናገረ የጻፈው መጽሐፍ፣...(4) ሰምና ወርቅ" የሚሉ ፍቺዎችን ሰጥተዋል።

ከላይ በተጠቀሰው መዝገበ ቃላት ውስጥ የቃሉ ፍቺ አንድ ብቻ አለመሆኑን እንገነዘባለን። ከተሰጡት ፍቺዎች መካከል በተራ ቁጥር አንድ የተመለከተው በዚህ ፅሁፍ ለምንነጋገርበት የስነ-ቃል ዓይነት አንዳንድ ሰዎች ከሰጡት ስያሜ ጋር ይቀራረባል። ሆኖም ለቃሉ መፍቻ ተብለው ከተዘረዘሩት ቃላት መካከል "ተረት" የሚለው ቃል ተጨምሮ መገኘቱ በመዝገበ ቃላቱ ውስጥ "ምሳሌ" ለሚለው ቃል የተሰጠውን ፍቺ አሻሚ ያደርገዋል። "ተረት" የሚለው ቃል ለስነ-ቃሉ አይነት መለ የሚያ ተደርጐ መወሰዱን በተጠቀሰው የመዝገበ ቃላት መጽሀፍ ውስጥ በተለያዩ ገጾች ላይ እናገኛለን። አዘጋጁ ለአንድ ቃል ፍቺ ከሰጡ በኋላ የቃሉን አጠቃቀም በዐረፍተ ነገር ውስጥ ለማሳየት አንዳንድ ጊዜ የስነ-ቃሉን አይነት በአስረጅነት ያቀርባሉ። የሚጠራበት ስያሜ ተረት መሆኑን ለማመልከት በቅንፍ ውስጥ ጽፈውት እናገኛለን። ለምሳሌ በገጽ 153፣ "አበጀ" ለሚለው ቃል "ሠራ፣ አዘጋጀ፣ አስመረ፣ አሳመረ፣ አሰዋበ" የሚሉ መፍቻዎች ከሰጡ በኋላ "(ተረት)፤ አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው።" በማለት ስነ-ቃሉ የሚጠራበትን ስምና አይነቱን ጠቅሰዋል። እንዲህ ያለው አሰራርና አጠቃቀም በመዝገበ ቃላቱ የተለያዩ ገጾች ላይ ተደጋግሞ ሰፍሯል። "ተረት"፤"ምሳሌ" ለሚለው ቃል ፍቺ ሆኖ መቅረቡ በመዝገበ ቃላቱ ለተጠቀሰው ቃል የተሰጠው ስያሜ ችግር ያለበት መሆኑን ይጠቁማል።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ያዘጋጀው <u>የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት</u> (1972፥44) "ምሳሌ" ለሚለው ቃል አንድን ነገር ግልጥ ለማድረግ ሲፈለግ የሚቀርብ ማስረጃ፣ማብራሪያና መግለጫ " በማለት ፍቺ ይሰጣል። ይኸው መዝገበ ቃላት በተጠቀሰው ገጽ ላይ የምሳሌ ዓይነቶችንና አተረጓጎም እንደሚከተለው በሦስት ይመድባቸዋል።

(ሀ) እንደ ተረት ያለ አጭር ምሳሌ፣ ለምሳሌ ያህል ኢየሱስ "መልካም እረኛ እኔ ነኝ" ሲል እረኛ በጎቹን እንደሚጠብቅ ተከታዮቹን ይጠብቃል ማለት ነው።

(ለ) ብዙ ድርጊት የሚገኝበት ለድርጊቱም ትርጉም የሚሰጥ ምሳሌ፣ ለምሳሌ ያህል የዘሪው ምሳሌ ይህን ያሳያል፣ እያንዳንዱ ነገር ትርጉም አለው (ማቴ 13፣ 3-9፣ 18-23)።

(ሐ) ብዙ ድርጊትና ነገር የሚገኝበት ለየድርጊቱና ለየነገሩ ትርጉም የማይሰጣቸው ምሳሌ፣ ይህን ለመተርጉም ምሳሌው የተነገረበትን ምክንያት ማስተዋል ያስፈልጋል። የርኅሩኅን ሳምራዊ ምሳሌ ይመ. (ሉቃ.10፣ 25-30)።...

በ 'ሀ' ምድብ የተጠቀሰው ምሳሌ አጭር አረፍተ ነገር ነው። ትርጉሙም በገሀዱ ዓለም በምናውቀው የእረኛ ተግባር ተመስሎ የቀረበ ነው። ይኸውም መልካም እረኛ የሚጠብቃቸውን የበግ፣ የፍየል፣ የከብት ወዘተ. መንጋዎች እንዳይርባቸው ግጦሽ ወደአለበት ያሰማራል፤ እንዳይጠማቸው ውሃ እንዲጠጡ ያደርጋል። ከተኩላ፣ ከነብር፣ ከአንበሳና ከሌላም ነጣቂ አውሬ ይጠብቃቸዋል። በዚህ መልካም ተግባሩም ለሰነፍ እረኛ ምሳሌ ወይም አርአያ ይሆናል። በገሀዱ ዓለም ከምናውቀው ወይም ከምናስበው መልካም እረኛ በላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምዕመናኑን ሁሉ ከክፉ ነገር እንደሚጠብቅ ምሳሌው ያስረዳል። "አልአዛርን ከመቃብር ያስነሳህ፣ ዳንኤልን ከአንበሳ አፍ ያዳንክ" እንዲሉ።

ሌሎች የምሳሌ ዓይነቶች ተብለው የቀረቡት በ'ሀ' እንደተመለከተው በአንድ ዐረፍተ ነገር የሚገለፁ አይደሉም። የሚያነሱት ጉዳይ በአንድ ሀሳብ ዙሪያ የሚሽከረከር ቢሆንም በብዙ ዐረፍተ ነገሮች የሚገለፁ ናቸው። በ'ለ' ስር የተጠቀሰው ምሳሌ (ማቴ. 13፣ 3-9) ላይ በቀረበው ምሳሌ የተገለፀው ድርጊት በአንድ ዘር ዘሪ ላይ የሚያተኩር ነው። ይህም ብዙ ፍሬዎችን እንዲያፈሩለት ወደ መሬት የበተናቸው ዘሮች የወደቁበት መሬትና የተከተለውን ነገር የሚያሳይ ነው። እያንዳንዱ የዘር ፍሬ ምሳሌ ነው። ምን አይነት ምሳሌ ለሚለው (ማቴ 13፥ 18-23) ላይ ዘርዘር ብሎ ቀርቧል። ከዚህ በላይ በ'ለ' ምድብ በተጠቀሰው የምሳሌ አይነት እያንዳንዱ ድርጊት ትርጉም በመስጠቱ በምሳሌውና በትርጓሜው መካከል መመጣጠን ይታያል። ይኸው የምሳሌ ዓይነት ትንሽ ለየት ባለመልኩ ከትርጓሜው ጋር በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 8፣ በቁጥር 4-15 ሰፍሮ ይገኛል።

ቀደም ሲል በተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ ከተዘረዘሩት የምሳሌ ዓይነቶች አንደኛው በ'ሐ' የተገለፀው ነው። የምሳሌው ዓይነት ይሆናል ተብሎ በአስረጅነት የተጠቀሰውም (ሉቃ.10፥ 25-37) አንድ ሕግ አዋቂ የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ የሚያስችለውን መንገድ ያውቅ ዘንድ ለኢየሱስ ክርስቶስ ላቀረበው ጥያቄ ከተሰጡት መልሶች አንዱ ባልንጀራውን እንደራሱ እንዲወድ የሚመክር ነው። ይህንንም ለማስረዳት በወንበዴዎች ተጠቅቶ በመንገድ ዳር ለወደቀ መንገደኛ ርኅሩኅ ሳምራዊ ያደረገለት እርዳታ ምሳሌ ሆኖ ቀርቧል። በዚህ ታሪክም የሕግ አዋቂው ወደፊት የሳምራዊን በጐ ምግባር የመሰለ ነገር ለጓደኛው እንዲያደርግ አስተምሮበታል። ለሕግ አዋቂው የተነገረው ታሪክ ምን ምሳሌን እንደሚያስረዳ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር (1972፥45) ያዘጋጀው የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት እንደሚከተለው አስፍሮታል።

> ...በስም የተጠቀሱ ነገሮች ወይን፣ ዘይት፣ አህያ ዲናር... ወዘተ. የምንና የምን ምሳሌዎች ናቸው ብለን ብንጠይቅ፣ የፈለግነውን ምስጢር ልናገኝባቸው እንችላለን። ክርስቶስ ምሳሌውን የተናገረው የህግ አዋቂውን ጥያቄ ለመመለስ ነው። እንግዲህ ይህ ታሪክ የሰው ባልንጀራ ማን እንደሆነ ያሳያል።ወይን፣ ዘይት፣...ወዘተ የሰውየውን ቸርነት ያሳያሉ እንጂ ለእያንዳንዱ ልዩ ትርጉም አይኖራቸውም።

በዚህም በታሪኩ ለቀረበው እያንዳንዱ ድርጊት ትርጉም አለመስጠቱን እንገነዘባለን። ከዚያ ይልቅ የሳምራዊ ቸርነት ጉልቶ እንዲታይ መደረጉንና ለሕግ አዋቂው የህይወት መመሪያ ምሳሌ ሆኖ መቅረቡን እንረዳለን።

የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት "ምሳሌ" ለሚለው ቃል የሰጠውን ስያሜ ከቅርፅ አንፃር ስንመለከተው በሁለት ይመደባል-በአጭር ፀረፍተ ነገር የሚገለፅና አንድን ታሪክ መሰረት በማድረግ በብዙ ዐረፍተ ነገሮች የሚቀርብ በማለት። በአጭር ዐረፍተ ነገር የቀረበውን የምሳሌ ዓይነት ስንመለከት "እንደ ተረት ያለ አጭር ምሳሌ" በሚል ተገልፆ እናገኘዋለን። "እንደ ተረት" የሚለው አገላለፅ ከተረት ጋር ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ተመሳሳይነት ያላቸው መሆኑን ይጠቁማል። ይህም በአማርኛው መዝገበ ቃላት ላይ "ምሳሌ" ለሚለው ቃል "ተረት" ተብሎ ከተሰጠው ፍቺ ጋር ይመሳሰላል። "ምሳሌዎችና ተረቶች" በይዘታቸው ወይም በገፀባህርያት አጠቃቀማቸው ሊመሳሰሉ ይችላሉ። ነገር ግን "ተረት" ብዙ ጊዜ በብዙ ዐረፍተ ነገሮች የሚቀርብ በመሆኑ በቅርፁ በ "ሀ" ምድብ ከተጠቀሰው የምሳሌ ዓይነት ይለያል። በዚህ ምድብ የተመለከተው ምሳሌ በቅርፅ ደረጃ የምንነጋገርበትን የስነ-ቃል አይነት ይመስላል። በ "ለ" ና በ "ሐ" ምድቦች የቀረቡት የምሳሌ ዓይነቶች ሊፈፀም በሚችል ታሪክ ላይ ተመስርተው ሀሳብን ግልፅ አድርጐ ለማስረዳት የቀረቡ ናቸው። በዚህ መዝገበ ቃላት የተመለከቱት የምሳሌ ዓይነቶች በቅርፅ ይለያዩ እንጂ በአገልግሎታቸው አንድ ናቸው።

በሌላ በኩል ስርቶ በማሳየት ተመሳሳይ ሁኔታ ለመስራትም ሆነ ለማሰራት መጣር ወይም እንዲሰራ ማዘዝ በመማር ማስተማር ሂደት የተለመደ ነው። ትምህርት ሚኒስቴር ለአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማርያ ይሆናል ብሎ ባዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ (1987፡ 78-79) የሰፈረው ምሳሌ ይህንኑ ሀሳብ ያረጋግጣል።

የሚከተሉትን ቅኔያዊ ጥያቄዎች በቀረበልህ ምሳሌ መሰረት በትክክል መልስ።

ምሳሌ 1. ስንቁን ሰንቄልኝ ርቄ እሄዳለሁ፤
እስከመቼ ድረስ ሳግ እኖራለሁ

ሰም:- የምኖቁን ባለሞያቴ እስከ መቼ ድረስ በሐሜትና በኃዘን ተቀምጬ እኖራለሁ።

ወርቅ:- ስንት ዘመን በሳማን ገዳም ተኹሜ እቀመጣለሁ፤ ወደሌላ ወደ ከፍተኛ ደብር አልዛወርምን? (ሰረዝ የራሴ)

ይህ ዓይነቱን ምሳሌ በመስጠት ተማሪዎች የቋንቋ ፣ የሂሳብና የሌሎችንም ትምህርቶች መልመጃዎች እንዲሰሩ ማድረግ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተዘውትሮ ይታያል።

ሰርቶ በማሳየት ምሳሌ መስጠትና ተመሳሳይ የሆነ ነገር እንዲሰራ የመጠየቅ ጉዳይ በተግባር ስራ ውስጥም ይስተዋላል። የግብርና ባለሙያዎች የማዳበሪያ አጠቃቀምን፣ የምርጥ ዘር አስፈላጊነትን ወይም የተሻሻለ አዘራርን በተወሰነ ክልል ላይ ለሚኖሩ ገበሬዎች ለማስተማር ለዚሁ ተግባር ተብሎ በተከለለ መሬት ላይ የራሳቸውን ሙከራ አድርገው ያሳያሉ። ይህም በአካባቢው ለሚኖሩ ገበሬዎች ምሳሌ እንዲሆንና እነሱም በራሳቸው ማሳ ላይ እንዲጠቀሙበት ታስቦ የሚሰራ ነው። በሌላውም የተግባር ስራ በሚጠይቅ መስክ ሰርቶ በማሳየት ምሳሌ መስጠትና ሌላው እንዲማርበትና የራሱን ተመሳሳይ ስራ እንዲሰራ ማድረግ የተለመደ ነው።

ከላይ የተነገረን ወይም የተገለፀን ሀሳብ በተጨባጭ የሚያስረዳ ነገር ማምጣት ሲያስፈልግ "ምሳሌ" የሚለውን ቃል እንጠቀማለን። የክልል 14 የትምህርት ቢሮ (1987፡94) ለአምስተኛ ክፍል የሳይንስ መማሪያ ብሎ ባዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ የሚከተለውን እናገኛለን። "ምንጮችና ጅረቶች በተለያዩ ነገሮች ይበከላሉ። ለምሳሌ ከአጠገባቸው የሚገኙ ዛፎች ቅጠሎች ብስባሽ፣ አቧራ፣ ጎርፍ አፈርና ትናንሽ እንስሳት ሊበክሏቸው ይችላሉ። ከብቶች አእዋፍና የዱር አራዊትም ይበክሏቸዋል" (ሰረዝ የራሴ)። "በተለያዩ ነገሮች ይበከላሉ" የሚለውን የፊቱልን በምሳሌው ስር የተዘረዘሩት ነገሮች ናቸው።

በህብረተሰባችን ውስጥ የዱር አራዊትንና የቤት እንስሳትን የተለያየ ባህርይ ምሳሌ አድርጐ ማቅረብ የተለመደ ነው። ነብር የቁጡ፣ አንበሳ የኃይለኛ፣ ጦጣ የብልጥ፣ ጅብ የፈሪ፣ በግ የየዋህ፣ ጥየል የለፍላፊ፣ አህያ የደደብ ሰው ምሳሌ ሆነው ይቀርባሉ። እያንዳንዱ እንስሳ የሚወክለው የባህርይ ምሳሌ አንድ ብቻ ነው ማለት ግን አይደለም። ለምሳሌ ጅብ የፈሪ፣ እንዲሁም የሆዳም ምሳሌ ሆኖ የሚቀርብበት ጊዜ አለ። በክርስትና እምነት በግ የፃድቅ ፍየል የሃጥእ ምሳሌ ሆነውም ይነገራሉ።

አእዋፍም የተለያዩ ነገሮች ምሳሌ ሆነው ይቀርባሉ። ርግብ የሰላምና የደስታ ምሳሌ ሆና ትቀርባለች። ቁራ የተላከውን ነገር ለማይፈፅም ሰው ምሳሌ ነው። አንድ ሰው ወደ አንድ ቦታ ተልኮ መልእክቱን ሳያደርስ ቢቀር ወይም ቢዘገይ "እገሌ የቁራ መላእክተኛ ነው" ይባላል። የሁለቱ አእዋፍ ምሳሌ ከኖኅ ታሪክ ጋር የተቆራኘ ነው።

<u>ታሪክና</u> ምሳሌ (፩ኛ፣ ፪ኛና ፫ኛ) በሚል ርዕስ በወጡት መጻሕፍት ውስጥ "ምሳሌ" የሚለው ቃል ለተለያዩ አገልግሎቶች ውሏል። ቀድሞ በመፃሕፍቱ የፊት ሽፋን ላይ እንደሚታየው ታሪክ ከሚል ቃል ጋር በመጣመር የመፃሀፍቱ ርዕስ ሆኖ አገልግሏል። ታሪክ የሚለው ቃል የሚገልፀው በመፃሕፍቱ ውስጥ የተካተቱትን ስለ አእዋፍ፣ የዱር እንስሳት፣ የዱር አራዊት፣ ነፍሳት፣ የታዋቂ ሰዎች ስራዎችና ምክሮች፣ ተረቶች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች በአጠቃላይ ተፈጥሮን ወይም ማህበራዊ ሳይንስን የሚገልፁ ፅሁፎችን ነው። "ምሳሌ" የሚለው ቃል ደግሞ በስድ ፅሁፍ ወይም በግጥም የቀረበው ሃሳብ የሚያስተላልፈውን መልእክት፣ በእያንዳንዱ ታሪክ የቀረበው ነገር የሚሰጠውን የህይወት ተሞክሮ ያመለክታል። ከሁለቱ ቃላት ጥምረት የምንረዳው የተለያዩ ጉዳዮችን መሰረት አድርገው በተነገሩት ታሪኮች ወይም ግጥሞች ህፃናት ልዩ ልዩ ቁምነገሮችን እንዲማሩ ለማድረግ የተዘጋጁ መሆኑንና ይህም በመፃሕፍቱ ርዕስ ላይ በተነበበው መመልከቱን ነው። የተላለፈውን ቁምነገር ህፃናቱ በትክክል መረዳት አለመረዳታቸውን እንዲሁም አስተማሪዎች የተገነዘቡት መሆኑን ለማወቅም "ይኸ ምሳሌ የሚያስተምረን ምንድን ነው?" (<u>ትምህርትና ስነ-ጥበብ ሚኒስቴር</u>፣ 1966፣ 53) በሚል ተጠይቆ እናገኛለን። ይህም በቀረበው ታሪክ የተላለፈውን መልእክት ህፃናት ወይም አስተማሪዎቻቸው አፅንኦት ሰጥተው እንዲያጠኑት ያደርጋል።

ከዚህ በላይ ከተመለከትነው በተጨማሪ "ምሳሌ" የሚለው ቃል ውክልናን እንዲያመለክት ተደርጐም ቀርቧል። በሶስቱም መፃሕፍት ውስጥ ሰንደቅ ዓላማና የእያንዳንዱ ቀለማት ውክልና ምንነት ተገልጿል። ለዚህ አስረጅ ይሆን ዘንድ <u>ታሪክና ምሳሌ ፩ኛ መጽሐፍ</u> (1966፣ ሰንደቅ ዓላማ) ላይ "...ሰንደቅ ዓላማችን፣ አረንጓደ፣ ቢጫና ቀይ ሶስት ቀለማት ናቸው። ምሳሌያቸውም አረንጓዴው ተስፋ፣ ልምላሜና ሀብት ቢጫው ሃይማኖት፣ አበባና ፍሬ፣ ቀዩ ፍቅር፣ መስዋዕትነትና ጀግንነት ነው" በማለት ተገልጿል። ይህም ምሳሌ የሚለው ቃል የእያንዳንዱን የሰንደቅ ዓላማ ቀለም ውክልና ያመለክታል።

"ምሳሌ" የሚለው ቃል ግንባር ቀደም ሆኖ መታየት "አርአያ" መሆን የሚል ፍቺ ይዞ አገልግሎት እንዲሰጥም ተደርጓል። ይህንን ለመገንዘብ ታሪክና ምሳሌ ፩ኛ መጽሐፍ (1966፡46) ላይ የሰፈረውን ሀሳብ እንጥቀስ፤"...አገልጋዮችህ ደግሞ ጊዜያቸውን በጨዋታና፣ በመማገጥ ያሳልፋሉ እንጂ ምንም ስራ አይሰሩ፤ አንተ ወደ ጨዋታ መሄድህን ስለሚያውቁ፣አንተ የምትሰጣቸውን መጥፎ ምሳሌ እየተከተሉ በልባቸው ስንፍና ያድራል" (ሰረዝ የራሴ)። በዚህ ጥቅስ ውስጥ "ምሳሌ" የሚለው ቃል የመጥፎ ተግባር አርአያ መሆንን ያመለክታል።

በሌላ በኩል ይኸው ቃል በዚህ ጽሁፍ ምሳሌያዊ ንግግር ብለን የጠራነውን የስነ-ቃል ዓይነት እንዲሰይም ተደርጓል። ቃሉ ለእንዲህ አይነቱ አገልግሎት ለመዋሉ አስረጅ ይሆን ዘንድ ታሪክና ምሳሌ ፫ኛ መጽሀፍ (1961፡15) ላይ ስለባልና ሚስት የሚያወሳ አንድ ተረት ከተነበበ በኋላ ምሳሌ በሚለው ቃል ንዑስ ርዕስነት የሚከተለው ተጽፏል። "ምሳሌ፤ ባልና ሚስት ፍትህና መንግስት፣ ምንም ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ፣ እንጀራ ያለወጥ፣ ቤት ያለሴት ክብት ያለበረት።" ከዚህም ምሳሌ የሚለውን ቃል ለስነ-ቃሉ ዓይነት መሰየሚያ ማገልገሉን እንገነዘባለን። እንዲህ አይነቱ አጠቃቀም በተረት ለተነገረ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ተረት ሳልሆነም ጭምር ሆኖ እናገኘዋለን። ታሪክና ምሳሌ ፫ኛ መጽሐፍ (1966፡4-6) "ትምህርት" በሚል ርዕስ ስለ ትምህርት አስፈላጊነት ጠቃሚ ምክሮች ከቀረቡ በኋላ "ምሳሌ፣ ትምህርት በልጅነት አበባ በጥቅምት፤ የተማረ ክብሩን መረመረ"፣ በማለት የቀረበው ይህንኑ ያረጋግጣል።

ከዚህም በላይ ሌሎች ሰዎች ለስነ-ቃሉ ዓይነት መሰየሚያ የተጠቀሙበትን "ተረትና ምሳሌ" የሚለውን የሁለት ቃሎች ጥምረት ታሪክና ምሳሌ ፫ኛ መጽሐፍ መቅድም ላይ ተጠቅመውበት እናገኛለን። ይህ የቃላት ጥምረት የስነ-ቃሉን ዓይነት ለመጥራት ማገልገሉን በእርግጠኝነት ለመናገር ቢያስቸግርም መገመት ግን ይቻላል። ከዚህም ምሳሌ የሚለው ቃል ለተለያየ አገልግሎት የሚውል መሆኑና ለስነ-ቃሉ ዓይነት የተሰጠው ስያሜም አንድ ወጥ አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

አበበ አይቼህ የተለያዩ ስነ-ቃሎችን ሰብስበው በሁለት መፃሕፍት አካተው አሳትመዋል። በሁለቱም መፃሕፍት ርዕስ ላይ "...ተረቶችና ምሳሌዎች..." የሚሉ ቃሎች አጣምረው ተገልግለዋል። "ተረትና ምሳሌ" ሲሉም በዚህ ፅሁፍ የምንነጋገርበትን የስነ-ቃል ዓይነት ማለታቸው እንዳልሆነ በመፃህፍቱ መቅድማትና በውስጥ በተካተቱት የስነ-ቃል ዓይነቶች እንገነዘባለን። ከዚህ ይልቅ የቃሉቹን ጥምረት የተገለገሉባቸው በአጠቃላይ በሰውና በእንስሳት ፀባህርያት አማካኝነት የተነገሩት ተረቶች "ጥንታዊ ግጥሞችና በአስቃ ገብረሀና ተነገሩ ባሏቸው" "ጨዋታዎች" እስቂኝና አስደናቂ ንግግሮች አማካይነት የተሳለፉ ቁምነገሮች ለልጆች ያስተማሩትን የህይወት ልምድ ለመግለፅ ነው። በመፃሕፍቱ ውስጥ በተካተቱት የተለያዩ ስነ-ቃሎች አማካይነት የተነገረው ቀም ነገር "ለክፉም ለመልካምም"

ተግባር በምሳሌነት መግለፅ እንዲችል የተሰጠ ስያሜ መሆኑን ከሚከተለው ገለፃ መረዳት ይቻላል።"የተዘጋጁት ተረትና ምሳሌዎች ውስጣቸውን በረቂቅ ሲመለከቱት ጥልቅ ምክሮች ሲሆኑ፤ እንዲሁም በጉልህ ዓይነት ሲመለከቷቸው ጊዜን ለማሳለፍ ንባቡ እጅግ ጣፋጭ ስለሆነ ተወዳጅ የማይጠገብ ስሜት ያለው መፅሐፍ ነውና ደስታ በአለው ንባብ ጊዜአችሁን አሳልፉ" (አበበ አይቸህ፣ 1942፤ መቅድም) (ስረዝ የራሴ)። "ተረትና ምሳሌዎች" ያሏቸው ስነ-ቃሎች "ጊዜን ለማሳለፍ" የሚነበቡ ከሆነ በመፃሕፍቱ ውስጥ የተካተቱትን ተረቶች፣ ግጥሞችና በተለያዩ ሰዎች የተነገሩ ንግግሮችን ማለታቸው እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። ምሳሌያዊ ንግግሮች ሲነበቡ እንደተረት ረዘም ያለ ጊዜ አይወስዱም። ከዚህም በላይ ምሳሌ የሚለውን ቃል ለምን ተግባር እንደተገለገሉበት "የሚያስረዳ ገለፃ በመፃሕፍቱ ውስጥ እናገኛለን።" "በአራዊትና በእንስሳት የሚነገሩ ምሳሌዎች እጅግ ጥሩ ናቸውና እስቲ እንመልከታቸው" (አበበ አይቸህ፣ 1948፡9) በሚለው ዐረፍተነገር ውስጥ "በአራዊትና በእንስሳት" ገፀባህርያት የሚነገሩ ተረቶች አማካኝነት ግብረገብ ማስተማሪያ መሆናቸውን ይጠቁማል።

አበበ አይቼህ በመፅሐፎቻቸው ውስጥ ለተካተቱ ጥቂት ተረቶች "ምሳሌያዊ ንግግር" የምንለውን የስነ-ቃል ዓይነት በአርእስትነትም ተጠቅመዋል። ለምሳሌ "ፊት የመቀመጫዬን እለች ዝንጀሮ" በሚል ርዕስ አንድ ተረት ያስነብቡናል። ነገር ግን ሁለቱ የስነ-ቃል አይነቶች ሲደጋገፉ መልእክትን ለማስተላለፍ የሚኖራቸውን ጉልበት ተገንዝበው ለመሆኑ በግልፅ ያሉት ነገር የለም። ስለዚህ ቀደም ሲል በሰይፉ በቀረበው ጥናት ላይ "ተረትና ምሳሌ" ለስነ-ቃሉ ዓይነት መሰየሚያ ይሆናል ተብሎ የቀረበው ስሌላም አገለገሎት የሚውል መሆኑን እንገነዘባለን።

ጳለታ ጳፈሮ፣ (1956)፣ ተረትና ምሳሌ በሚል ርዕስ እንቆቅልሾችን፣ተረቶችንና ምሳሌያዊ ንግግሮችን ሰብስበው አሳትመዋል። ይህ ፅሁፍ ትኩረት ያደረገበት የስነ-ቃል ዓይነት በመፅሀፋቸው ውስጥ "ምሳሌ" ተብሎ ተሰይሟል (1956፡6)። "ምሳሌ ከተረት ጋር ጎን ለጎን ሆኖ በብዙ ኢትዮጵያውያን ሲቃውንትና ንግግር አዋቂዎች ሲነገር ኖሮአል። ምሳሌ ከተጠና በኋላ ለማስታወስ ቢቀልም ምስጢራት ያሉት የንግግር ዓይነት ነው" (ስረዝ የራሴ)። እንደምንገነዘበው "ምሳሌ" ከተረት ጋር የሚነገር የስነ-ቃል ዓይነት ነው። ከተረት ጋር ጎን ለጎን ሆኖ ሲባል ከሌላ የስነ-ቃል ዓይነት ጋር በመሆን የሚሰጠውን አገልግሎት ይጠቁማል። ነገር ግን አንዳንዶቹ እንደሚሉት የተረት ርዕስ በመሆን ወይም ተረት ሲነገር በተረቱ ጣልቃ በመግባት ወይም ተረት ተነግሮ ሲያበቃ የመልእክት ማጉያ ሆኖ በመጨረሻ በመነገር የሚያገለግል መሆን አለመሆኑ በትክክል አልተመለከተም። ከተረት ተጨምቆ የተወሰደ ፍሬ ሀሳብ ስለመሆኑም ያሉት ነገር የለም። ይህንኑ ቃል በተረት አማካይነት የሚተላለፍ መልእክት ለህይወት ተመክሮ በመሆን የሚሰጠውን ትምህርታዊ አገልግሎት ለመግለፅም ተጠቅመውበታል።

> ምሳሌ ትምህርት ነው። ጥንት አባቶቻችን ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ እያሉ ያወሱ ነበር። ይህን መሰረት በማድረግ ልዩ ልዩ <u>ትምህርታዊ ተረቶችን</u> ከአማርኛና ከሌላም ነገድ ቋንቋ በመተርጉም ከራሴም በመጨመር ይህን መጽሐፍ አዘጋጅቼ በምስራች ድምፅ ስነፅሁፍ ድርጅት ታትሞ ቀርቦላችኋል (ጳለታ ጳፌሮ፣ 1956፤ 6) (ሰረዝ የራሴ)።

ፀሃፊው እንዳሉት "ምሳሌ ትምህርት ነው"። ለዚሁ ትምህርታዊ ተግባር እንዲያገለግሉ ብለው ያቀረቡዋቸውም "ትምህርታዊ ተረቶችን" ነው። እንደ ጳለታ አባባል ተረት ብለን የምንጠራው የስነ-ቃል ዓይነት ምሳሌ ነው። የመፅሀፋቸው ርዕስም የስነ-ቃሉን ዓይነት ማለትም ተረትንና በዚሁ ስነ-ቃል የተላለፈው መልእክት ትምህርታዊነቱን ለመግለፅ እንደ ተገለገሉበት ግልፅ ይቻላል። ስለሆነም ምሳሌ የሚለውን ቃል ለሶስት ተግባር አውለውታል። ተረት በሚል የሚታወቀውንና በዚህ ፅሁፍ ምሳሌያዊ ንግግር ብለን የጠራነውን የስነ-ቃል ዓይነት ለመሰየም፤ እንዲሁም በተረት አማካይነት የሚተላለፍ ቁም ነገር ሰውን የሚያስተምር መሆኑን ለመግለፅ ተጠቅመውበታል።

ይህንኑ የቃላት ጥምረት ከበደ ደስታም <u>ምሳሌና ተረት በእንስሳት አንደበት</u> (1971) በማለት የሃያ ሁለት ተረቶችን ስብስብ ለያዘው መፅሐፋቸው ርዕስ ተገልግለውበታል። በመፅሐፉ ውስጥ ከተካተቱት ተረቶች መካከል የአስራ አንዱ ርዕሶች የቆዩና አዳዲስ ምሳሌያዊ ንግግሮች መሆናቸውን ገልፀዋል።

> ከልዩ ልዩ የአነጋገር ፈሊጦችና የንግግር ስልቶች ጋር የእያንዳንዱ ግጥም መሰል አርእስት ሲታይም ኢትዮጵያዊውን የምሳሌ አተራረክ መነሻ የሚያሳስብ ነው። ለምሳሌ "ያገለገለ ተቀማጠለ። አጉል ፈዝ ያመጣል መዘዝ..." እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ <u>አዳዲስ</u> ም<u>ሳሌያውያን</u> አርእስት ሲሆኑ፣ አጋጣሚ ሲሆን ደግሞ "አውጪኝ እግሬ፣ ወርቅ ላበደረ ጠጠር..." የመሳሰሉት <u>ጥንታውያን</u> ምሳ<u>ሌዎችም</u> አልፎው አልፎው ለየክፍለ ታሪኩ አርእስት ሆነው ገብተዋል (ከበደ ደስታ፣ 1971 መግለጫ) (ሰረዝ የራሴ)።

በመጽሐፉ መግለጫ ላይ ርዕሱን ሲያስረዱም "ግብሩን ከነስሙ" ይዞ እንዲገኝ ለማድረግም የመፅሃፉ ስም "ምሳሌና ተረት በእንስሳት አንደበት" ተብሎአል በማለት ይገልፃሉ። ግብሩ በተረቶች ውስጥ በገፀባህርይነት በተፈጠሩ እንስሳት ወይም ሰዎች አማካይነት ለአድማጭ ወይም ለአንባቢ ትምህርት ሰጭነቱን በአጠቃላይ የተረትን የተለያየ አገልግሎት ያመለክታል። ተረት ለሰው ልጅ ትምህርት የሚሆን የህይወት ልምድ ምሳሌ ማቅረቢያ ነው የሚልን ሀሳብ ይጠቀማል። በዚህም ከጳለታ ጳፌሮ ጋር ይመሳሰላሉ። ከበደ ደስታ የተረትን ግብርና "ተረት" ብለን የምንጠራውን የስነ-ቃል ዓይነት አንድ ላይ አጣምረው ለመፅሐፋቸው ርዕስ አድርገው መገልገላቸውንም እንገነዘባለን። ይህንንም:-

> በተረትነቱ እያንዳንዳቸውን አራዊትና እንስሳት በስምና በመልክ በቅርፅና በጠባይ እያቀረበ በማሳቅና በማስገረም ሲያሜውት፥ በምሳሌነቱ ደግሞ በብልጥና በቂል፥ በትልቅና በትንሽ፥ በግዙፍና በኮሳሳ፥ በኃይለኛና በደካማ መካከል የሚፈፀመውን ውድድር እያሳየ በጭውውት መልክ ያስተምራል፥ ያስረዳል (ከበደ ደስታ፥ 1971፥ መግለጫ)።

ሲሉ ይገልፃሉ። በጥቅሱ ከተገለፀው ሃሳብም በመጽሐፉ ውስጥ ለተዘረዘሩት ብዙዎቹ ተረቶች ምሳሌያዊ ንግግሮች ርዕስ ሆነው በማገልገላቸው ምክንያት "ምሳሌና ተረት"፥ የሚለውን የቃላት ጥምረት እንዳልተገለገሉ መገንዘብ ይቻላል። ሆኖም መግለጫ ብለው ባሰፈሩት ፅሁፍ ላይ "ተረትና ምሳሌ"ን ስድስት ጊዜ "ምሳሌና ተረት" የሚለውን ደግሞ ሰባት ጊዜ ተገልግለውበት እናገኛለን። ከዚህም ሁለቱ ቃሎች ሲጣመሩ"ተረት" ወይም "ምሳሌ" የመቅደሙ ጉዳይ እንዳሳሳሰባቸው መገንዘብ ይቻላል።

ከበደ ደስታ "ምሳሌ" የሚለውን ቃል ይህ ፅሁፍ ትኩረት ባደረገበት የስነ-ቃል ዓይነት መሰየሚያ ለመገልገላቸው በመጽሐፋቸው ላይ እናነባለን። ይህንንም "ጥንታውያን ምሳሌዎችም..." በሚል ገልፀውታል። ሆኖም የስነ-ቃሉ አይነት የተሰየመበትና በተረት የሚተላለፍ መልእክት ለሰው ልጅ የህይወት መመሪያ መሆኑን የገለፁበት ቃል "ምሳሌ" የሚል ነው። ቃሉ ሁለቱንም ፍቺዎች እንዲይዝ አድርገው ተገልግለውበታል።

ምሳሌ" የሚለውን ስያሜ ከመረጡት ሰዎች መካከል አለማየሁ ሞገስ (1954፤48) ምንነቱን"ምሳሌ... ሃሳብ አልረዳ ሲል ብዙ እረፍተ ነገር ከማግበስበስ ለመዳንና በአጭሩ ለመግለፅ እንዲመች በአብዛኛው ህዝብ ዘንድ የተለመዱ አጫጭር አረፍተ ነገሮች ናቸው።" በማለት ያስረዳሉ። ይህ አባባል የስነ-ቃሉ አይነት የሚሰጠውን አገልግሎትና በመጠኑም ቢሆን ቅርፁን ይገልፃል እንጂ ስያሜው የተመረጠበትን ምክንያት አያስረዳም። በመሆኑም እንዲህ የሚል ስያሜ ተሰጥቶአል ከማለት ያለፈ ነገር አያስገነዝብም። እንደ አለማየሁ ምክንያታቸውን ያልገለፁት ፀጋ ገብረኪዳን (1958፡72) የስነ-ቃሉን አይነት "ምሳሌ" የሚል ስያሜ ሰጥተውታል።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ እንደተመለከተው "ምሳሌ" የሚለው ቃል ብዙ ፍቺዎች አሉት። "ምሳሌያዊ ንግግር" ብለን ለጠራነው የስነ-ቃል አይነት መሰየሚያነት ሊያገለግል የሚችል ፍቺም ተሰጥቶታል።

4. ለ"ምሳሌያዊ ንግግር" የተሰጡ ስያሜዎች አጠቃቀሞች

የስነ-ቃሉን አይነት ሰብስበው በመፅሀፍ መልክ ያሳተሙም ሆኑ ከሌሎች ስራዎቻቸው ጐን የጠቀሱ አበው ኢትዮጵያውያን በጋራም ሆነ በተናጠል በአንድ የሙያ

ቃል ሲጠሩት አይሰሙም። ሀጂ ፀሱፍ አብዱረሀማን <u>የአማርኛ ምርጥ ምሳሌና ተረት</u> (1942) በሚል ርዕስ በአማርኛ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ሰብስበው አሳትመዋል። ጸሐፊው የስነ-ቃሉን አይነት ሰብስቦ በማሳተም በኩል የመጀመሪያው ሰው ሳይሆኑ አይቀሩም። ለዚሁ የስነ-ቃል አይነት የሰጡት ስያሜ "ምሳሌና ተረት" የሚለውን የሁለት ቃሎች ጥምረት ነው። ይህም የመፅሐፋቸው ርዕስ ሆኖ ይነበባል። ነገር ግን ይህንኑ ስያሜ ሌሎች ሰዎች ተቀብለው ሲጠቀሙበት ብዙም አይታዩም።

ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል <u>የአባቶች ቅርስ</u> (1943) በሚል ርዕስ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ሰብስበው በማሳተም ሁለተኛው ሰው ናቸው። ለስነ-ቃሉ አይነት የሰጡት ስያሜ አንድ ወጥ አለመሆኑ በመፅሐፋቸው መግቢያ ላይ ይታያል። "ምሳሌ"፡ "ተረት"፣ "ምሳሌና ተረት"፣ "የምሳሌ ንግግር"ና "ተረት (ምሳሌ)" የሚሉትን ስያሜዎች እየለዋወጡ ተጠቅመውባቸዋል (አባሪውን ይመለከቷል)። ማኅተመስላሴ <u>የኢትዮጵያ ጥናት ቡሌ.2</u> (1961፣12) በሚለው መፅሐፋቸው "ምሳሌዎች አንዳንድ ጊዜም ተረቶች የምንላቸው" በማለት ሁለት ቃሎችን ለአንድ የስነ-ቃል አይነት መስየሚያ አድርገው መገልገላቸውን እንረዳለን። ሌላ ጊዜ ደግሞ "ምሳሌ (ተረት)" በማለት በቅንፍ ሁለተኛ ስያሜ ሰጥተው እናገኛለን።

ሞገስ ዕቁባጊዮርጊስ የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ሰብስበው ባሳተሙት <u>የኢትዮጵያ ጥንታዊ ምሳሌ (በአማርኛ)</u> (1959) በሚለው መጽሐፋቸው መግቢያ ላይ "ምሳሌ፣ ምሳሌና ተረት" የሚሉትን ስያሜዎች እያፈራረቁ ተጠቅመዋል። ለአንድ የስነ-ቃል ዓይነት የሚሰጠው ስያሜ አንድ ብቻ መሆኑ ተገቢ ነው። ይህ ሲደረግም የመግባባት ሂደቱን ቀልጣፋና ቀላል ያደርገዋል። አንዳንድ ጊዜ ወይም በሚል፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በቅንፍ የተሰጡት አማራጭ ስያሜዎች ትክክለኛ ስያሜ አሰጣጥን አያመለክቱም። ይህም በአንድ ሰው አንድ ዓይነት ስራ ውስጥ ቋሚ ስያሜ በመስጠት አለመገልገላቸውን ያስገነዝባል።

አንዳንዶቹ ለሰጡት ስያሜ ምክንያታቸውን ያቀርባሉ። መርስዔ ኀዘን ወልደቂርቆስ (1935፣221) "ምሳሌ (ተረት)" የሚባልበትን ምክንያት ሲገልፁ "በግብሩ ምሳሌ ይባላል፣ በጥንታዊነቱም ተረት ይባላል። " ይላሉ። ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (1945፣6) በበኩላቸው "ተረት ተብሎ መነገሩም ከመቼ ዘመን ጀምሮ እንደመጣ የማይታወቅ በመሆኑ ይሆናል" በማለት ይገልፃሉ። ተክለማርያም ፋንታዬም (1964፣137) "ተረት የተባለበት የቆየ ስለሆነ ነው። " በማለት ያስረዳሉ።

መርስዔ ኀዘን ስያሜውን የሰጡት አገልግሎቱንና ጥንታዊነቱን መሰረት በማድረግ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። ነገር ግን በጥንታዊነቱ ምክንያት "ተረት ተባለ" የሚለው ዳር የሚያደርስ ምክንያት አይደለም። ሌሎች የስነ-ቃል ዓይነቶችም ለብዙ ዓመታት በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የኖሩ ናቸው። ይህም የስነ-ቃሉን

ዓይነት በቃል ለሌላ ሰው የሚያስተላልፈው ሰው የሚጨምረው ወይም የሚቀንሰው እንዳለ ሆኖ ማለት ነው። ጥንታዊ መሆን "ተረት" ያስብላል ከተባለ ሁሉም የስነ-ቃል ዓይነቶች ተረት ናቸው ወደሚል የተሳሳተ ማጠቃለያ ያደርሳል። በቃል ከአባት ለልጅ ሲተላለፉ የኖሩ የስነ-ቃል ዓይነቶች ሁሉ ተረት አይደሉምና። እያንዳንዱ የስነ-ቃል ዓይነት የቆየ ቢሆንም የየራሱ መለያ ባህርይና ስያሜ አለው።

አስፋው ተፈራ (1950፡49) በበኩላቸው "የተረት"ንና የ"ምሳሌ"ን ምንነትና ጥምረት እንደሚከተለው ይገልፁታል።

> ተረት የጥንት አባቶቻችን በትርፍ ጊዜያቸው ይጫወቱት የነበረ የአንድ ሰው የአንድ እንስሳ ወይም የአንድ ነፍሳት ታሪክ ነው። ተረት የተባለበትም የቆየ ስለሆነ ነው። "ምሳሌ" ለተነገረው ታሪክ ወይም ነገር ማስረጃ ሆኖ የሚባል ነው። ተረት በምሳሌ ጠጅ በብርሌ እንደሚባለው ሁሉ ጠጅ በብርሌ ካልጠጡት ወጉን ስለማይዝ፡ ወይም ስለማያስደስት እንደዚሁም ተረትን በምሳሌ ካልተረኩት ስሜትን ይቀንሳል። ስለዚህ ተረትና ምሳሌዎች በሚነገሩበት ጊዜ መደጋገፍ ይገባቸዋል።

"ተረት" እና "ምሳሌ" ለሚሉት ሁለት ቃሉች የተሰጣቸውን ፍቺ ስንመለከት ተረት መቼና በእነማን እንደሚነገር እንዲሁም ገፀባህርያቱ እነማን ሲሆኑ እንደሚችሉ ያስረዳል። "የቆየ በመሆኑ ተረት ተባለ" የተባለውም ቀደም ብሉ እንደተገለፀው ስያሜ ለመስጠት በቂ የሆነ መመዘኛ አይደለም። የ"ምሳሌ" ምንነት የተገለፀው በአገልግሎቱ ብቻ ነው። "ተረትና ምሳሌ" የተባለበትን ምክንያት አስፋው (1950፡49) ሲያስረዱ ሁለቱ የስነ-ቃል ዓይነቶች ባላቸው የመደጋገፍ ባህርይ መሆኑን ገልፀዋል። ከዚህ በተጨማሪ በተረት አማካይነት የሚተላለፈውን መልእክት አጉልቶ ለማሳየት "ምሳሌ" እንደሚያገለግልና የመደጋገፍ ባህርያቸውም እንዲጣመሩና አንድን የስነ-ቃል ዓይነት ለመሰ የም እንዳስቻላቸውም አመልክተዋል። ተረት በ"ምሳሌ" እየተደገፈ እንደሚነገር ለማሳየትም ሁለቱን የስነ-ቃል አይነቶች አጣምረው፣ የሚከተለውን ምሳሌ አቅርበዋል።

> በአንድ አገር አንድ ባለፀጋ ከበላይ ሆኖ የሚያስተዳድራቸው ስድስት ሎሌዎች ነበሩት። እነዚህም አሽከሮች የሺ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ እንደሚባለው ጌትየው የሚሰጣቸው የዕለት ምክር እያስደሰ ታቸው ለብዙ ወራት በፍቅር በመተሳሰር በፍቃደኛነት ሲረዱት ቆየ (ኖሩ)።
>
> ይሁን እንጂ አብድ ቢጨምት ለጥቂት እንደተባለው እያደር ገንዘብ እነስን ድርጎችንም ቀረብን በማለት ማጉረምረም ጀመሩ። ምሬታቸውም ስለበዛ አንድ ቦታ ሄደው ችግራቸውን ለመወያየት ተማክሩና ወደተባለው ስፍራ ሄዱ።

> ከዚያም አንዱ ተነሳና "ጌታችን ቤት ስንቀመጥ ያገኘነው ጥቅም የለም። ስለዚህ ጉልበታችንን ዘከንቱ ከማሳለፍ ሌላ ጌታ ብንፈልግ ይሻላል" ሲል የተሰማውን አቀረበ። ሌሎችም በዚሁ ተስማምተው ነበር። ግን ሺ ተማክረ አንድ በወረወረ እንደሚባለው የፈፀመው አንዱ ብቻ ነበር። ሌሎቹ ግን አሜን ብለው ተመልሰው ወደ ጥንት ጌታቸው ገቡ። የሆነ ሆኖ ጥቂት ጊዜ እንደቆየ ያልጠረጠ ተመነጠረ እንደሚሉት እየመነጠቀ አስወጣቸው። ያኛው ግን ሌላ ጌታ ዘንድ የገባው በተድላና በደስታ ጊዜውን ካጠፋ በኋላ ውሎ ውሎ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከመሬት የሚቀር የለምና ሞተ ይባላል (አስፋው ተፈራ፣ 1950፣ 49-50) (ሰረዝ የራሴ)።

ከዚህ በላይ በሰፈረው ተረት ውስጥ አምስት ምሳሌያዊ ንግግሮች ተነተው ይነበባሉ። ይህንኑ ተረት ሌላ ሰው ከላይ በተመለከተው የምሳሌያዊ ንግግር አጠቃቀም መልክ ይተርከዋል ማለት ያስቸግራል። ሁለቱ የስነ-ቃል ዓይነቶች በዚህ መልክ ሁልጊዜ ይደጋገፋሉ ማለትም አይቻልም። አብዛኛውን ጊዜ ተረት በዚህ ዓይነት ምሳሌያዊ ንግግር አጠቃቀምና መደጋገፍ ሲቀርብ አይታይም። ተረት እንዴት እንደሚነገር ካለን ልምድ አንፃር ይህ አይነቱን አባባል ምሳሌ አቅራቢው ሆን ብለው ያደረጉት ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። ተረት ሁልጊዜ በምሳሌያዊ ንግግር እየታገዘ አይተረክም። ይህ በመሆኑ ደግሞ ተረቶች ሳድማጩ ወይም ላንባቢው ስሜት ርቀት አላቸው ማለት አይቻልም። መልእክታቸውም አይደበዝዝም።

አንድን ተረት ለሕፃናት በምሳሌያዊ ንግግር ሳናስደግፍ ብናቀርብላቸው በስሜት ሊያዳምጡ ወይም ሊያነቡ ይችላሉ። በአንፃሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በተረቶች የትረካ ሂደት ውስጥ እየደጋገሙ በማስገባት መገልገል በሕፃናቱ የማዳመጥ ወይም የማንበብ ፍላጎት ላይ መደናገርንና መሰላቸትን ሊያስከትል ይችላል። የዚህ ምክንያት አንደኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች ታሪክን፣ እምነትን፣ ፍልስፍናን፣ ልምድን በአጠቃላይ የህይወት ገጠመኝን መሰረት ያደረጉና እምቅ ሀሳቦችን የያዙ በመሆናቸው ለሕፃናቱ ግንዛቤ ከብደት ይኖራቸዋል፣ ለመረዳትም ያስቸግሯቸዋል። ሁለተኛው ከሚነገረው ወይም ከሚነበበው ተረት በዐረፍተ ነገር ቅንብርም ሆነ በሀሳብ ወጣ ይላሉ። ይኸውም አንዳንዶቹ ቁጥርን አስተካክለው ማሰሪያ አንቀፅን አሟልተው ስለማይነገሩ በአዕምሮ ላልበሰሉና ቋንቋውን በመልመድ ላይ ላሉ ሕፃናት በምሳሌያዊ ንግግሮች የተነገረውን ሀሳብ እንዳይረዱ ተጨማሪ ችግሮች ናቸው። ምሳሌያዊ ንግግሮችን በትረካው ሂደት እያስገቡ መገልገል ሕፃናት የቀረበላቸውን ተረት ሲያዳምጡ ወይም ሲያነቡ እንዲቸገሩ ያደርጋል። ከዚህ ሌላ አንድ ተረት ተራኪ በትረካው ሂደት ውስጥ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ጣልቃ እያስገባ አያቀርብም። ሕፃናቱም ያለ ምሳሌያዊ ንግግሮች ቢተረክላቸው ደስ ብሏቸው ሊያዳምጡ፣ ሳይደናቀፉ በተረቱ የቀረበውን ጉዳይ ሊገነዘቡ ይችላሉና። ስለዚህ "ተረትን በምሳሌ ካልተረኩት ስሜትን ይቀንሳል" ብሎ ማጠቃለል አይቻልም። ተረቶች የምሳሌያዊ ንግግር ማሰረጊያ ሳይኖራቸው ሊነገሩ ይችላሉና።

በሌላ በኩል ክብረአብ አድማሱ (1977፣19) ተረትና ምሳሌ መባሉ ብዙ ምሳሌዎች ተረትን ስለሚያስከትሉ ወይም ከተረት የተወሰዱ ፍሬ ነገሮች ስለሆኑ ነው

ይላሉ።ምሳሌዎች ተረት የሚያስከትሉ ወይም ከተረት ተጨምቀው የሚወሰዱ ፍሬ ነገሮች ስለመሆናቸው በደስታ ተክለወልድ (1928፤55) መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን የምሳሌና ተረት ቁርኝት መመልከቱ ለግንዛቤ ይረዳል።

> እባብ በክረምት ውሃ ሞልቶበት ዳር ዳሩን ሲንቀዋለል አንድ ሰው መጣ፤ እባቡም ሰውዬ እባክህ አሻግረኝ ብሎ ለመነው። ያም ሰው እጅ የለህ፥ እግር የለህ፥ ምንህን ይዤ ነው የማሻግርህ አለው። እባቡም ፈቃድህስ ከሆነ ራስህ ላይ ጠምጥመኝ ቢለው ጠምጥሞ አሻገረው። ካሻገረው በኋላ በል ውረድልኝ ቢለው እንቢ አልወርድም አለ። ወደ ዳኞች (አራዊትም) ኹሉ ሄዶ ቢከሰው ዳኞቹ (አራዊቶቹ) በገዛ እጅህ እባብ ራስህ ላይ ጠምጥመህ እያሉ ፈረዱበት። በመጨረሻም በቀበሮ ዳኝነት ከሰሰው፥ ቀበሮዋም እባብን እምድር ወርደህ በግራ ቆመህ ስራት ለብሰህ ተነጋገር አለችው፤ እሱም ተተረተረና ዱብ አለ። ከዚኽም በኋላ ቀበሮዋን ሰውዬው እህ አላት፤ እሷም ሰው በትር ይዞ ቆሞ፥ እባብ እምድር ተጋድሞ ብትለው ራስ ራሱን ብሎ ቀጥቅጦ ገደለው። ችሎትም ሲመለስ ብድሯን ለመክፈል ማታ በግ አመጣልሻለሁና ቤትሽን አሳዩኝ አላት፤ እሷም አስከትላው ሂዳ ቤቷን አይቶ ተመለሰ።ማታም ውሻውን አስከትሎ በመሄድ ከበርአፏ ቆሞ "እንኮይ ቀበሩት ብቅ በዪ አላት፤ በግ ይዞልኝ መጥቶ ይኾናል አለችና ብቅ ብትል ያዢ ኩቲ ብሎ ውሻውን ለቀቀባት፥ እሷም ሰው ሰው ሰው ለሰው ሞት አነሰው እያለች ወደቤቷ ጥልቅ አለች።

ተረቱ ቀበሮ ውለታ የሰራችለት "ወዳጅ ነው" ብላ የገመተችው ሰው የወዳጅ ጠላት በመሆን እሷን ለመጉዳት ባደረገው ሙከራ እጅዋ አመድ አፋሽ ስለመሆኑ የተሰ ማትን የሀዘን ስሜት የገለፀችበት ነው። ይህ የታሪኩ አካል የሆነው"... ለሰው ሞት አነሰው" ምሳሌያዊ ንግግር በመሆን ይታወቃል። ስለሆነም "ለሰው ሞት አነሰው" አለች ቀበሮ እየተባለ የሚነገረውን ምሳሌያዊ ንግግር ስንሰማ ለምን እንደዚህ እንደሚባል ብንጠይቅ የተጠቀሰውን ተረት ታሪክ እንድናውቅ ወይም እንድንናገር ይገፋፋናል። ስለዚህ ምሳሌያዊ ንግግሩ ተረት ማስከተሉን እንገነዘባለን። ምሳሌያዊ ንግግሩም ከተጠቀሰው ተረት የመጨረሻ ሃሳብ የተወሰደ ነው። ሆኖም አንዳንድ ምሳሌያዊ ንግግሮች በተረት ከተነገረ ሀሳብ ተጨምቀው ሊወጡና ሊወሰዱ ቢችሉም የሁሉም ምንጫቸው ይኸው ብቻ ነው ማለት ግን አይቻልም። ምሳሌ ተረትን ያስከትላል ከተባለም ስያሜው ምሳሌና ተረት መባል ነበረበት።

የሙያ ቃሉ በተለያየ ስያሜ እየተደበላለቀ መጠራቱንና አሳቸው የመረጡትን ስያሜ ክብረአብ (1977፤14) እንደሚከተለው ይገልፁታል።

> በሀገራችን ምሳሌ ማለትና ታሪክና ምሳሌ ተረትና ምሳሌ የሚባሉ አባባሎች አንዳንዴ ሲደበላለቁ ይታያሉ። አንዳንድ ምሳሌዎች የተረት ርዕስ ወይም የተረት ማሰሪያ ማሳረጊያ ስለሆኑ ተረትና ምሳሌ ይባላሉ።
> አንዳንድ ምሳሌዎች ታሪክ ልብወለድ ስለሚያስከትሉ ታሪክና ምሳሌ ይባላሉ። አንዳንድ ጊዜ አይነቱን ከሌላው ለመለየት ምሳሌያዊ አነጋገር በመባል ቢታወቅም፥ ይህ ጥናት የሚከተለውና የሚመረምረው በአጠቃላይ ስሙ ምሳሌ የተባለውን አጭሩን አነጋገር ነው።

"ተረትና ምሳሌ" ባላቸው መደጋገፍ ምክንያት "ተረት በምሳሌ ዜማ በሃሌ" እየተባለ ይነገራል። ክብረአብ እንዳሉት "ምሳሌ" የተረት ርዕስ በመሆን ያገለግላል። ለዚህ ብዙ ማስረጃ ማቅረብ ቢቻልም ቀደም ሲል የተጠቀሰው "ለሰው ሞት አነሰው" በሚል ርዕስ የተነገረው ተረት በቂ ማስረጃ ይናሆናል። ነገር ግን ምሳሌ በርዕስነት የሚያገለግለው ለተረት ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ፅሁፎች ጭምር ነው።

ከዚህ ሌላ ምሳሌ የተረት ማሰሪያ (ማሳረጊያ) እንደሚሆን ማንተመ ሥላሴ (960፤62) ካሳተሙት የተረት ስብስብ ውስጥ እናነባለን። ነገር ግን አንድ ተረት በቃል ከተተረከ በኋላ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ለተረቱ "ማሰሪያ ማሳረጊያ" እንዲሁም ለመልእክት ማተያነት ብዙውን ጊዜ እንደማንነለገልበት መናገር ይቻላል። ስለዚህ በፅሁፍ ላይ የምናየው የሁለቱ የስነ-ቃል ዓይነቶች ቁርኝት በቃል በሚነገርበት ጊዜ የተለየ እንደሚሆን ማጤን አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ተረቶች በቃል በሚተረኩበት ጊዜም ለመልእክት ማተያ በሚል ምሳሌያዊ ንግግሮችን ተራኪው አብዛኛውን ጊዜ እንደማይጠቀም ማስተዋል ይገባል።

የምሳሌያዊ ንግግሮች አገልግሎት ሰፊ በመሆኑ በገደብ የሚወሰን አይደለም። ከተረት ጋር ብቻ በመደጋገፍ እንደሚነገሩ አድርጎ በመቁጠር ስያሜ መስጠትም ትክክል አይሆንም። በማንኛውም አጋጣሚ ሀሳብን ግልፅ ለማድረግ በቃልም በፅሁፍም እንገለገልባቸዋለን። ይህንን የበለጠ ለመረዳት በደስታ ተክለወልድ (1928፤55-56) መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን የታሪክና የምሳሌያዊ ንግግር መደጋገፍ እንመልከት፤

> በኃይለመለኮት ጊዜ አንዱ የወግዳ ሰው ክፉ ስራ ሰለሰራ ቤቱ ሲወረስና ከብቱ ሲቆጠር ባሪያውን በጕተራ ውስጥ ደበቀው። ሹሞቹም ከብት ከገባ በኋላ መጥተው ቤቱን ሲይዙና ከብቱን ሲቆጥሩ ያ ባሪያ በከብቱ መካከል እያቀናጀ ጉልማውን የሚያርስበት አንድ በሬ ነበረውና ራሱን ከጕተራው ውስጥ ብቅ ዘለግ አድርጎ ይመለከት ጀመር፤ ሹሙም ከብቱን ሁሉ እየቆጠረ ከሁለት በሬ አጠገብ ሲደርስ አየና ተው አያ እሱ የኔ በሬ ነው ብሎ ቢጮህ አንተም እዚህ ኑረሃልን ብሎ ከጕተራው ውስጥ ጐተተና አውጥቶ ወሰደው፤ <u>በለፈለፉ ባፍ ይጠፉ</u>። (ሰረዝ የራሴ)

በአንድ ወቅት ወይም አጋጣሚ የተፈፀመን ድርጊት ለመግለፅ የተነገረውን ጉዳይ የበለጠ ለማብራራት ፀሃፊው "በለፈለፉ ባፍ ይጠፉ" የሚለውን ምሳሌያዊ ንግግር የታሪኩ መቋጫ አድርገው ተጠቅመውበታል። ስለዚህ ይህ የስነ-ቃል ዓይነት ሁልጊዜ ተረትን ተከትሎ እንደሚመጣ አድርጎ በማሰብ "ተረትና ምሳሌ" በማለት አጠቃሎ መሰየም ስህተት ይሆናል።

ታሪክና ምሳሌ የሚለው የሁለት ቃሎች ጥምረት የስነ-ቃሉ ዓይነት የተሰየመበት መሆኑን ተመልክተናል። ሰዎች ታሪክና ምሳሌ የሚለውን ስያሜ መጠቀማቸው ምሳሌው ታሪክን ስለሚያስከትል ነው። ይህም የሚነገረው ወይም የሚጠቀሰው "ምሳሌ" የያዘው

ሀሳብ መነሻው በአንድ ወቅት የተፈፀመ ታሪክ በመሆኑ ነው። ይህንን ይበልጥ ለመገንዘብ "ሀዘንሽ ቅጥ አጣ ከቤትሽ አልወጣ" የሚለው ምሳሌያዊ ንግግር መነሻ ያደረገውን ታሪክ እንመልከት።

አፄ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ ራሳቸውን በመግደላቸው የስልጣን ክፍተት ይፈጠራል። የላስታው ባላባት ዋግሹም ጉባዜና የእንደርታው ባላባት ደጃዝማች ካሳ ምርጫ ለየራሳቸው የስልጣን ይገባኛል ጥያቄ ይዘው ይፎካከራሉ። እቴጌ ድንቅነሽ፣ የደጃዝማች ካሳ እህት፣ ዋግሹም ጉባዜን አግብተው ይኖሩ ነበር። ከዚያም ዋግሹም ጉባዜ ስመ መንግስታቸውን ተክለጊዮርጊስ አስብለው ይነግሳሉ። የእሳቸውን ንግሥና ያልተቀበሉትና ራሳቸውንም ለማንገሥ የፈለጉት ደጃዝማች ካሳ አፄ ቴዎድሮስን ለማጥቃት ከመጡ የእንግሊዝ ወታደሮች በተቀበሉት የጦር መሳሪያ ጉልበታቸውን አደርጅተው ለንጉሥ ተክለጊዮርጊስ አልታዘዝም፣ አልገብርም ይላሉ። በሚስታቸው ወንድም ድርጊት የተበሳጩት ንጉሥ ተክለጊዮርጊስ አማቻቸውን ለማስገበር ከተለያዩ ግዛቶቻቸው ጦር አስከትለው ከላስታ በመነሳት ወደ ትግራይ በምተው በ1863 ዓ.ም. አድዋ አጠገብ ጦርነት ይገጥማሉ። በዚህ ጦርነት ደጃዝማች ካሳ ያሸንፋሉ። ተሸናፊው ንጉሥ ተክለጊዮርጊስ ተማርከው ከልጆቻቸው ጋር አምባ ሰላማ በሚባል ተራራ ይታሰ ራሉ። ደጃዝማች ካሳ ምርጫም ስመ መንግስታቸውን አፄ ዮሐንስ ብለው ይነግሳሉ። የእህታቸውን እቴጌነት ያከብራሉ። በተራራ ላይ የተጋዙት ንጉስ ተክለጊዮርጊስ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ይሞታሉ (ተክለጻድቅ መኩሪያ፣1982)። እቴጌ ድንቅነሽ በባላቸው መሞት ያዝናሉ። ባላቸውን አስረው እንዲሞቱ ያደረጉት ነጋሲው ወንድማቸው በመሆናቸው ሀዘናቸው ቅጥ ያጣል። በጊዜው ይህንን ድርጊት የሚያውቅ ማንነቱ ያልታወቀ ሰው የንጉሥ ተክለጊዮርጊስን ባለቤት በድርጊቱ ግራ መጋባት በመረዳት፦ "የገደለው ወንድምሽ፣ የሞተውም ባልሽ፣ ሃዘንሽ ቅጥ አጣ፣ ከቤትሽ አልወጣ።"(ከብረአብ፣ 1977፣17) በማለት ይገጥማል /ገጣሚዋ ሴትም ልትሆን ትችላለች/። ግጥሙ ታሪኩን መነሻ ያደረገ በመሆኑ ገዳይ ወንድም ሟች ባል መሆኑን ይገልፃል። ከግጥሙ የመጨረሻዎቹ ሁለት ስንኞች በምሳሌያዊ ንግግሮች ዝምችት ውስጥ ተካተዋል። አንድ ምሳሌያዊ ንግግር ሆነውም ይጠቀሳሉ። እንዲሁ ግጥሙ ምሳሌያዊ ንግግር ሆኖም ይነገራል። መነሻውም በአንድ ወቅት የተፈፀመ ታሪካዊ ድርጊት ነው። ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ሆኖ አገልግሎት መስጠት የጀመረው ከታሪካዊ ክንዋኔው በኋላ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። የተፈጠረው ይህን ታሪካዊ ድርጊት መነሻ አድርጐ ነው ማለት ከተቻለ። የስነ-ቃሉ ዓይነት ዛሬ በተለያዩ መፃሕፍት ውስጥ በስብስብነት ተካቶ ይገኛል።

በሌላ በኩል ደግሞ የስነ-ቃል አይነት የተገኘበት ግጥም ድርጊቱን የፈፀመውንና ድርጊቱ የተፈፀመበትን በመለዋወጥም ይነገራል። የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ (1982፣208) "የገደለው ባልሽ፣ የሞተው ወንድምሽ፣ ሃዘንሽ ቅጥ አጣ፣ ከቤትሽ አልወጣ።" በሚል እንደሚነገር በስብስቡ ውስጥ አካቷል። ገዳይ ባል፣ ሟች ወንድም ሆኖ የተነገረበት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንደኛው ሊሆን ይችላል። ግጥሙ በቃል

ከትውልድ ወደ ትውልድ በትክክል ባለመተላለፉ ወይም በሌላ አጋጣሚ ላይ ባል ጉዳይ ወንድም ሚች በመሆን የተፈፀመ ድርጊት በመኖሩ ቀደም ብሎ የነበረውን የግጥም ቅርፅና በከልፈም ይዘቱን ሰዎች ተገልገለውበት ሲሆን ይችላል። እንዲህ ዓይነት ለውጥም የስነ-ቃል አንዱ ባህርይ ነው።

ቀደም ብሎ እንደተመለከትነው አንዳንዶቹ ምሳሌያዊ ንግግሮች በአንድ አጋጣሚ ላይ የቀረበን ታሪክ ግልፅ ለማድረግ በታሪኩ መጨረሻ ላይ ይጠቀሳሉ። ሌሎቹ ደግሞ አንድን ታሪካዊ ክንዋኔ መነሻ አድርገው የሚነገሩ ናቸው። በመሆኑም የታሪካዊ ድርጊት መነሻ ያላቸውን ወይም በአንድ ታሪክ የተላለፈን መልእክት ለማጉላት የሚጠቀሱትን "ምሳሌዎች" በማጤን ታሪክና ምሳሌ የሚል ስያሜ መስጠት በአንድ በኩል ተገቢ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ አንድ "ምሳሌ" ሲጠቀስ ታሪክን የሚያስከትል ከሆነ "ምሳሌና ታሪክ" ወደሚል ስያሜ እንድናመራ ያደርጋል-ቀድሞ "ምሳሌው" በመነገር ታሪኩን የሚያስከትል በመሆኑ። ሆኖም ለሁሉም "ምሳሌዎች" የታሪክ መረጃ ስለማይጠቀስላቸው እንዲሁም ሁልጊዜ "ምሳሌዎች" የአንድን ታሪክ መልእክት ለማጉልበት ከታሪኩ በስተመጨረሻ ወይም በመሃል ብቻ ስለማይጠቀሱ ለስነ-ቃሉ አይነት መሰየሚያ "ታሪክና ምሳሌ" ይሆናል ብሎ ማጠቃለል ትክክል አይሆንም። "ታሪክና ምሳሌ" ተብሎ የተሰየመውን የስነ-ቃል አይነት ከሌላው ለመለየት "ምሳሌያዊ አነጋገር" እንደሚባል ክብረአብ አድማሱ ገልፀዋል። ነገር ግን "ምሳሌያዊ አነጋገር" ከማለት ይልቅ ለምን "ተረትና ምሳሌ" ወይም ሌላ አይባልም? ከዚህ ሌላ "አይነቱን ከሌላው ለመለየት" ሲባል ምን ማለት ነው? ለእነዚህ ጥያቄዎች የክብረአብ ጥናት መልስ አይሰጥም። "ታሪክና ምሳሌ" የሚለው ስያሜ "ምሳሌያዊ አነጋገር" እንደሚባል ብቻ ይገልጻል እንጂ።

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ታሪክና ምሳሌ ወይም ተረትና ምሳሌ ብሎ ስያሜ ለመስጠት ሰዎች ምክንያት አላቸው። "ምሳሌ" ከተረት ወይም ከታሪክ ጋር ተጣምሮ በመነገር መሰየሚያ መሆኑ በአንድ በኩል ተገቢ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ጉድለት አለበት። በቁጥር ውሱን የሆኑትንና የታሪክ ወይም የተረት መነሻ ያላቸውን ወይም የተረት ማሰረጃ የሆኑትን ወይም ተረት ሲተረት ወይም ታሪክ ሲነገር በታሪኩ መካከል የሚጠቀሱትን ምሳሌያዊ ንግግሮች ብቻ በማጤን ሁሉንም በተመለከቱት የቃላት ጥምረቶች በአንደኛው አጠቃሎ መሰየም ትክክል አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ በታሪክ ወይም በተረት የቀረበን ሀሳብ የበለጠ ግልፅ ለማድረግ ብቻ ነው የሚያገለግሉት ማለትም የምሳሌያዊ ንግግሮችን ሰፊ አገልግሎት መወሰን ይሆናል።

ከእነዚህ ስያሜዎች ሌላ ክብረአብ አድማሱ የመረጡትና ጥናታቸው የሚመረምረው "በአጠቃላይ ስሙ ምሳሌ የተባለውን አጭሩን አነጋገር" መሆኑን ገልጸዋል። "ምሳሌ" የሚለውን ስያሜ የመረጡበት ምክንያት በአጭርነቱ እንደሆነም ከገለፃቸው እንገነዘባለን። ነገር ግን ሌሎች ሰዎች የስነ-ቃሉን አይነት ይጠሩባቸዋል ካሏቸው ስያሜዎች የእሳቸው የሚለይበትንና ተገቢነቱም በምን በምን ምክንያት እንደሆነ

ዘርዝረው አላስረዱም። ከዚህ ሌላ የመረጡት ስያሜ "ምሳሌ" የሚል ብቻ ሳይሆን "አነጋገር" የሚል ቃል አጣምረው "ምሳሌያዊ አነጋገር" በሚል እንደሆነ ከስያሜያቸው ገለፃ እንረዳለን። በጥናታዊ ፅሁፋቸው ባተለያዩ ገፆች ላይ ምሳሌያዊ አነጋገር በሚል ስያሜ ለውጠው መጠቀማቸውንም እንመለከታለን። ስለሆነም ከብረአብ የሰጡት ስያሜ አንድ ካለመሆኑም በላይ ምክንያታቸውን በትክክል አይገልፅም።

" መኩሪያ ወርቁ(1982፡6) በበኩላቸው ምሳሌያዊ አነጋገር የሚለውን ስያሜ ለምን እንደተጠቀሙ ሲያስረዱ፡-

> ስለመፅሃፉ ስያሜ አላማና አገልግሎት አሳብ ካካፈልኳቸውና ምክር ከጠየቅኋቸው አንዳንድ ወዳጆቼ ጋር ልዩ ልዩ አማራጭ ርዕሶች መዝግበን የተሻለ ሆኖ ያገኘነው "ምሳሌያዊ አነጋገር" የተሰኘውን ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ያንዳንዱ ምሳሌያዊ አነጋገር ተረት መሰልነት አላማውና መንፈሱ ለምሳሌነት መጠቀሚያ ስለሆነ ነው። ለምሳሌ "የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች" ይላል። ሌላውም ሁሉ እንደዚሁ ነው።

ብለዋል። ይህን ለመምረጥ ምን ምን አማራጭ ስያሜዎችን አቅርበው እንደነበርና "ምሳሌያዊ አነጋገር" የሚለውን የቃላት ጥምረት ካቀረቧቸው አማራጮች በምን ተሽሎ እንደተመረጠ አያስረዳም። ያንዳንድ ምሳሌያዊ አነጋገር ተረት መሰልነት መኖሩ የተመለከተውን ስያሜ ለመስጠት እንዴት እንዳስቻለም አያብራራም። ስለሆነም የተመለከተው የቃላት ጥምረት ለመፅሐፋቸው ርዕስ የተጠቀሙበት ነው ከማለት ውጭ የመረጡበትን መሰረታዊ ሀሳብ ትክክል ነው ወይም አይደለም በማለት ለመተቸት አይቻልም። ያም ሆኖ ሌሎች ስያሜዎችን በተለዋጭነት ተገልግለውባቸዋል (አባሪውን ይመለከቷል) ። በተጠቀሙበት ስያሜ ውስጥም ምሳሌ በሚለው ቃል 'ይ' '-አዊ' የሚል ምዕላድ ተጨምሮበታል። የተጨመረው ምዕላድም የወገን ቅፅል አመልካች ነው። 'አ' የሚለው ፊደል ወደ 'ያ' የተለወጠበት ምክንያት "ምሳሌ" የሚለው ቃል ሲነበብ 'የ' የሚል ድምፅ በቃሉ መጨረሻ ላይ ይሰማል። ይህ 'የ' የሚል ድምፅ 'አው' ከሚለው ወገን አመልካች ቅፅል ጋር ሲጣመር 'አ' ና 'የ' ተዋህደው ራብዕ 'ያ'ን ይሰጥና 'ያዊ' ወደሚል ምዕላድ ይለወጣል። ይህም 'አ' ከማንኛም የግዕዝ ፊደል ጋር ሲዋሀድ በሚታይበት ባህርይ መሰረት መሆኑ ነው። 'ያዊ' የሚለው ምዕላድ "ምሳሌ" ከሚለው ቃል ጋር ሲጣመር "ምሳሌያዊ" የሚል ቃል ይሰጣል። ስለሆነም ምሳሌያዊ ሲባል የምሳሌ ወገን የሆነ ማለት ነው። በዚህ ፅሁፍ ምሳሌ የምንለው በተረት፣ በታሪክ ወይም በሌላ ምክንያት የተነገረን ጉዳይ መነሻ ያደረገ ወይም በልዩ በምክንያት ተነግሮ ልዩ ልዩ ጉዳይን ለማስረዳትና ለማብራራት በቃልም በፅሁፍም የሚጠቀስ የነገር መግለጫ ነው።

"ምሳሌያዊ አነጋገር" በሚለው መሰየሚያ ውስጥ "አነጋገር" የሚለው ቃል ደግሞ የአገሊት ወይም የአገሌ አነጋገር የሚል ስሜት አለው። ይህም ለግለሰብ ወይም ለግለሰ

በች የባለቤትነት መብትን የሚሰቅና የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ ለልዩ ልዩ ጉዳይ መገልገያ መሆኑን ያመለክታል። ስለዚህ "ምሳሌያዊ አነጋገር" ሲባል የ"ምሳሌ" አጠቃቀምን ድርጊት ስለሚያመለክት የግንኙነት መግለጫ ነው። ይህም በመሆኑ የስነ-ቃሉ አይነት መሰየሚያ አድርጐ ለመቀበል የሚያስቸግር ይመስላል።

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካደሚ እንዲሁም በአንዳንድ ሰዎች ስራዎች ላይ አልፎ አልፎ እንደሚታየው "ምሳሌያዊ ንግግር" የሚለው ስያሜ እየተለመደ መጥቷል። ምሳሌያዊ በሚለው ውስጥ የስርወ ቃሉንና የምዕላዱን ጥምረት ቀደም ሲል ለማሳየት ተሞክሯል። ቀጥሎ የምንመለከተው "ንግግር" የሚለው ቃል "ምሳሌያዊ" ከሚለው ቃል ጋር ተዋህዶ ለሙያ ቃሉ መሰየሚያ ሊሆን ስለመቻሉ ነው። "ንግግር" የሚለው ቃል ሀሳብን በቃል ለሌላ ሰው ወይም ሌሎች ሰዎች ማስተላለፍን ይገልፃል። የፅሁፍ ጥበብ ባልተስፋፋበት ህብረተሰብ ውስጥ አንድ ሰው "ንግግር አደረገ" ሲባል በቃል መልእክት አስተላለፈ ማለት ነው። የፅሁፍ ጥበብ በተስፋፋበት ህብረተሰብ ውስጥ ደግሞ እገሌ በህዝብ ፊት ንግግር አደረገ ሲባል በቃል ይልቁንም በፅሁፍ እንደተናገረ እንገምታለን። ይህም በፅሁፍም ንግግር ማድረግ የተለመደ መሆኑን ይጠቁማል። ይህ ማለት ግን ሀሳብን ለሌላ ለማስተላለፍ በቃል ንግግር ማድረግ ቀሚል ማለት አይደለም። በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ስነ-ቃልና ስነ-ፅሁፍ እንዳላቸው ተጣምሮ በቃልም በፅሁፍም ንግግር ማድረግ የዘወትር ክስተት ነው። ስለዚህ ንግግር የሚለው ቃል በቃል ሀሳብ ማስተላለፍን ይገልፃል። ከዚህ በተጨማሪ ንግግር የነገር መጠሪያ ነው።

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ምሳሌያዊ የሚለው ቃል የምሳሌ ወገን የሆነ የሚል ፍቺ ይሰጣል። ንግግርና "ምሳሌያዊ" የሚሉትን ቃላት አንድ ላይ አጣምሮ መሰየሚያ ማድረጉ የስነ-ቃሉ አይነት የምሳሌ ወገን መሆኑንና ከትውልድ ወደትውልድ በቃል ሲተላለፍ መኖሩንና ዛሬም የሚተላለፍ መሆኑን ያስገነዝባል። ስለሆነም ሁለቱ ቃላት ተጣምረው "ምሳሌያዊ ንግግር" በሚል የስነ-ቃሉን ዓይነት እንዲሰይሙ መደረጋቸው ስነ-ቃላዊነቱንና ዓይነቱንም በትክክል መግለጽ ብቻ ሳይሆን የስያሜ ችግሩን ሊቀርፍ ይችላል።

5. ማጠቃለያ

በአማርኛ የሚነገሩ የተለያዩ የስነ-ቃል አይነቶችን መሰብሰብና ማሳተም ከተጀመረ በርካታ ዓመታት ተቆጥረዋል። አበው ኢትዮጵያውያን ካሳተሙዋቸው የስነ- ቃል መጻሕፍት ሌላ ስለ ኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ያደረጉ የውጭ ሀገር ሰዎች የተለያዩ ዓላማዎችን መሰረት አድርገው የተለያዩ ስነ-ቃሎችን በየስራዎቻቸው አካተው አሳትመዋል። ይሁን እንጂ በሀገራችን ስነ-ቃል በአንድ የሙያ መስክነት መታወቅ የጀመረው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ክፍል ስነ-

ቃል በትምህርት ዓይነትነት መሰጠት የተጀመረው፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካደሚ እንደ አንድ የጥናትና ምርምር መስክ መታየት ከጀመረ ከሁለት አስርታት አይበልጥም። ይኸው የሙያ መስክ ስነ-ቃል በሚል መጠሪያ ከመታወቁ በፊት የተሰያዩ ስያሜዎች ይዞ ቆይቷል። "ስነ-ቃል" የሚለው ስያሜ ዛሬ በስፋት እየተለመደ መምጣቱን በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን እናነባለን፤ ወይም እንሰማለን።

በአማርኛ ከሚነገሩት የስነ-ቃል አይነቶች መካከል አንድ ትክክለኛ ስያሜ በመስጠት መገልገል የመግባባት ደረጃን ከፍ ያደርጋል። ስለዚህ ስያሜ ሳልተሰጣቸው የስነ-ቃል አይነቶች ትክክለኛ መጠሪያ መስጠት ያስፈልጋል። በስነ-ቃል ላይ ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ ባለሙያዎች ለአንድ የስነ-ቃል አይነትና እሳቤ ትክክለኛውን ስያሜ በመስጠትና እንዲለመድ በማድረግ በኩል የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ይህንን ተግባራቸውን በተገቢው መንገድ ያከናውኑ ዘንድም በመጀመሪያ እስከዛሬ ለየስነ-ቃሉ አይነት መጠሪያ ሆነው የሚያገለግሉ ቃላት በህብረተሰባችን ዘንድ የተለመዱ መሆን አለመሆናቸውን ማጤን ይገባል። ለአንድ የስነ-ቃል አይነት የተሰያዩ ስያሜዎች ተሰ ጥተውት ከሆነም ለየስያሜዎቹ የቀረቡትን ምክንያቶች መመርመር ያሻል።

"በባህላዊ ጥሪትነት" ስያሜ ላልተሰጣቸው የስነ-ቃል አይነቶችና እሳቤዎች ስያሜ ሲሰጥም የስነ-ቃሉን አይነት ወይም እሳቤ ምንነት በጥንቃቄ ማጥናት አስፈላጊ ነው። ለእንዲህ አይነቱ ተግባርም ልዩ ልዩ ዘደዎችን መጠቀም ይቻላል። ለምሳሌ በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ካሉት ቃላት መካከል ፍቺዎቻቸውን በማስፋት የስነ-ቃሉ አይነት መሰ የሚያ ሊሆኑ የሚችሉበትን መንገድ መሻት አንዱ ነው። ይህ ካልሆነ የተለያዩ ቃላትን በማጣመር መሰየም ይቻላል። በአማርኛ ስያሜ ልናገኝለት ያልቻልነውን የስነ-ቃል አይነት ወይም እሳቤ በኢትዮጵያ ውስጥ ወደሚነገሩት ቋንቋዎች ፊታችንን በማዞር ስያሜ ሊሆን የሚችል ቃል እንፈልጋለን። ምናልባት የስነ-ቃሉ አይነት በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ቋንቋዎች በአንደኛቸው ያለ በአማርኛ ግን የሌለ ሊሆን ይችላልና። ለዚህም በአማርኛ ቋንቋ ስያሜ ለመስጠት የተፈለገው የስነ-ቃል አይነት ወይም እሳቤ በሁሉም ቋንቋዎች ወይም በአንደኛቸው የሚታወቅና ስያሜ ያለው መሆኑን ለይቶ ማወቅና ከዚያም በአማርኛ ለሚነገረው የስነ-ቃል አይነት መሰየሚያ እንዲሆን በማድረግ መገልገል ተገቢ ይሆናል።

በአማርኛ ቋንቋ የሌለ ነገር ግን በውጭ ቋንቋዎች (በተለይም የስነ-ቃል ጥናትና ምርምር በዳበረባቸው አገሮች) የሚታወቅ የስነ-ቃል አይነት ካለ ምን ስያሜ እንደተሰ ጠው በማጤን ወደ አማርኛ ለመመለስ መሞከር አስፈላጊ ነው። ስያሜው አለማቀፋዊ አገልግሎት እየሰጠ ያለ ከሆነ እንዳለ መዋስም ይቻላል።

ይህ ጽሁፍ ትኩረት ያደረገበት የስነ-ቃል አይነት በአማርኛ የስያሜ ችግር ያለበት መሆኑ ተመልክቷል። በይሻላል የተሰጠው ስያሜም ተጨማሪ ውይይት እንደሚያስፈልገው ጽሁፍ አቅራቢው ያምናል።

መረጃ ጽሁፎች

ሁሴን በዳሶ 1968። **ከአርሲ የተሰበሰቡ የኦሮምኛ ተረትና ምሳሌዎች።** ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

መርስዔ ኀዘን ወልደቂርቆስ 1935። **በአዲስ ስርዓት የተሰናዳ የአማርኛ ሰዋሰው።** አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

መንገሻ ገዛው 1973። **የወላይትኛ ተረትና ምሳሌዎች።** ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል፣ ለዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

መኩሪያ ወርቁ 1982። **ምሳሌያዊ አነጋገር።** አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ሙሉጌታ ሰዩም 1972። *ሰያሜና ችግሩ፡* በባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ኢንስቲትዩት የተዘጋጀ የትርጉም ሴሚናር ከግንቦት 14-16 ቀን 1972 ዓ.ም. አዲስ አበባ፤ (በስቴንስል ተባዝቶ የተጠረዘ)።

ማንተመ ሰላሴ ወልደመስቀል (ብላቴን ጌታ) 1943። **የአባቶች ቅርስ።** አዲስ አበባ፤ ነፃነት ማተሚያ ቤት።

__________ 1960። **እንቅልፍ ለምኔ።** አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

__________ 1961። **የኢትዮጵያ ጥናት ቡሌጋ።** አዲስ አበባ ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ሊሚትድ።

ሜጋ አሳታሚ ድርጅት 1991። **አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ** 8ኛ ክፍል።አዲስ አበባ ሜጋ ማተሚያ ኢወተር ፕራይዝ።

ሞገስ ዕቁባጊዮርጊስ (ሊቀመዘምራን) 1959። **የኢትዮጵያ ጥንታዊ ምሳሌ** (በአማርኛ)። አሥመራ፤ ማኀበረ ሃዋርያት ከከበጽባህ ማተሚያ ቤት።

ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው 1972 (እ.ኤ.አ)። *የባሪያ ስም በአማሪው ባህል* የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር **መጽሔት Journal of Ethiopian Studies**,vol.x,No.2,pp.127-200

ሰይፉ መታፈሪያ 1973። *ስነቃል በኢትዮጵያ፣* "ትውፊት" በሚል ርዕስ ለተዘጋጀ ሴሚናር የቀረበ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ (በስቴንስል ተባዝቶ የተጠረዘ)።

__________ 1993። *የፎክሎር መዝገበ ቃላት ጥንቀራ ቅድመ ዝግጅት፣* **የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር** መጽሄት፤ ቅጽ 26፣ ቁጥር 1፣ ገጽ 73-115።

ሳህለ ሚካኤል ወልደ ስላሴ 1953። **ለመራቀቅ ምሳሌን ማወቅ።** አዲስ አበባ፤ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

ሳሙኤል እንዳለ 1982። **ስነ-ቃል ነክ ስያሜዎች አጠቃቀምና ችግራቸው።** ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ክፍል ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፤አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ባህል ሚኒስቴር 1972። *የስነ-ቃል (ORAL LITERATURE) አገልግሎት፣* **ዜና ባህል።** ቅጽ 2፣ ቁጥር 9 ገጽ 9-11።

ተሰማ ሀብተሚካኤል ግጽው 1951። **ከሳቴ ብርሃን ተሰማ፤ የአማርኛ መዝገበ ቃላት።** አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ተክለማርያም ፋንታዩ 1964። **ጥንተ ጥበብ ዘስነ-ጽሁፍ።** አዲስ አበባ፤ ሴንትራል ማተሚያ ቤት።

ተክለጻድቅ መኩሪያ 1982። **አፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት።** አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ቤት።

ታደሰ እሸቴ 1972። የቤቶችን የበታችነት የሚያንፀባርቁ የአማርኛ አባባሎች። ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል ለቢ.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ትምህርት ሚኒስቴር 1987። *የአማርኛ መማሪያ* ዘጠነኛ ክፍል። አዲስ አበባ፤ የትምህርት *መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ* ድርጅት።

________ 1987 ። **የአማርኛ** *መማሪያ* **አስረኛ ክፍል**። አዲስ አበባ፤ የትምህርት *መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ* ድርጅት።

ትምህርትና ስነ ጥበብ ሚኒስቴር 1966። *ታሪክና ምሳሌ* ፩ኛ *መጽሐፍ*። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ. ማተሚያ ቤት።

________ 1958። *ታሪክና ምሳሌ* ፪ኛ *መጽሐፍ*። አዲስ አበባ፤ ሴንትራል ማተሚያ ቤት።

________ 1961። *ታሪክና ምሳሌ* ፫ኛ *መጽሐፍ*። አዲስ አበባ፤ ሴንትራል ማተሚያ ቤት።

አምሳሉ አክሊሉ 1980። *የሙጭ ቋንቋ ፅንሰ ሐሳብ ትርጉም በአማርኛ፣* **የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር** *መጽሔት*, Journal of Ethiopian Studies, Institute of Ethiopian Studies; Addis Ababa University: Vol.XIV (1976-79), pp-1-26.

አሰፋ ገብረማርያም ተሰማ 1976፡ *የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካደሚ አላማና ተግባር፤ ለአካደሚው የስነ-ቃል (Oral Literature) ሴሚናር የቀረበ* (ተባዝቶ የተጠረዘ)።

አሰፋው ተፈራ 1950። *መ*ከስተ ሰዋስው (የሰዋስው *መ*ልመጃ)። አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት።

አስመሮም ገብረስላሴ 1973፡ *በትግርኛ ቋንቋ የሚነገሩ ስነ-ቃሎች፤* ዜና ልሳን። ቅጽ 1፣ ቁጥር 3፤ ገጽ 23-33።

አበበ አይቼህ 1942። ቢልጮ። ግሩማዊ የሆኑ ተረቶችና ምሳሌዎች። እንዲሁም የአለቃ ገብረሀና ንግግሮች። አዲስ አበባ፤ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

________ 1948። ጉራማይሌ። ግሩማዊ የሆኑ ተረቶችና ምሳሌዎች እንዲሁም አስቂኝና አስደናቂ ንግግሮች በያይነቱ። አዲስ አበባ፤ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

አከሪክ 1987። *እንቆቅልሽ* ኩኩሉ። አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ ልዩ እትም፣ የካቲት።

አድነው ገ/መስቀል 1961። ዘይቤና ቅኔ። አዲስ አበባ፤ ተስፋ ማተሚያ ቤት።

ከበደ ሆርዶፋ 1974። *በኦሮምኛ ቋንቋ የሚነገሩ የቃል ትውፊቶች፤* ዜና ልሳን። ቅጽ 2፣ቁጥር 1፤ ገጽ 17-19።

ከበደ እንግዳሰው 1954። ነገር በምሳሌ፣ ተረትና ሳቅ፤ በመሳቅ ጨዋታ። ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት (የታተመበት ቦታ አልተጠቀሰም)።

ከበደ ደስታ 1971። ምሳሌና ተረት በእንስሳት እንደበት። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ክብረአብ አድማሱ ደጀኔ 1977። ምሳሌና መስተዋትነቱ። (በስቴንስል ተባዝቶ የተጠረዘ)።

ወርቁ ገዳ 1975። *የምሳሌያዊ አነጋገር ስብስቦች*። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ተባዝቶ የተጠረዘ)።

ውድነህ ዓለሙ 1971። ስርአትን የሚያንፀባርቁ አባባሎች። ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ክፍል፣ ለቢ.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ዓለማየሁ ሞገስ 1954። የአማርኛ ቅኔ ማስተማሪያ። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ. ማተሚያ ቤት።

ዓለማየሁ ደጉ 1975። *የጌዲኦ ተረትና ምሳሌ፣* ዜና ልሳን። ቅጽ 3፣ ቁጥር 1 ።

ዓለማየሁ ደጉና ሽንጡ ሉሌ 1973። *በጌዲኦ ቋንቋ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣* ዜና ልሳን። ቅጽ 1፣ ቁጥር 2፣ገጽ 19-21።

ዘውዴ አክሊሉ 1979። *ምሳሌያዊ አነጋገርና ግንዛቤው፣* ዜና ልሳን። ቅጽ 7፤ ቁጥር 3ገጽ 32-39።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር 1972። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፡ሴንትራል ማተሚያ ቤት።

________ 1980። *መጽሐፍ ቅዱስ።የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት።* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካደሚ 1973። *ምሳሌያዊ ንግግሮች (የቃል ትውፊት)*፣ ዜና ልሳን። ቅጽ 1፣ ቁጥር 3፣ ገጽ 21።

________ 1974። *የአፋርኛ ምሳሌዎች ከነትርጉማቸው፡* ዜና ልሳን። ቅጽ 2፣ ቁጥር 1፣ ገጽ 20-22።

________ 1982። **የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች።** አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

የክልል አስራ አራት ት/ ቢሮ 1987። ሳይንስ አምስተኛ ክፍል የተማሪ መጽሐፍ። አዲስ አበባ፤ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ።

________ 1987። **የአማርኛ መማሪያ አምስተኛ ክፍል።** አዲስ አበባ፤ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ።

ዩሱፍ አብዱረህማን (ሐጂ) 1942። **የአማርኛ ምርጥ ምሳሌና ተረት።** (የታተመበት ቦታና ማተሚያ ቤት አልተገለፀም)።

ይትባረክ እጅጉና ሳሙኤል መኻ 1974። *ለሚሱዋ (Lemisuwa) (ለሜሜር የወላይታ ተረትና ምሳሌዎች) ክፍል አንድና ሁለት።* በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል የአፃ ቋንቋዎች ጥናት ዘርፍ (በስቴንስ ተባዝቶ የተጠረዘ)።

ደስታ ተክለወልድ 1962። **አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት።** አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

________ 1928። **ገበታ ሀዋሪያ የንባብ መማሪያ።** ድሬዳዋ፤ ቅዱስ አልአዛር ማተሚያ ቤት።

ጃለታ ጃፌሮ 1956። **ተረትና ምሳሌ ።** አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ገሰሰ አርአያ 1973። **የትግርኛ ተረትና ምሳሌ።** ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ክፍል፣ ለቢ.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ገነነ ኡደሳ 1994። *ለሞር ቅኝት በጉጂ ኦሳ ስነ-ቃል፣* **አስራ አንደኛው የኢትዮጵያ ጥናት ዓለም አቀፍ ጉባዔ (Proceedings of the Eleventh International Conference of Ethiopian Studies).** Vol. II, Addis Ababa, Addis Ababa University Printing Press, pp.99-113

ጉርፉ ገብረመድኀን 1961። **በአማርኛ የሚነገሩ ጥቅሶች፣ ምሳሌዎችና ፈሊጦች።** አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ. ማተሚያ ቤት።

ገዛኸኝ ከበደ፤ 1981። **የተረትና ምሳሌዎች ገፅታ ከስድስት የአማርኛ መጻህፍት ውስጥ።** *ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍል አርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።*

ጥላሁን በየነ 1965። **ልሳን።** *አሥመራ፤* ኮከበጽባህ ዘማህበረ ሀዋርያት ማተሚያ ቤት።

ጨፋ ኡመሮ 1973። *በሃዲይኛ ቋንቋ የሚነገሩ የቃል ትውፊቶች፣* ዜና ልሳን። ቅጽ 1፣ ቁጥር 3፣ ገጽ 22-27።

ጽጌ ገብረኪዳን እሊቃ 1958። **ያለመምህር አስተማሪ።** አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ. ማተሚያ ቤት።

ፀጋዬ ተወልደብርሃን 1959። **ጣዕመ ልሳን የአነጋገር ለዛና የጨዋነት ማነጣጠሪያ።** አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ. ማተሚያ ቤት።

ፈቃደ አዘዘ 1977። *የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ስነ ቃል ጥናት ቅኝት፡ ግምገማና የስነ-ቃል ስብስቦችና ጥናቶች መዘርዝር (ቢብሊዮግራፊ)።* የሀገር ፍቅር ቴያትር 50ኛ ዓመት በዓል ሲምፖዚየም፤ አዲስ አበባ (በስቴንስል የተባዛ)።

________ 1996። *የስነ-ቃል ትምህርትና ምርምር ፋይዳ በኢትዮጵያ፡* **Ethiopian Journal of Education**; Institute of Educational Research, Addis Ababa University, Vol. XVI, No.2, pp. 54 -85

ፍቅረ ድንግል በየነ 1985። **የምሳሌያዊ ንግግሮች (ሰዋሰው ሰምና ወርቅ ሰዋሰው)።** አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

Dorson, R.M. (ed.) 1972. **Folklore and Folklife: An Introduction**. Chicago: The University of Chicago Press.

Finnegan, Ruth 1979. **Oral Literature in Africa.** Oxford: Cloredon Press.

Maria, Leach (ed.) 1949. **Funk & Wagnalls Standard Dictionary of Folklore Mythology and Legend.** New York: Funk and Wagnalls Company.

ጋዜጦች

መስፍን ሀብተማርያም፣ "አንድ ቀን"፣ አዲስ ዘመን። 54ኛ ዓመት፣ ቁጥር 71፣ ኅዳር 23 ቀን 1986።

______፣ "አንድ ቀን"፣ አዲስ ዘመን። 54ኛ ዓመት፣ ቁጥር 83፣ ታኅሳስ 7 ቀን 1986።

የጸሃፊው ስም አልተገለጸም፣ "ላም ባለዋለበት ኩበት ለቀማ?"፣ አዲስ ዘመን። 55ኛ ዓመት፣ ቁጥር 198፣ ታኅሳስ 9 ቀን 1988።

ሚሊዮን ከበደ፣ "ቅምሻ"፣ የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ። 41ኛ ዓመት፣ ቁጥር 13፣ ሚያዝያ 30 ቀን 1985።

ሮዚና እንድሪስ፣ "ቅምሻ"፣ የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ። 43ኛ ዓመት፣ ቁጥር 52፣ ጥር 25 ቀን 1988።

ስመኝ ግዛው፣ "ቅምሻ"፣ የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ። 41ኛ ዓመት፣ ቁጥር 47፣ ታኅሳስ 23 ቀን 1986።

አ ባ ሪ

አንድ ሰው የስነ-ቃሉን አይነት ለመጥራት የተጠቀመባቸው ስያሜዎች ከተገለጋዩ ስምና ስራ ጋር ተመልክቷል። ከየስያሜዎቹ ፊት ለፊት የሰፈሩት ቁጥሮች በተጠቀሰው ስራ ውስጥ የሚገኙበትን ገፅ ያመለክታሉ። ቁጥሮቹ ለአብነት ያህል የተጠቀሱ በመሆናቸው የየሰዎቹን የስያሜ አጠቃቀም የበለጠ ለመረዳት ፅሁፎቹን ማንበብ ያስፈልጋል።

ሁሴን በዳሶ 1968። በአርሲ የተሰበሰቡ የኦሮምኛ ተረትና ምሳሌዎች።

ምሳሌያዊ አነጋገር (ርዕሱን የመረጥኩበት ምክንያት)	
ተረትና ምሳሌ	8
ተረት	9
ምሳሌ	10
አባባል	16

መርስዔ ኀዘን ወልደቂርቆስ 1935። በአዲስ ስርአት የተሰናዳ የአማርኛ ሰዋስው።

ምሳሌ/ተረት	221
ምሳሌ	221

መስፍን ሀብተማርያም 1986። *አንድ ቀን* አዲስ ዘመን፤ 54ኛ አመት ቁጥር 71ና 83።

ምሳሌያዊ አነጋገር	3
ምሳሌያዊ አባባል	3
አባባል	3

መኩሪያ ወርቁ 1982፤ **ምሳሌያዊ አነጋገር**።

ምሳሌያዊ አነጋገር	6
ምሳሌ	6
ተረትና ምሳሌ	7
ምሳሌያዊ ንግግር	13

ማኅተመሥላሴ ወልደመስቀል (ብላቴን ጌታ) 1945። **የአባቶች ቅርስ**።

ምሳሌ	4	የምሳሌ ንግግር	4
ተረት	4	ተረቶች/ ምሳሌዎች	5
ምሳሌና ተረት	4		

ሞገስ ዕቁባ ጊዮርጊስ (ሊቀመዘምራን) 1959፤ **የኢትዮጵያ ጥንታዊ ምሳሌ**። (በአማርኛ)፤

ጥንታዊ ምሳሌ	(ገጽ፣ ምክንያት)
ምሳሌና ተረት	(ገጽ፣ ምክንያት)
ምሳሌ	(ገጽ፣ ምክንያት)

ተክለማርያም ፋንታዬ 1964፤ ጥኀተ ጥበብ ዘስነ-ጽሁፍ።

ተረትና ምሳሌ	123
ተረት	126

ታደሰ እሸቴ 1972። *የሴቶችን የበታችነት የሚያንፀባርቁ የአማርኛ አባባሎች*።

አባባል	22	ተረት	25
ተረትና ምሳሌ	20	ምሳሌያዊ አነጋገር	25

ክብረአብ አድማሱ 1977። *ምሳሌና መስታዋትነቱ*።

ምሳሌ	14
ምሳሌያዊ አነጋገር	29

ውድነህ ዓለሙ 1971። *ሥርዓትን የሚያንፀባርቁ አባባሎች*።

አባባል	9
ተረትና ምሳሌ	4

ገሠሠ አርአያ 1971፤ *የትግርኛ ተረትና ምሳሌ*።

ተረትና ምሳሌ	3
ምሳሌ	3
ምሳሌያዊ አነጋገር	3

ፈቃደ አዘዘ 1977፤ **የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ጥናት ቅኝቶች ግምገማና የሰነ-ቃል ስብስቦችና ጥናቶች መዘርዝር**።

ተረት	27
ተረትና ምሳሌ	72
አፈታሪክ	82

__________ 1996። **የሥነ-ቃል ትምህርትና ምርምር ፋይዳ በኢትዮጵያ።**

ምሳሌያዊ አነጋገር	55
ምሳሌያዊ ንግግር	55
ንግግር	59

ፍቅረ ድንገል በየነ 1985። **የምሳሌያዊ ንግግሮች ሰዋስው (ሰምና ወርቅ ሰዋስው)።**

ተረትና ምሳሌ	5
ምሳሌ እና ተረት	6
ምሳሌያዊ ንግግር	7
ምሳሌ	7

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ በተለያዩ ጊዜያት በ"ዜና-ልሳን" መጽሄት ላይ የወጡ መጣጥፎች ለስነ-ቃሉ አይነት የሰጡት ስያሜ

አስመሮም ገብረስላሴ 1973። ኪነ-ቃል 28

ከበደ ሆርዶፋ 1974። የቃል ትውፊት 17

ዓለማየሁ ደጉ 1975። ተረትና ምሳሌ 42

ዓለማየሁ ደጉና ሽንጡ ሱሌ 1973። ምሳሌያዊ ንግግር 18

ዘውዱ አክሊሉ 1979። ምሳሌያዊ አነጋገር 32

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ 1973።

ምሳሌያዊ ንግግር (የቃል ትውፊት) 21

ምሳሌ 21

የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት

ትምህርት ሚኒስቴር 1987። **የአማርኛ መማሪያ አሰረኛ ክፍል።**
ተረትና ምሳሌዎች 31

የክልል 14 መስተዳድር ትምህርት ቢሮ 1987። **የአማርኛ መማሪያ አምስተኛ ክፍል።**

ምሳሌያዊ ንግግሮች 55

አኙዋዎችና[1] ትረካዎቻቸዉ

ባይለየኝ ማሰዉ

መግቢያ

ስነቃል መንፈሳዊ ቅርስ ነው። እምነትንና ልማድን ከዘመኑ አስተሳሰብና የአኗኗር ስልት ጋር አቆራኝቶ ያሳያል፤ ርዕዮተ ዓለምን፥ ታሪክን፥ ባህላዊ እሴትን፥ ስነምግባርን፡ እውቀትንና ጥበብን ያመለክታል። የአንድን ህዝብ ማንነት፥ ማህበራዊ ግንኙነትንና ደንቦችን ብቻ ሳይሆን ስሜትን ከምክንያት ይገልፃል፥ የፍትህና ርትዕ መሰረቶችንም ይነግራል።

ስነቃል ማህበራዊና ባህላዊ ገጽታ ነው። በአንድ ሀብረተሰብ ውስጥ በእውን የሚከናወነውን ወይም ሊከናወን የሚችለውን ድርጊት በተረቶቹ ውስጥም ሲከናወን እናገኛለን፤ በእውነተኛው ማህበራዊ ግንኙነት እንደሚታየው ሁሉ በትረካዎች ውስጥም ባለታሪኮቹ የሚከተሉት መርህ፡ እምነትና ርዕዮተ-ዓለም፥ የሚግባቡበት ቋንቋና የወል ስሜት (common sense)፥ የሚገዙበት ህግ፥ ደንብና ስርዓት፥ የሚለዩበት የግል ፍላጎትና ምኞት... ይንጸባረቃል።

ስነቃል በግንኙነት ስልትነቱ ምሳሌያዊ ነው፤ ከማንኛውም ማህበራዊ እንቅስቃሴ በስተጀርባ የስነቃል ኃይል አለና። በመሆኑም አጠቃላዩን ማህበራዊ እንቅስቃሴ በስነቃል ቅርጾች በሚተላለፉ መልዕክቶችና ታሪኮች አማካይነት መረዳት ያሻል (Peacock, 1969: 172)። አንድን ማህበረሰብ ለማወቅ ስነቃሉን መመርመር አስፈላጊ የሚሆነዉ ስነቃል የሰው ልጅ ካካበተው ልምድ፥ ከተፈጥሮ ጋር በሚያደርገው ያልተቋረጠ ትግል፥ እርስ በእርሱ ከሚፈጥረው ግንኙነት፥ ግጭት፥ ጦርነት፥ ከቦታ ቦታ ከሚያደርገው ዝዉዉርና ፍልሰት፥ ስለ ዓለም አመጣጥ ወይም አፈጣጠር ከሚሰጠው አስተያየት፥ ከስርዓትና ከማህበራዊ ደህንነት ጋር

---

[1] አኙዋዎች ራሳቸውን "አኙዋ" ብለው ነው የሚጠሩት። "አኙዋክ" የሚለውን ቃል እንደቤተኛ ሳይሆን የሚመለከቱት እንደባዕድ ቃል ነው። ለዚህም ቻም አዶም "ትክክለኛ ስያሜያችን 'አኙዋ' ሆኖ ሳለ ባዕዳን 'አኙዋክ' እያሉ ይጽፋሉ ወይም ይናገራሉ" በማለት ገልጸው ስለቃሉ አመጣጥና አጠቃቀም ቀጥለው ሲያስረዱ "አኙዋ"፡ "ኙዋ" ከሚለው ስረወ ቃል የተገኘ ነው። "ኙዋ" ማለት "አብሮ መብላት፥ ያለውን ነገር ተካፍሎ መጠቀም ፡ ተጋርቶ መኖር" ማለት ነው (ቻም አዶም፡ 1996፡ 3)። ከቻም አዶም አገላለጽ እንደምንረዳው 'አኙዋክ' የሚለው ቃል ህዘቡ በሚረዳው መንፈስ የጋራ ህይወቱንና ማንነቱን አይጠቅስም። "አኙዋ" የሚለው ቃል "ኙዋ" ከሚለው መሰረታዊ ቃል መገኘቱን ፔትሮር (1990) ባዘጋጁት አኙዋ-እንግሊዝኛ መዝገበ ቃል ውስጥም እንደዚሁ ሰፍሮ ይገኛል። ሁለቱም ጸሀፊዎች እንዳስረዱት ሁሉ በትረካዎች ውስጥም"አኙዋክ" ሳይሆን "አኙዋ" ወይም "አኙዌ" በሚል ቃል ተጠቅሶ እናገኛለን። "አኙዋ" ነጠላ ቁጥር ሲሆን አንድን የአኙዋ ተወላጅ ወይም ብሄረሰቡን በአጠቃላይ ያመለክታል። "አኙዌ" ሲሆን ደግሞ "አኙዋዎች" ማለት ነው። ስለዚህ ይህ ጥናት "አኙዋክ" በሚለው ፈንታ "አኙዋ" የሚለውን ቃል ተጠቅሞበታል።

በእጅጉ የተሳሰረ በመሆኑ ነው (Courlander, 1977: 1-7)። ከዚህ አንጻር ፎክሎርን የማጥናቱ አስፈላጊነት ጉልህ ቢሆንም ከራሳችን ሁኔታ ተነስተን ስንመለከተው ገና ጥረት አልተጀመረም ማለቱ ይቀላል። ስነቃሎች በየቋንቋው አልተሰበሰቡም፣ አልተጠኑም፣ አልተመደቡም።

ይህ ጥናት ከናይሎ ሰሀራ የተለያዩ ብሄረሰቦች መካከል አንዱ በሆነው በአኙዋ ህብረተሰብ ትረካዎች ይዘትና ሚና ላይ ያተኩራል። ትረካዎችን እንደ አንድ የባህል ገጽታ በሚኖሩበት ባህላዊና ማህበራዊ አውድ ውስጥ ይዘታቸውንና አገልግሎታቸውን በመመርመር ከህብረተሰቡ መዋቅራዊ አደረጃጀት አንጻር ይተነትናል። በመሆኑም ስለትረካዎች ይዘትና ሚና ከመናገራችን በፊት አኙዋዎችና ባህላቸዉ ምን ይመስላል? የሚለውን በቅድሚያ መመልከት አስፈላጊ ይሆናል።

1 አኙዋዎችና ባህላቸው

አኙዋዎች በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በጋምቤላ ቆላማ፣ ሞቃትና በርሃማ፣ ነገር ግን ለም በሆነ ስፍራ ላይ ይኖራሉ። መንደሮች በጋ ተክረምት ሳይነጥፉ በሚፈስሱ አራት ትልልቅ ወንዞች (ባሮ፣አልዌሮ፣ጊሎና አኮቦ) ግራና ቀኝ ዳርቻዎች የተቆረቆሩ ናቸዉ። የአኙዋዎች ዋነኛ የኑሮ መሰረት እርሻ ነው። እርሻውም በእጅ፣በዶማና በሹል እንጨት የሚቆፈር ሲሆን በዓሳ ማስገርና በአደን ጥቅማጥቅም ይደገፋል። የአኙዋዎች ተወዳጅ ምግብ ገንፎ ሲሆን፣ ዋና ዋና ሰብሎቻቸው ደግሞ በቆሎና ማሽላ ናቸው። ማጣፈጫ ጨውም ከተለያዩ የዕጽዋት ዓይነቶች ይቀምማሉ።

አኙዎዎች በአንድ ፈጣሪ ኃይል ያምናሉ። እሱም "ጆክ" (Jwok)ይባላል። "ጆክ" ክልኤ ተቃርኖ ባህርያት አሉት። አንድም ሁለትም ነው። በአንድነቱ ዓለምን ፈጥሮ በሰማይ ይኖራል። በሁለትነቱ የሰራውን ያፈርሳል፤ ይሽራል። በፈጣሪነት ባህርይው "ጆክ–ኚንጋላ-ብዎ" ተብሎ ይጠራል። በአፍራሽ ባህርይው ደግሞ "ጆክ-ዱጉ-ኚንጋላ-ብዎ" በሚል ይታወቃል። "ጆክ" ክልኤ ተቃርኖ ባህርያቱን የሚፈፅሙ አገልጋይ መናፍስት በምድር ላይ እንዳሉት አኙዋዎች ያምናሉ። መናፍስቱም በቸርነት ወይም በጭካኔ የተሞሉ በመሆናቸው እንደባህርያቸው ለሰዎች ክፉም ደግም ነገር ይፈጽማሉ። ሁለቱ ተቃራኒ የ"ጆክ" መናፍስት በአገልጋይነት በምድር ላይ መገኘት ብቻ ሳይሆን ሰዎችን በዖታ ሳይለዩ "ያገኟቸዋል" ተብሎ ይታመናል። የፈጣሪ፣ የቸርነት፤ የመሃሪነትና የዘላለማዊነት ባህርይ ያለው የ"ጆክ" አንዱ ገጽታ ያደረባቸው (የተጋባቸው) ሰዎች የተመረጡ ወይም የተመረቁ ቅዱሳን ናቸው። በተቃራኒው ደግሞ የ"ጆክ" አፍራሽ ኃይል ያደረባቸው ሰዎች "የጥፋት" ወኪሎች ተደርገው ይታያሉ። እነዚህም "ቺ-ጆክ" (ci-jwok) ተብለው ይጠራሉ። ይህ ማለትም "የጆክ-ዱጉ-ኚንጋላ-ብዎ ሚስት" እንደ ማለት ሲሆን የህመም፣ የደዌ፣ የሞት፣ የመቅሰፍት፣ የውሽት፣ የወንጀል፣ የግድያ፣ የጥልና የጭቅጭቅ፣ የሀዘን፣ የስቃይና የመከራ፣... ምንጮች ተደርገው ይቆጠራሉ።

አኙዋዎች በአባቶቻቸው መናፍስትም (ancestral souls) ያምናሉ። ለመናፍስቱ መስመኛ መስዋዕት ያቀርባሉ። ከመናፍስቱ ጋር በህልም ይገናኛሉ። ይህ ብቻ አይደለም- አኙዋዎች በ"አኒሚዝም"[2] ና በ"ቶተሚዝም"[3] ያምናሉ። በአኙዋዎች እምነት የንጋሲ፥ የባላባት ዘር፥ "ወደውሃ ተመለሰ" እንጂ "ሞተ" አይባልም። "ሞተ" የሚባለው ዝቅተኛው የህብረተሰብ አባል (የንጋሲነት ዘር የሌለው) "ዋቶንግ" (watong)፥ ጆይ (jey) ወይም የንጋሲ ዘር ሆኖ የህብረተሰብን ስነምግባር በመጣስ በአደባባይ "ውርደት"ን የተቀበለ ሰው ነው። "ህይወት ወደ ውሃ ተመልሳ ትኖራለች። በመሆኑም ውሃ የላይኛው ሰማያዊ አካል ቅጥያ ተደርጎ ነው በአኙዋዎቹ ዘንድ የሚታመነው። ውሃ የህይወትና የምርት መሰረት እንዲሁም የፍትህ፥ የስርዓትና የህግ ምንጭ ነው።

አኙዋዎች ብዙ ሴቶችን የማግባት የቆየ ልማድ አላቸው። በምሳሌያዊ አነጋገር እንደሚገልፁት "አንድ ሚስት ያለው ላጤ ነው።"- ካገባ አይቆጠርምና። ለአንድ አኙዋ (ሀብት እስካለው ድረስ) የሚስት ቁጥር ወሰን የለውም። ሀብቱም በ"ዲሙይ" ይተመናል። "ዲሙይ" ውድ የሆነ የጨሌ ዓይነት ነው። የቃል ትረካዎች እንደሚያመለክቱት ለጥንታዊ አኙዋዎች ስደትና በተለይም የምስራቅ አፍሪቃ አገሮች መበታተን አንዱ ዋነኛ መንስኤ "ዲሙይ" ነው። በመሆኑም "አኙዋዎች የጨሌ አፍቃሪዎች" ተብለው ይጠቀሳሉ (ባህሩ ዘውዴ፥ 1976፤ 12)። አንድ አኙዋ ሚስት ለማግባት "ዲሙይ" ለወላጆቿ መክፈል አለበት። "ዲሙይ" ዛሬም እንደገንዘብ ያገለግላል። በቆየው ልማዳዊ አሰራርና እምነት መሰረት ጨሌ የስልጣን፥ የአንድነት፥ የሉዓላዊነት፥ የማንነት ተምሳሌት (Symbol) ነው (Evans-Pritchard, 1941:56-57)።

በአኙዋዎች ልማድ ዕድሜ ከፍተኛ ሚናና ቦታ አለው። ማስወገድ (Rejection) ወይም መቀበል (Incorporation) የወሲድ ቅጽበትን ተከትሎ በርጥብ ጨቅላ ላይ የሚከናወን ወሳኝ የምርጫ ሥርዓት የአኙዋዎች ልማድ ነው። ከአሥር እስከ አሥራ ሁለት አመት ዕድሜ ያላቸው ልጆች ስድስቱን የታች የፊት ጥርሶች በጉጠት መውለቅ አለባቸው። ይህም የራሱ

2

"አኒሚዝም" በአማርኛ "አረማዊነት" የሚል ስያሜ የተሰጠው ይመስላል። "አኒሚዝም" አንድ የዕምነት መስመር ሲሆን ሁለት ገጽታዎች ይዞ ይገኛል። አንደኛው መልኩ ነፍስ ከሥጋ ተለይታ በህይወት መቀጠል እንደምትችል ማመን ሲሆን ሁለተኛው ገጽታ ደግሞ ከመናፍስት (Spirits) ጋር የተቆራኘ እምነት መከተል ነው። በአማኞቹ ዘንድ መናፍስቱ ከፈጣሪ ቀጥሎ በተዋረድ የተሰየየ ደረጃና ክብር ይሰጣቸዋል፤ መስዋዕት ይቀርብላቸዋል። ከነዚህ የዕምነት ገፅታዎች ጋር በተያያዘ የአኒሚዝም አማኞች አምልኮና ሥርዓት ከዋኙ ያካሂዳሉ (ታይለር፥ 1876፥ 426-427)።

3

"ቶተሚዝም" አንድ የእምነት መስመር ሲሆን ከሶስት ገፅታዎች ማለትም ከማህበራዊ፥ ከስነልቦናዊና ከክዋኔ ስርአት(ritual) አኳያ ተከፋሎ ይተነተናል። በማህበራዊ ገፅታው ቶተሚዝም አንድ የህብረተሰብ ክፍል ወይም ወገን ከእንስሳት ወይም ከእፅዋት ዝርያዎች ወይም ከግኡዛን ፍጥረቶች ጋር መስርቶት በቆየው ግንኙነት ይገለፃል። በስነልቦናዊ ገፅታው ደግሞ የህብረተሰቡ አባላት ከእንስሳት ወይም ከእፅዋት ወይም ከግኡዛን ፍጥረቶች ጋር የስጋ ዝምድና እንዳላቸው አምነው የዘር ሃረግ መነሻ አድርገው በመውሰዳቸው ይገለፃል። ሶስተኛው የቶተሚዝም መገለጫ የክዋኔ ስርአት ነው። ይኸውም አማኞች "ቶተም" ሆነው ለተወሰዱት እንስሳት፥ ወይም እፅዋትም ሆነ ግኡዛን ፍጥረታት አክብሮት ይኖራቸዋል፤ እንስሳቱንም ሆነ እፅዋቱን ከመብላት ይቆጠባሉ (Levi-Strauss, 1968: 8 - 9)።

የሆነ ማህበራዊ ግብ አለው። አንዱ ስቃይን መቻል ሲሆን ሁለተኛው የአኙዋነት መለያ ነው። ከዚህም በላይ ጥርስ ማውለቅ "ውበት" ነው። ወጣቶች በ"ጆቢራነት" የሚታቀፉትም ከአስራ ስምንት እስከ ሃያ አምስት ባለው የእድሜ ዘመናቸው ሲሆን ይህ የሚከናወነው በትግል፣ በኃይል፣ በድብድብና ውድድር ይሆናል። "ጆቢራ"፣ "ዘብ" ማለት ሲሆን ዘብነቱም ወንዙን፣ አገሩን፣ ወገኑን ከወራሪ ለመጠበቅ ይሆናል። "ጆቢራነት" በመንፈስም በአካልም ለኃላፊነት ብቁ የመሆንን ማህበራዊ ቦታ ያመላክታል፤ ሃላፊነቱም እስከ አርባ ዓመት የእድሜ ደረጃ ይቀጥላል። አንድ አኙዋ ከጆቢራነት ሲገለል የ"ጆ-ዶንጎ" (የሀገር ሽማግሌነት) ቦታ ይይዛል። በአኙዋ ማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ "ጆ ዶንጎ" ከፍተኛ ሚና አለው። እንዲያውም የማህበራዊ መዋቅሩ የጀርባ አጥንት "ጆ-ደንጎ" ነው ሊባል ይችላል፤ ምክንያቱም ማንኛውም ቅራኔ መፍትሄ ሊያገኝ የሚችለው በ"ጆ-ደንጎ" ውሳኔ ነውና። የ"ጆ-ደንጎ" ውሳኔ ሳያርፍበት ኘያ(ንጉሥ) ወይም ኳሮ (የአገሩ አለቃ) ጣልቃ እንዳይገባ ባህሉ ያግዳል። በአኙዋዎች ልማዳዊ ህግም (በክዎር) መሰረት "ጆ ደንጎ" የጠቡን፣ የወንጀሉንና፣ የክርክሩን መነሻ አመሳክሮ ውሳኔ ሰጥቶ ሳያሳውቅ "ኘያው" ወይም "ኳሮው" ስልጣኑን ተመክቶ በማንኛውም ጉዳይ ጣልቃ ቢገባ "አጌም" (ተቃውሞ፣አመፅ) ሊያስነሳና በሰበቡ ከስልጣን ሊወገድ፣ አገር ለቆ ሊሰደድ፣ ሀብት ንብረቱን ሊወረስ ወይም ሊገረፍና ሊገደል ይችላል። ይህንንም ኢቨንስ-ፕሪቻርድ (1941:40) "ውሻውን ጅራቱ ያንቀሳቅሰዋል" ሲሉ በዘይቤ አስቀምጠውታል። "ውሻው" ኘያንና ኳሮን ሲያመለክት "ጅራቱ" ደግሞ የህዝብ አመጽ "አጌም" መሆኑ ነው (ቻም አዶም፣1996:7)።

"አኙዋነት" ተጋርቶ መኖር ማለት ሲሆን፣ ይህ የአኙዋነት የማንነት መገለጫም ባህላዊና ማህበራዊ ተቋም መስርቶ በሰፊው ሲሰራበት የቆየ ይመስላል። ተቋሙም "ዊ-ማች" ይባላል። "ዊ" (Wii) "ትልቅ ሰው" እንደማለት ሲሆን "ማች" (Maac) ደግሞ " እሳት" ማለት ነው። "ዊ-ማች" በቁሙ "ትላልቅ ሰዎች በእሳት ዙሪያ" የሚለውን ፍች ያስገኛል። ውጫዊ ትርጉሙ ይህን ቢመስልም ሚስጢሩ ጥልቀት እንዳለው መገንዘብ ይቻላል። ይኸውም በእያንዳንዱ የአኙዋ መንደር ከልጂቅ እስከ ደቂቅ ከዐሀይ ግባት በኋላ በእሳት ዙሪያ ተገናኝቶ የውሎ ገጠመኙን የሚካፈልበት፣ የሚጠያየቅበት፣ ሀሳብ ለሀሳብ የሚለዋወጥበት፣ችግሩን የሚገልጽበት፣ ወይም የሚፈታበት ነው። "ዊ-ማች" የሀሳብ መለዋወጫ መድረክ ብቻ አይደለም። በባህሉ መሰረት ያለአንዳች ችግር ወደ "ዊ-ማች" መምጣት ሳይሳነው በጤናው ራሱን አግልሎ ብቻውን የሚበላ አኙዋ "ች-ጆክ" ወይም የ "ጆክ ሚስት" መሆን አሰበት ተብሎ ይታመናል፣ በእምነቱ መሠረት ይህ ሰው ለህብረተሰቡ ፀር ነው፣ መወገድ ይኖርበታል። ለአኙዋዎች በ"ዊ-ማች" ዙሪያ መገኘት ግዴታም ውዴታም ነው። ቤት ያፈራው ምግብና መጠጥ ወደ "ዊ-ማች" ይቀርባል። ይበላል። ይጠጣል። ከዚያም ይጨፈራል። ይዘፈናል። በቀርም በእሳት ወይም በጨረቃ ብርሃን ተረት ይነገራል። ይህ የአኙዋዎች ዘወትራዊ የህይወት ገጽታ ብቻ አይደለም የጋራ ኑሮ ፍልስፍና ተግባራዊ መገለጫ ጭምር እንጂ፤ በመሆኑም አንድ አኙዋ ሰብዕናው የሚታነጽበት፣ ክፋውን ከደግ የሚለይበት፣ ያባቶች ውጣ ውረድ የተሞላበት የጀግንነት ታሪክ፣ እምነት፣ ልምድና እውቀት በስነቃል አማካይነት

በሰፊው የሚዘከርበት ባህላዊ ትምህርት ቤት ነው "ዊ-ማች"!

1.1 የአኙዋ ተረቶች

አኙዋ ሶስት ዋና ዋና የተረት ዓይነቶች (genres) አሉት። እነዚህም "ሌሮ"፥ "ዋች" እና "አንጋዶ" በሚል ይታወቃሉ።

1.1.1 ሌሮ

"ሌሮ" ሁለት ፍቺዎች አሉት። አንዱ "ኮከብ" ማለት ነው። "ሌሮ" ነጠላ ቁጥር[1] ሲሆን "ሊሬ" ደግሞ ብዙ ቁጥርን በማመልከት "ከዋክብት" የሚል ትርጉም ይሰጣል። (ፊሊፕ አፒየው፥ ቃለመጠየቅ፥ ጥር 25 ቀን፥ 1990፥ ጋምቤላ)። ከዋክብት በጨለማ ይነግሳሉ። ደምቀው ይዋባሉ። አኙዋዎች ሰማያዊውን ብርሃን ከምድራዊው ህይወት ጋር በማቆራኘት ለከዋክብት የሰጡትን ስያሜ ለተወሰኑ የተረት ዓይነቶች ጥቅል መጠሪያ አድርገውት እናገኛለን። በመሆኑም "ሊሬ"፥ "ታሪክ"፥ "የአባቶች ጥንታዊ ህግ፥ሥርዓት፥ ወግ"፤ ወይም "ከአባቶች ሲወርድ ሲዋረድ ለዘመኑ ትውልድ በቃል የተላለፈ፥ የደረሰ ጥበብ፥ እውቀት፥ እውነተኛ የታሪክ ጨዋታ" የሚለውን ሁለተኛውን ፍቺ ይዟል።[4]

በአኙዋዎች አመለካከትና እምነት ሰማያዊውም ሆነ ምድራዊው ዓለም ከእምህበ አልቦ (ex-nihilo) የተዘረጋ አይደለም። በሰማያዊውም ሆነ በምድራዊ ዓለም ላይ የሚገኘው ግዑዝና ህያው ፍጥረት ሁሉ የአንድ ሰማያዊ ኃይል ሥራ ነው። ይህ ሰማያዊ ኃይልም ከላይ እንደተገለፀው "ጆክ" (Jwok) ይባላል። የጆክ ተቃራኒ ኃይሎችን ፍላጎት በምድራዊው ዓለም ላይ እየፈፀሙ የሚኖሩ መናፍስት (spirits) በፍጥረተ ግዑዛንና ህያዋን፥ በተራሮች፥ በወንዞች፥ በሀይቆች፥ በቋጥኞች፥ በሙቅና በቀዝቃዛ ምንጮች (ጠበሎች)፥ በዋሻዎች፥ በደኖች፥ እንዲሁም በዘንዶ፥ በግዙፍና በአደገኛ አራዊትና እንስሳት፥ በጠንቋዮች በንጉሦችና በሌሎች ፍጡራን ላይ ሰፍረው ይኖራሉ ተብሎ ይታመናል። ይህ የስነፍጥረት እምነትና አመለካከትም ከአባት ወደ ልጅ፥ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ቆይቷል። እየተላለፈም ይገኛል። በአኙዋ ህብረተሰብ ውስጥ የአባቶችን ጥበብ፥ እውቀት፥ ጀግንነት ፍልስፍናና እምነት የማስተላለፊያ መንገድም "ሌሬ" ሆኖ እናገኛለን። "ዓለም እንዴት ተፈጠረ?"፥ "የሰው ልጅ በምድር ላይ እንዴት መጣ?" የሚለውን ሁለንተናዊ የስነፍጥረት ጥያቄ መልስ ለመስጠት የሚሞክረው "መንትዮች"፥ የተሰኘው "ሌሮ" ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ ይሆናል። ትረካውም እንደሚከተለው ቀርቧል።

---

4 ኝግዎ ዳራ፤ እድሜ 87፤ ቻዎ አኳይ፥ እድሜ 58፥ ቄስ አኳይ አሹዶ፥ እድሜ 69፥ በጋምቤላ ከተማ ከተካሄደ ውይይት፥ ጥር 30 ቀን፥ 1990 ዓ.ም።

በጥንት ዘመን ሰው በምድር ላይ አልነበረም:: ጆክ ከሰው በፊት የፈጠረው ሰማይና ምድርን፣ አራዊትንና እንስሳትን፣ አዕዋትንና ውሃን ነበር:: ከእነዚህ ፍጥረቶች በኋላ ጆክ ሰው የሚባል ከዱር አራዊት ከአንበሳ፣ ከዝሆን፣ ከነብር፣ ከቀጭኔ፣ ከአእዋፍና ከሌሎች እንስሶች ሁሉ የተሻለ፣ ያማረ ፍጡር ሊፈጥር አሰበ:: ጆክ ሰውን ሲፈጥር ሴት ወንድ እንዲሆኑ አድርጎ ነው:: በመሆኑም ጆክ እንዳሰበው መንታ (ሴትና ወንድ) ሰዎችን ፈጠረ:: ከፈጠራቸው በኋላ ግን በስራው ተናደደ:: የተናደደበት ምክንያትም እንዳሰበው ያማሩና የተዋቡ ስላልሆኑለት ነበር:: ሰርቶ ሲያያቸው አስቀያሚዎች ሆኑና አስጠሉት::

ኋላም "እኔ ለመፍጠር የፈለግሁት እንደዚህ ያሉ አስቀያሚዎችን አልነበረም:: ከሁሉም ፍጥረቶች ሁሉ የባሱ ብልሹ ናቸው:: ስለዚህ እነዚህን ውሃ ውስጥ ወርውሬ ሌላ ያማሩ መንታ ሴትና ወንድ ሰዎችን እንደገና መስራት አለብኝ" በማለት ወሰነ:: ጆክ ይህን በመወሰንና በስራው ብልሹነት በመናደድ ላይ እንደነበረ ውሻ ሰምታ ነበር::

ውሻም "ለምን መጀመሪያ ይፈጥራቸዋል? ሲፈጥራቸውስ ለምን አሳምሮ አልሰራቸውም ነበር? ምን አጠፉ? ያጠፉት ሳይኖር እንዴት ወደ ውሃ ሊወረውራቸው ይወስናል?" አለችና፣ ጆክ ሳያይ መንትዮቹን ሰርቃ ከሰማይ አውርዳ፣ ከትልቅ ዛፍ ጉሬ ውስጥ ደበቀቻቸው:: ከዚያም አራዊት በልተው የሚያተርፉትን ሥጋ እያመጣች በመመገብ አሳደገቻቸው::

ጆክም እንደወሰነው መንትዮቹን ወደ ውሃ ሊጥላቸው ቢፈልግ አጣቸው:: በዚህ ጊዜ ውሻ ወደ ምድር እንደ ወሰደቻቸው አወቀ:: በድርጊቷም በጣም ተናደደ:: "ይች ሌባ ሰስደቻቸዋለች! እንዴት እነዚያን አስቀያሚ ነገሮች በጥሩ ሁኔታ ከሰራሁዋቸው ፍጥረቶቼ ጋር ወስዳ ትቀላቅላቸዋለች?" አለና የባሰ ተናደደ:: በምድር ላይ ያለው ህይወት እንዳይጠፋ፣ እንዳይሞት፣ የሚጠብቅበትን በእጁ ይዞት የሚኖረውን "ኪሲ-ጉር" ወደ ውሃ በብስጭት ወረወረው:: በምድር ላይ የሚኖረው ህይወት እንዲደመሰስ- ለዘለዓለም እንዲጠፋ! ውሻም አብራ እንድትጠፋ::

ውሻ ግን "ኪሲ-ጉር" ከሰማይ ተወርውሮ ከውሃው ውስጥ ሊገባ ሲል አየችው:: ወዲያው ፈጥና በአፏ ቀለበችውና ከውሃ በማራቅ ከደረቅ መሬት ደብቃ አስቀመጠችው:: "ኪሲ-ጉር"ም ከውሃ ውስጥ ሳይገባ ቀረ:: በምድር ላይ ያለው እንስሳ፣ አራዊት፣ አዕዋፍና ሰውም ሳይጠፉ መኖር ቻሉ::[5]

ስለ መንትዮች የሚተርከው ይህ ሌሮ የአኙዋ "ዘፍጥረት" (Genesis) ሊባል ይችላል:: "ሚት" (Myth) በዓለማችንና በሰው ልጅ እጣ ላይ ተዕሰኖ እየሳረፈ ሲቀጥል የቆየ በእውን የተፈፀመ ድርጊት ነው ተብሎ የሚታመን ታሪክ ነው:: እንድ የክርስትና ሃይማኖት አማኝ ስለ ዘፍጥረት፣ ስለ ጥፋት፣ በክርስቶስ ስቅለትና መስዋዕትነት የሰው ልጅ መድህን ስለ ማግኘቱ በመጽሀፍ ቅዱስ ታሪኮች እንደሚያምን ሁሉ ሚትም በጥንታዊ ሰው ሃን ያህል ዋጋ አለው (Malinowski, 1926:18):: ጆክ በመጀመሪያ ዓለምን (ሰማይና ምድርን)፣ ቀጥሎም አዕዋትንና እንስሳትን፣ ከዚያም የሰውን ልጅ መፍጠሩን ሌሮው ያስረዳል:: ሴትና ወንድ መንትዮችም አዳምና ሄዋንን ያስታውሳሉ:: ከታሪኩ መገንዘብ እንደሚቻለው ጆክ ኃያል ነው- ፈጣሪ ነውና! ግን "ፍጹም" ሆኖ አይገኝም:: ምክንያቱም እንደተመኘው አሟልቶና አሰውቦ

5

ተራኪ አጊዮው ኡቶው፣ እድሜ 56፣ ጋምቤላ፣ 1990

የሰውን ልጅ ሊፈጥር አልቻለም:: በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሄር አዳምንና ሄዋንን እንደ ፈጠረ በእባብ አሳሳችነትም እርግማን ላይ ወደቁ (ዘፍጥረት:ምዕ.1:13-14):: የጆክ አዳምና ሄዋን፥ መንቶች፥ ግን የፈጣሪያቸው ቁጣ የሚወርድባቸው በዚያው በፈጣሪያቸው ደካማ ባህርይ ምክንያት ነው:: ፈጥሮ አስተዋለ:: ሆኖም በመጀመሪያ ፍጥረቱን በአእምሮው ውስጥ እንደቀረፃቸው ውብ ሆነው አላገኛቸውም:: በዚህም ተስፋ በመቁረጥ ይናደዳል:: ስለዚህ የሰራውን አፍርሶ እንደገና በተሻለ ሁኔታ ሊፈጥር ይወስናል:: ውሳኔው መንቶችን ማጥፋት ቢሆንም ውሻ ከፈጣሪ ቁጣና ጭፍን ፍርድ በተቃራኒ ትቆማለች:: ቀውሱንም ትገላግላለች:: ውሃ ውስጥ ይሰጥሙ ዘንድ የተወሰነባቸውን መንቶች ከሰማይ ወደ ምድር ይዛ በመሸሽና ጎሬ ውስጥ በመደበቅ:: ይህ የውሻ (እሷም የጆክ ፍጡር ነች) የታዳጊነት ሚና ጆክን ወደባሰ ቁጣ ይመራዋል:: እናም የዓለም ሚዛን በዘላለማዊነት ሳይዛባ ተጠብቆ ይቀጥል ዘንድ በጥንቃቄ በእጁ ይዞት ይኖር የነበረውን "ኪሊ-ጉር"ን (Kil-guur) ወደ ውሃ ይወረውረዋል:: ህያው ፍጥረት ይጠፋ፥ ዓለም ይደመሰስ ዘንድ ከሰማይ በንዴት ኃይል ወደ ውሃ የወረወረውን "ኪሊ-ጉር" ግን ገና በአየር ላይ እንዳለ አሁንም ውሻ በአፏ በመቅለብ ከደረቅ መሬት ላይ ታስቀምጣለች:: በዚህም ዓለምን ደጋግማ ትታደጋለች:: በመሆኑም አኙዋዎች ስለ ፍጥረት የሚያነሱትን ጥያቄና ለጥያቄው ስለሚሰጡት መልስ፥ እንዲሁም በራሳቸውና በፈጣሪ መካከል ስላለው ግንኙነት፥ እምነትና አመለካከት "ሌሮ" በሚል ስያሜ በሚጠሩት ሚት/myth/ አማካይነት ከትውልድ ወደ ትውልድ በማስተላለፍ እንደሚጠቀሙበት እንገነዘባለን::

የአኙዋዎች ታሪክ: ባህልና የአኗኗር ስልት በጽሁፍ አልተመዘገበም:: እምነትን፥ አመለካከትንና ልምድን (እውቀትን) ለመጪው ትውልድ ህብረተሰቡ የሚያስተላልፍበት ብቸኛው መንገድስነቃል በመሆኑ "ሌሬ" የህዝቡን አመጣጥ፥ ውጣ ውረድ የተሞላበትን ታሪክ ለተተኪው ትውልድ ያስተምራል:: ለምሳሌ. የአኙዋ ጥንታዊ አባቶች (የኝካንግ፥ የጊሎና የዲሞ) ጥል መፍጠር፥ እርስ በእርስ መዋጋት፥ በኋላም መሰደድና በየአቅጣጫው መበታተን የሚተርከው ቀጥሎ የሰፈረው ሌሮ በአኙዋዎች ዘንድ እንደ እውነተኛ ታሪክ ሆኖ ሲዘከር ይኖራል:: ታሪኩም እንደሚከተለው ሰፍሯል::

> በድሮ ዘመን ሶስት ወንድማማቾች ነበሩ:: እነዚህ ወንድማማቾች ኚካንግ፥ ጊሎና ዲሞ ይባሉ ነበር:: ወንድማማቾቹ አብረው በፍቅር፥ በሰላምና በመተሳሰብ ሲኖሩ ከዕለታት አንድ ቀን የጊሎ ልጅ አጎቱን-ኝካንግን፥ "አደን ልሄድ ነውና ጦር ስጠኝ" ብሎ ለመነው:: ኚካንግም ጦሩን ለወንድሙ ልጅ ሰጠው::
>
> የጊሎ ልጅ አደን ተሰማርቶ ሳለ ዝሆን አገኘ:: በኋላም ዝሆኑን በጦር ወጋው:: ዝሆኑ ግን ሳይሞት፥ ጦሩ እንደተሰካበት ሮጦ ጠፋ:: የጊሎ ልጅም ዝሆኑን ቢፈልግ፥ ቢፈልግ ሊያገኘው አልቻልም:: የአጎቱን ጦር ዝሆኑ እንደተወጋ ይዞበት ስለጠፋ በጭንቀት ላይ ወደቀ:: ስለዚህ የዝሆኑን ዱካ መፈለግ ቀጠለ:: በመፈለግ ላይ እንዳለም፥ ስንቁን ጨርሶ፥ የሚበላው አጥቶ፥አፈር እየቃመ ቢፈልግ፥ ቢፈልግ...ዝሆኑን ወይም ጦሩን ሊያገኝ አልቻለም:: ከብዙ ጊዜ በኋላም ተስፋ በመቁረጥ ወደ ቤቱ መጣ::

የገጠመውን ችግር፥ የጦሩን መጥፋት፥ የዝሆኑን በጦር እንደተወጋ ማምለጥ፥ ለአባቱና ለአጎቱ አንድ በአንድ ዘርዝር ነገራቸው።

አጎቱ ኒካንግም የጦሩን መጥፋት በሰማ ጊዜ በጣም ተናደደ። ስለዚህ "ጦሬን ስጠኝ" አለው። ያ አደን ወጥቶ የነበረው የወንድሙ ልጅም ተጨንቆ "እባክህ ተመሳሳይ ጦር ልስጥህ ወይም ደግሞ ዲሙይ ልስጥህ፥ ዋጋውን ልክፈል" ብሎ ለመነው። ኒካንግ ግን "የራሴን ጦር ካላመጣህ ተመሳሳይ ጦር ወይም ግምቱን አልቀበልም" በማለት "እንቢ" አለ። በዚህ ጊዜ የወንድሙ ልጅ በጣም ተጨነቀ። ከመጨነቁ ብዛትም ስንቅ ይዞ ጦሩን በየሸንተረሩና በየደኑ አንድ በአንድ አገሩን እየዞረ ለብዙ ጊዜ ሲፈልግ፥ ሲፈልግ በጦር የተወጋው ዝሆን ሞቶ፤ ስጋው ረግፎ፥ አጥንቱ ቀርቶ አገኘው። ግን ዝሆኑ ጦሩን እንደተሸከመ ሞቶ ስለነበረ ከዚያው ከወደቀበት ቦታ ላይ አገኘው። የአጎቱን ጦር በማግኘቱም በደስታ ተውጦ ወደቤቱ መጣ። ጦሩንም ለአጎቱ ሲመልስ እንዲህ ሲል ተናገረው ይባላል። "ተመሳሳዩን ጦር ልትቀበለኝ ትችል ነበር፤ 'እንቢ' በማለትህ ከብዙ አደጋ ላይ ወደቅሁ፤ ብዙ ፈተና ደረሰብኝ። ከህመምና ከሞት ፥ ከአንበሳ፥ ከዝንዶ፥ ከነብር፥ ጋር ተዋግቼ አምልጬ መጣሁ። አሁን ጦርክን ተቀበል። እኔንም እንደማትወደኝ አውቄአለሁ" አለው።

ከዚህ በኋላ ኒካንግና የወንድሙ የጊሎ ልጅ ሆድ ለሆድ ሳይገናኙ ቂም ይዘው ሲኖሩ አንድ ቀን የኒካንግ ቤት ህፃን ልጅ የዚያን የጊሎን ልጅ "አንዲት የዝሆን አይን" (ዲሙይ) አንስታ ዋጠች። በዚህ ጊዜ ለአባቷ /ለኒካንግ/ ልጅህ ዲሙይ ዋጠችብኝ፤ ምን ላድርግ?" ብሎ ጠየቀው።

ኒካንግም "ልጄ ዲሙይ ከዋጠችብህ ዲሙይ እከፍልሃለሁ" በማለት መለሰለት። የወንድሙ ልጅ ግን "አንተ ተመሳሳይ ጦር ልስጥህ፤ ወደሞት አትግፋኝ፡" ብዬ በለመንኩህ ጊዜ 'የራሴን ጦር ካልሆነ ሌላ አልቀበልም' አላልከም ነበርን? እኔም የራሴን ዲሙይ ካልሆነ የአንተን ዲሙይ አልቀበልም" በማለት "እንቢ" አለው ይባላል። በዚህ ጊዜ ኒካንግ ተጨነቀ። "ከልጅቱ ዓይነምድር ጋር የዋጠችው ዲሙይ ሊወጣ ይችላል፤ ስለዚህ ሰገራ ስትወጣ እየተጠባበቅን እንያ አለው፥ የወንድሙን ልጅ። ከዚያ ልጅቱ ሰገራ በወጣች ቁጥር እየጠበቁ ቢያዩ፥ ቢያዩ የዋጠችው ዲሙይ ሊገኝ አልቻለም። ወር፥ ሁለት ወር አለፈ። አልተገኘም።

ከዚህ በኋላ የኒካንግ የወንድም ልጅ "የልጅቱ ሆድ ተቀዶ ዲሙዬን ማውጣት አለብኝ" ሲል ኒካንግን አስጨንቆ ያዘው። የኒካንግን ልጅ ሆድም ቀደደና ዲሙዬን አገኘ። ህፃኒቱ ሞተች። በዚህ ምክንያት ኒካንግና የወንድሙ ልጅ የማይበርድ ጠብ ፈጠሩ። በወንድማማቾቹ መካከል መገዳደል ተጀመረ። ከዚያ ወዲያ አንዱ የአንዱን ልጅ ይገድላል። በዚህ የተነሳ ኒካንግ ወደ ሱዳን፥ ጊሎ ወደ ኢትዮጵያ ዲሞም እንደዚሁ ወደኬንያ አቅጣጫ ተበታተኑ ይባላል።[6]

አኙዋዎች ከዚህ በላይ ከሰፈረው፥ "ሌሮ" በማለት ከሚጠቅሱት፥ ተረት ጋር አያይዘው ዘመኑን በውል ባያውቁትም "በጥንት ጊዜ" በማለት ቅድመ አያቶቻቸው ኡጋንዳ ውስጥ "በቪክቶሪያ ሀይቅ" አካባቢ ከሚገኝ "አሾሌ" (Acholli) ከተባለ ስፍራ ተነስተው፥ ደቡብ ሱዳንን በማቋረጥ የአኮቦን ወንዝ ተከትለው በመስደድ ከዛሬው አኙዋ ምድር አዶንጎ-ዊአዶሮ ከተባለ ቦታ ላይ መስፈራቸውን ይተርካሉ። ይህን የአመጣጣቸውን ታሪክም ለልጆቻቸው

6

ተራኪ፥ ካፒቴን ኃይለሥላሴ ኝገም፥ አቦቦ፥ ጥር 27 ቀን፥ 1990።

እንዳይዘነጋ፥ በጊዜ ርቀት እንዳይረሳና እንዳይጠፋ ይነግራሉ።

በተረቱ አማካይነት የቀረበው ይህ ታሪክም እውነትነት ያለው ይመስላል። ምክንያቱም የቋንቋና የአንትሮፖሎጂ ምሁራን የኢትዮጵያ አኙዋዎች በዑጋንዳ ውስጥ ከቪክቶሪያ ሀይቅ አካባቢ ከሚኖሩ አቾሊዎች ጋር በቋንቋ፥ በባህልና በማህበራዊ ገጽታዎች እጅግ በጣም የሚመሳሰሉ መሆናቸውን ስለሚጠቁሙ ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በሱዳን ውስጥ ከሽሉኮች፥ በምዕራብ ኬንያ ከሉኦዎች ጋር ዝምድና እንዳላቸው ጨምረው ያመለክታሉ (Evans-Pritchard, 1941; Lusted, 1976; Kurimoto, 1992; Reh, 1996)። ይልቁንም P'Bitek (1974) ባዘጋጀው መጽሀፍ ውስጥ የአቾሊዎች አኑዋኑዋር፥ ልማድና የባህላዊ ቁሳቁስ ስያሜዎች ከአኙዋዎቹ ልማድና ስያሜዎች ጋር በእጅጉ ተመሳሳይነት እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል።

ሌሮው አያሌ ዘመናትን ወደ ኋላ አቋርጦ በመመለስ ጥንታዊ አኙዋዎች በአደን ስምሪት ይኖሩ እንደነበር ይጠቅሳል። ቶንግ (ጦር) እና "ዲሙይ" (ጨሌ) በፍቅር፥በደስታና በሰላም ይኖሩ በነበሩ ወንድማማቾች መካከል ቅራታ፥ ጥል፥ መጨካከንና መገዳደል፡ ኋላም መበታተንና መሰደድን ያስከተሉ ባህላዊ ቁሶች መሆናቸውን ጨምሮ ያስረዳል። ይህ በሁሉም መስኮች ሰፊ ጥናትን የሚጋብዝ ሲሆን ዛሬ የአኙዋዋችን ማንነትና ልማድ በመግለጽ በኩል "ዲሙይ" እና "ጦር" ያላቸውን ጠቀሜታ እንድናጤንም ይጋብዛል። "ዲሙይ" የጋብቻ ማስተሳሰሪያ ውድ የሆነ የወግ ዕቃ ነው። "ዲሙይ" ዛሬም የአኙዋዎች ማህበራዊ ቦታ መገለጫ ነው። ውበት ነው። በተለይም "ኡቾክ" የተባለው የጨሌ ዓይነት ከስርዓተ-ንግሥ ወይም ከሹመት ማረካከቢያ (ማውረሻ) የደንብ ዕቃዎች አንዱና ዋናኛው ነው። ጦርም(ቶንግ) የአደንና የራስ መጠበቂያ መሳሪያ ከመሆኑ ባሻገር እንደ ጨሌ የጋብቻ ማስተሳሰሪያ፥ እንደ "ኡቾክ"የሥርዓተ-ንግሥ የወግ ዕቃ ሆኖ ያገለግላል። ከዚህም በላይ ሌሮው ኚካንግ በደቡብ ሱዳን፥ ዲሞ በኬንያ፥ ጊሎ ደግሞ የአኮቦን ወንዝ ተከትሎ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት መስፈሩን ይጠቁማል። ቻም አዶም (1996:7) እንደ ፃፉት ጊሎ የኢትዮጵያ አኙዋዎች ቀዳሚ አባት ነው። ሌሮውም ይህን ታሪካዊ ሁኔታ ነው የሚያቀርበው። የሞራል ዋጋውም ከፍተኛ ሆኖ ነው የሚገኘው። ምክንያቱም በወንድማማቾች መካከል ለደረሰው ጥፋት መንስኤ የሆኑትን ጉዳዮች መሰረት በማድረግ "ብድር በምድር"፥ "አትፍረድ ይፈረድብሃል"፡ ወይም "ሥራ ለሠሪው፥ እሾህ ላጣሪው" የሚባለውን የህይወት ኀጠመኝ ያስተውሉ ዘንድ አኙዋዎች ለልጆቻቸው ትምህርት ይሰጡበታልና።

አኙዋዎች "ሌሬ" ብለው በሚጠቅሱት በዚህ የተረት ዓይነት ውስጥ የሚመደበው "አሹዶ" (Ocuudho) አንድ የስነቃል ቅርስ ምን ያህል የተፈጠረበትን (የሚነገርበትን) ህብረተሰብ ባህላዊ ተቋሞች፥ ልማዳዊ ህጎች፡ ስነምግባራዊ ደንቦችና መርሆዎችን እንዴት እንደሚያሰርጽ፡ ህጋዊ እንደሚያደርግ፥ እንደሚያስጠብቅና ማኀበራዊ ግንኙነትን እንዴት እንደሚመራ...መረዳት እንችላለን። የአገሩ ተወላጆች እንደሚረዱትና ማስተዋልም እንደሚቻለው የአሹዶ ሚት (ሌሮ) የአኙዋ ህብረተሰብ የዕለት ተዕለት ማህበራዊ ግንኙነት

ሞዴል ነው ማለት ይቻላል። መሀመዳዊያን በመሀመድ ትምህርቶች፥ አይሁዳውያን በሙሴ ትዕዛዛት፥ ህዝበ ክርስቲያኑም በኢየሱስ ታምራት፥ ቡዲሂስቶች በቡድሃ ትምህርቶች... እንደሚያምኑ ሁሉ እነሆ አኙዋዎችም በአሹዶ አስተሳሰብና ትምህርት ይመራሉ። የአኙዋ ማህበራዊና ባህላዊ የአስተዳደር ተቋሞችም በዚሁ በአሹዶ ሌሮ ላይ ተመስርተው የቆሙ ነው የሚመስሉት። በመሆኑም የሌሮውን ይዘት ከመመልከታችን በፊት ባህላዊ የአስተዳደር ተቋሞችን ስዕል (pattern) በቅድሚያ ማየቱ ይበልጥ ግልጽ ሊያደርግልን ይችላል።

አኙዋዎች በንጉሥ (Nyieya) እና በአለቆች (Kwari) ይተዳደሩ ነበር። ዛሬም ባህላዊ አስተዳደሩ እያንሰራራ ይገኛል። የሁለቱም ሥልጣን በዘር ሀረግ የሚተላለፍ ነው። ሥልጣን በዘር ሀረግ ቢተላለፍም "ኜያነት" ወይም "ኳሮነት" በሚሰጠው ሰው ብቃትና ችሎታ ላይ በቅድሚያ ህዝቡ ማመንና መቀበል አለበት። ሥልጣን አውራሽ "ይሻላል" ለሚለው ለአንድ ሰው ሊናዘዝ ይችላል። ኑዛዜውም ልማዳዊ ስርዓትን (ritual) በተከተለ ሁኔታ ለህዝብ ይገለፃል። ስርዓቱ ሲከናወን በኑዛዜ ስለቀረበው ስለ እጩው ስነምግባርና ሰብዕና በረጋ ሁኔታ ህዝብ ይነጋገርበታል። ከልጅነቱ አንስቶ የሠራቸው ስህተቶች ካሉ በግልፅ ይቀርባሉ። እነዚህ ስህተቶች ለስልጣን እንደማያበቁት በህዝቡ ከታመነበት አውራሹ ባቀረበው እጩ ምትክ ከዚያው የዘር ሀረግ ውስጥ ሌላ ሰው ይፈለጋል። ተፈልጎ ሲገኝ ስለ እርሱም የስምምነት ስርዓቶች ይከናወናሉ። ይህ ሰው በህዝቡ ዘንድ "ብቁ ነው" ከተባለ በስርዓት ይነግሳል ወይም ይሾማል። አንድ ሰው ኜየ (ንጉሥ) ሆኖ በህዝብ ፊት በሚነግስበትና ኳሮ ሆኖ ሹመቱ በሚፀድቅለት ባህላዊ ስነስርዓት ወይም የሥርዓተ-ንግስና ሹመት(Rony) ላይ የወግ ዕቃዎችን ካለፈው ኜያ ወይም ኳሮ በህዝብ ፊት ይረከባል። ጥቂቶቹን የወግ እቃዎችና የስነስርአቱን ሁኔታ ለመጥቀስ ያህልም:-

1. "ኡቾክ" ጨሌ ከአንገቱ አነቱ እንዲያስሩለት ይደረጋል።
2. "ኡቻላ" የተባለ የጦር አይነት ተረክቦ በእጁ ይይዛል።
3. የ"ኡቻላ" ማስደገፊያ "ዲክዌሪ" ይረከባል።
4. ትልልቅ በርጩማዎች "ውሎ" ("ዙፋን" ማለት ነው።) ይረከባል፤ ይቀመጥባቸዋልም።
5. ከዚህ በኋላ ለህዝቡ ንግግር ያደርጋል፤ "የአባቶቼ ልጅ እሆናለሁ" በማለትም ቃል ይገባል። በስሩ በተለያዩ ሃላፊነቶች ሊሾማቸው የመለመላቸውን ሰባት ሰዎች ተራ በተራ እያቀረበ በህዝቡ ድጋፍ ያስፀድቃል። እነዚህ በስሩ የሚሾሙት የጦር ሃላፊ፥ የግቢ ሃላፊ፥ መልዕክተኛ፥ ዳኛ፥ ሙጋቢ ወዘተ ይባላሉ። በተጨማሪም ከእናቱ ወንድሞች መካከል አንዱን መርጦ ላም ይሸልማል።
6. ሥርዓተ-ንግሡ በዚህ ሁኔታ ሲካሄድ የባላባት ዘሮች ከአንበሳ ወይም ከነብር ቆዳ ላይ በክብር መቀመጥ አለባቸው።
7. ሥርዓተ-ንግሡ እንዳበቃ ጭፈራ መብልና መጠጥ ይቀጥላል።

ባህላዊው አስተዳደር የሚዋቀረው ከላይ በተጠቀሰው መልክ መሆኑን ከተመለከትን ዘንድ የአሹዱን ሌሮ ከማቅረባችን በፊት "ደንቦቹና ልማዳዊ ህጎቹ ምንድን ናቸው?" የሚሉትን ነጥቦች፥ ማየት ያስፈልጋል፡፡ስለሆነም የአኙዋን ማህበረሰብ ልምዳዊ ደንቦችና ህጎች ከዚህ ቢታች እንገልጻለን፡፡

1. የሰው ሚስት መድፈርና የልጃገረድን ክብረ ንፅህና መግሰስ እስከሞት ድረስ ያስቀጣል፡፡
2. የነፍስ ግድያ እንዲሁም ሌሎች ወንጀሎች "በክወር" መንገድ (በእርቅ) በካሳ ወይም በስምምነት በ"ጆ-ዶንጎ" (በሀገር ሽማግሌ) በኩል ይፈጸማል፡፡
3. አንድ ሰው በእጁ ነፍስ ከጠፋበት፥ ወይም ጉዳት በማድረስ ወንጀል ከፈፀመ ወዲያውኑ ጊዜ ሳይወስድ ለኜያ ፥ ለኳሮ አለያም በእነርሱ ስር ለተሾሙት ከላይ ለተጠቀሱት ባላባቶች እጁን መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ በቸልተኝነት ይህን ሳያደርግ ቀርቶ በቀል ቢደርስበት ግን በባህሉ መሠረት ወንጀለኛው ደመከልብ ይሆናል፡፡
4. እጁን ለኜያ ወይም ለኳሮ የሰጠ አንድ ወንጀለኛ ከበቀል እርምጃ ነፃ ነው፡፡
5. አንድ ወንጀለኛ እጁን ለኜያ ወይም ለኳሮ እንደሰጠ ኜያው ወይም ኳሮው ለወንጀለኛው ቤተሰቦችና ጥቃት ለተፈፀመባቸው ወገኖች ወንጀለኛው እጅ የሰጠ መሆኑን ወዲያውኑ ያስታውቃል፡፡ ኡቶቺንግ (የእጅ ማሰሪያ) ይከፍላል፡፡ በመልዕክቱ መሰረት ሁለቱም ወገኖች ከኜያው ወይም ከኳሮው ግቢ መጥተው ስለተፈፀመው ድርጊት በመነጋገር በጆ-ዶንጎ ታይቶ ፍርድ እንዲሰጥበት መስማማታቸውን መግለጽ ይኖርባቸዋል፡፡ በጆ-ዶንጎ ነባሪነት ስምምነት እንደተደረገም ወንጀለኛው ያለፍርሃት፥ እየሰራ በሰላም እየኖረ ፍርዱን ይከታተላል እንጂ አይታሰርም፡
6. አንድ አኙዋ አንዲትን ልጃገረድ "አገባሻለሁ" ብሎ የቃለመሀላ የወንብ "ዲሙይ" ወይም ጨሌ በሁለቱ መካከል በፍቅር (በችድ) ከተለዋወጡ በኋላ ከሀደት ቢፈፅም በልጅቷ ወገኖች በቀል ሊፈፀምበት(ሊገረፍ) ይችላል፡፡ ይህ ድርጊት በባህሉ መሰረት ትልቅ ወንጀል በመሆኑ በተራ ቁጥር (3) የተጠቀሰው ልማዳዊ ህግም ይመለከተዋል፤ ካሳም እንዲከፍል ይገደዳል፡፡

የእነዚህ የተዘረዘሩት ባህላዊ ህጎች አፈጻጸም በአንድ ቃል "ክወር" ተብለው ይታወቃሉ፡፡ "ክወር" የአኙዋዎች የዳኝነትና የእርቅ ባህላዊ መንገድ ነው፡፡ በአኙዋ ማህበራዊ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ህጉን ያቋቋመውም፥ ከፊል የሰው ከፊል ደግሞ የፈጣሪ ባህሪይ የተሰጠው "አሹዱ" መሆኑ ይነገራል፡፡ በአሹዱ ትምህርት ወይም በ"ክወር" ህግ መሠረት አንድ ወንጀለኛ

እጁን ለኘያ ወይም ለኳሮ ከሰጠ በኋላ መበቀል ወንጀለኛን እንደመጉዳት ሳይሆን ይልቁንም ሥርዓትን እንደመጻረር፣ ሰላምንና ፀጥታን እንደማደፍረስ፥ ከዚያም በላይ የሙታንን እርግማን (acieni) እንደመቀበል ተደርጎ ስለሚቆጠር እጁን በሰጠ ሰው ላይ የበቀል እርምጃ በኦሮሞ ባህል የተከለከለ ነው። ስለዚህ ማንኛውም ሰው በሽማግሌ መማክርት የተያዘውን የ"ክወር" ሂደት ይከታተላል። ሽማግሌዎችም የወንጀሉን አፈፃፀም አጥንተው የፍርድ ሀሳብ ለኘያ ወይም ለኳሮ ከገለፁ በኋላ በኘያው ወይም ኳሮው በኩል ለባለጉዳዮቹ ውሳኔው ይነገራል። በክወር ህግ መሰረት በኦሮሞ ባህል በተራ ቁጥር (1) ከተመለከተው በስተቀር የእስራትም ሆነ የግድያ ቅጣት የለም ማለት ይቻላል። ቅጣቱ፥ ቅጣት ከተባለ ካሳ በ"ጉሙዶ" መልክ መክፈል ነው። ካሳውም እንደ ወንጀለኛው አቅም፥ የኑሮ ደረጃና ሁኔታ ይመዘናል፤ ይለያያልም። ወንጀለኛው ሀብትና ገንዘብ ካለው "ጉሙዶ" ወይም ጦር ወይም ገንዘብ ይከሳል። ደሀ ከሆነ ሴት ልጁን ጉዳት ለደረሰበት ወገን (ቤተሰብ) ይከፍላል። ወንጀለኛው ሀብትም ሴት ልጅም የሌለው ከሆነ ደግሞ ወንድ ልጅ ይከሳል። ሀብትም ልጅም ጨርሶ የሌለው ከሆነ ግን ራሱን በቅን አገልጋይነት አሳልፎ መስጠት እንዳለበት የ"ክወር" ልማዳዊና ባህላዊ ህግ ያስገድዳል።

በኦሮሞ የዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ ከፍተኛ ዋጋ ካላቸው ባህላዊና ስነምግባራዊ ደንቦች መካከል ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጥቂቶቹ ናቸው። ሆኖም የእነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ልማዳዊ አሰራሮች፥ ህጎችና ደንቦች የፍልስፍና መሰረትና የመርሆ ምንጮች ምንድን ናቸው? እንዴት በህብረተሰቡ ህይወት ውስጥ ሊሰርፁና የዕለት ተዕለት ማህበራዊ ግንኙነቶችን ዛሬ በሚገኙበት ደረጃና ሁኔታ ሊመሩ፥ ሊቆጣጠሩና ሊገዙ ቻሉ? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በመጠኑም ቢሆን ለመረዳት የአሹዶን ሴር(ሚት) ከተቀረፀበት አውደ ስርዓት ጋር አያይዘን እንመልከት።[7]

7

ቀኑ ጥር 26፥1990 ነበር። ቦታው በአቦቦ ወረዳ "ኡኩና" የተባለ ቀበሌ ሲሆን መንደሩ በደንና በበዝሌጥ የታጀበ ነው። ቢት በሁለት ሰዓት ጊዜ ግ ከአቦቦ ከተማ ወደ ኡኩና ለንጋህ ከርቀት የነጋሪት ድምፅ ያስተጋባል። ከተለያየ አቅጣጫ ጥሪ የደረሰውና የአካባቢው ነዋሪ ሴት ወንድ፥ ወጣት ሽማግሌ ሳይል ወደዚያው ይጓዛል። ከቦታው እንደደረስን የተለያዩ ትዕይንቶች ይታዩ ነበር። ነጋሪቱ በሁሬየው ከተካለሉ ከበሮዎች ጋር ተራውን እየጠበቀ ይተማል። የነጋሪቱንና ("ቡል" ይባላል በአኝዋክ) የከበሮዎቹን ንዝረትና ምት እየተከተለ ግማሹ ህዝብ ይጨፍራል። የሚጨፈረው ተሳታፊ ወንዱን ሴቱን አርጊቱንና ሽማግሌውን ሁሉ ያካተተ ነበር። ግማሹ በውሃቱን ነጭ ከጠብቀዋል ተቀብሏል። ግማሹ ቀይ፣ ሌላው ቀይና ነጭ በመቀባት በእጁ ጦር፥ ቅጠል ወይም የኢዝግና የጎሽ ቀንድ በመያዝ፣ ከራሱም ላይ በማድረግ የተለያዩ የተቀናጀ የዳንስ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ውዝዋዜው በራሱ የቀለጠፈ ቋንቋ ይመስል ነበር። አልፎ አልፎ ቀንደ መለከትና ጡሩንባ ይነፋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከነብር ቆዳ ላይ ተቀምጠው "አተርቡን" የሚባል ባህላዊ መጠጥ ሙሰው እንደሸንበቆ ከፍት በሆነ ቀጭን፥ ረጅም የአገዳ ቧንቧ እየሳቡ፥ እየጠጡ፥ በረጋ መንፈስ ጭፈራውንና ስርዓቱን ሲያዩ የሚጫወቱ ሰዎች አሉ። እነዚህ ከነብር ቆዳ ላይ የተቀመጡት ባላባቶች ናቸው። የባላባትና የነገሢ ዘርነታቸውን በተለይ የሚያመላክተውም የተቀመጡበት የነብርና የአንበሳ ቆዳ ነው። አንዳንዴ "ጀይ" በሌላ ጊዜ "ዋቶንግ" ተብሎ የሚጠራው የባላባት ወገን ያልሆነው ተራው አኝዋ ደግሞ ከቢዶ ሳር ላይ ተቀምጧል። አተርቡኑን ግን ከአቶ ተከሎ ይሰባል። ግማሹ መጠጡን ሲስብ ግማሹ ደግሞ ከ"አኪዮ" ትንባሆውን ሲጋይቶ እየማገ የስርዓቱ ንግሱን ጭፈራ በሊቃ ይመለከታል።ብሎ አልቆየም። ጫጫታው ዳንሱና የከሉ ስግምግምታ ረብ አለ። ወዲያውም ሁለት ሰዎች ከባላባቱ ፊት ቆሙ። ከሁለቱ መካከል በእድሜ ጠና ያለ ሽማግሌ ከነፍጣው አገዙ ቆሞ ከነበረው ሰው አንገት ጨሌ አጠለቀ። ጦርም ሰጠዋቸው።ሁሉም በጉጉት ይመለከታል። ይህ የሹመት ስርዓት በአጠቃላይ "ሮኒ" ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን በአለቱ የኳሮነት ማዕረግ የፀደቀላቸው ፊሊፕ አሞድ ኘየር የሚባሉ፥ በእድሜ አሁል ፍሬ የሆኑ፥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀቁ፣ ለብዙ ዓመታትም በግብርና ሙያ ያገለገሉ የመንግሥት ሠራተኛ ናቸው። "አባቴ ኳሮ እንደሆን ከመሞታቸው በፊት ተናዘዙ። ኑዛዜው በህዝብ ፀደቀ። እንዳየኸው በዛሬው እለት ሮኒው (ስርዓተ-ሹመቱ) ተከናወነ።" አሉ ከስርዓቱ በኋላ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ሲመልሱ።

እናም ኳሮ ፊሊፕ ኘየር በደስታ ተውጠው ተመልሰው ከባላባቶች መሀል ከነብር ቆዳ ላይ ተቀመጡ።

ጥንት አባቶቻችን ህግ አልነበራቸውም። እንደዛሬው ስርዓት አልነበረም። ጉልበት ያለው ትልቅ ይሆን ነበር። አንዱ እንደፈለገ የሌላውን ሀብት ይዘርፋል። የሌላውን ሚስት ይቀማል። ደካማውን ይገላል። የገደለ በሰው መሀል እንዲገደል፥ አካል ያጎደለ በህዝብ ፊት በተመሳሳይ አካሉ እንዲጎድል፣ የሰው ሚስት የደፈረ ሚስቱ እንድትደፈር ይደረግ ነበር። በዚህ ምክንያት እልቂት፥ ፍጅት፥ ጦርነትና ስደት በርክቶ ሳለ አንድ ቀን "አሹዶ" የሚባል ሰው ከባህር ወጥቶ ህግ አስተማረ ይባላል። ታሪኩ የሚከተለው ነው።

ከዕለታት አንድ ቀን ሁለት ወንድማማቾች ዓሳ ለማጥመድ ወደ ወንዝ ሄዱ። ማጥመድ እንደ ጀመሩም አንድ ዓሳ ያዙ። ሲይዙትም ትልቁ ራሱን፥ ትንሹ ጅራቱን ነበር። ሁለቱ ወንድማማቾች ዓሳውን በዚህ ሁኔታ ከያዙት በኋላ "እኔ ነኝ የያዝኩት፤ የእኔ ነው፣ የእኔ ነው፤" በመባባል ተጣልተው ሊጋደሉ ሆነ።

በዚህ ጊዜ አሹዶ ከባህሩ በመውጣት ቅጠል ከራሱ፥ ኡቾክ ከአንገቱ፥ ዲቻሪና ዲሙይ ከወገቡ አድርጎ፤ በእጁ ኡቻላ ጦርና ዲክዌሪ ይዞ፤ ከክንዱ አንባር አጥልቆ ወጣና ከወንዙ መሀል ከበቀለ ግን ከደረቀ ትልቅ የግንድ ጉማጅ ላይ ተቀምጦ "ዓሳው የኔ ነው፤ የኔ ነው፤ ልቀቅ..." እየተባባሉ የሚጣሉትን ወንድማማቾች "እናንተ ልጆች አትጣሉ። ይልቅ እኔ የምነግራችሁን አድርጉ" አላቸው። ወንድማማቾችም በድንጋጤ አሹዶን በማየት "እሺ!" አሉት። ኋላም "አንተ ዓሳውን በራሱ በኩል የያዝከው ልጅ ልቀቀው" አለው።

ራሱን ይዞት የነበረው ልጅ እንደታዘዘው ዓሳውን ለቀቀ። ወዲያው ጅራቱን ይዞት ከነበረው ልጅ ዓሳው አፈትልኮ አመለጠ። በጅራቱ በኩል ይዞት የነበረውን ልጅም አሹዶ "በል ደግመህ ጅራቱን ያዝና ዓሳውን አስቀር እንጂ!" አለው። ይዞ ለማስቀረት ደጋግሞ ሞከረ፤ የዓሳውን ጅራት ግን ይዞ ማስቀረት አልቻለም።

በኋላ "በል ዓሳውን በራሱ በኩል ያዘው" አለው። እንደታዘዘውም በራሱ በኩል ያዘው። ዓሳውም ሊያፈተልክና ሊያመልጥ አልቻለም። ከዚህ በኋላ መጀመሪያ ዓሳውን በራሱ በኩል ይዞ የነበረውን ልጅ አሹዶ በተመሳሳይ ሁኔታ የዓሳውን ጅራት ያዝ ብሎ አዘዘው። እሱም ጅራቱን ያዘ። ግን ዓሳውን ማስቀረት አልቻለም። "በል አሁን በራሱ በኩል መጀመሪያ ይዘኸው እንደነበረ አድርገህ ያዘው" አለው። በራሱ በኩል ያዘው። ዓሳው ሊያመልጥ አልቻለም። ከዚህ በኋላ አሹዶ በዓሳ ተጣልተው ለነበሩት ወንድማማቾች እንዲህ በማለት አስረዳቸውና ዳኝነት ሰጣቸው ይባላል።

"የዓሳ ጉልበቱ ከአናቱ ነው። ከጅራቱ አይደለም። ራሱን የያዘ ያስቀረዋል። ጅራቱን የያዘ ግን ያመልጠዋል። ስለዚህ ዓሳው ለማን የሚገባ ይመስላችኋል?" አላቸው። እነሱም "ራሱን ለያዘ ሰው ነው እንጂ!" ብለው መለሱለት።

እሱም "እዎ! ራሱን የያዘ የዓሳው ባለቤት ነው" በማለት ከፈረደ በኋላ ወደ ሰማይ ይውጣ፣ ተመልሶ ወደመጣበት ወደባህሩ ይግባ፤ ወደሌላ አቅጣጫ ይሂድ፤ እይሂድ ሳይታወቃቸው ተሰወረባቸው።

ሁለቱ ወንድማማቾችም ይህን ፍርድና ተአምር ለአገሩ ሰው

"ይህ ዓይነቱ ስርዓተ-ሹመትና ሀገራዊ የአስተዳደር አሰራር መቼና በማን እንደተጀመረ ይታወቃል ወይ?" የሚል ጥያቄ እንዳነሳሁ ጊዜው ጥንት "በሸዋይ ዘመን" እንደነበረና የአስተዳደሩን ህጎችና ደንቦች ግን "አሹዶ" የሚባል መንፈሳዊ ሰው ከውሃ ወጥቶ፥ ከህዝቡ ተቀላቅሎ፥ ተአምር አያሳየ የአስተዳደር ስራት መመስረቱንና ማስተማሩን ከዚያም "ካራ" የምትባል የሸዋይን ልጅ አስረግዞ ወደመጣበት አገር (ወደውሃ) በስውር መመለሱን... የሚተርኩትን ሊር(ሜት) እንደ ታሪክ ማስረጃ አድርገው ተረኩ (አሹዶን አንዳንዶቹ "አዚር" በማለት ይጠሩታል)።

ተናገሩ። ሰው ሁሉ በፍርዱና በተአምሩ ተደነቀ። አሹዶንም ለማግኘት ወሰነ። በኋላ ህዝቡ ከወንዙ ተደብቆ መጠበቅ ጀመረ። ግን አሹዶ ፈጽሞ ሊገኝ አልቻለም። በኋላም መጀመሪያ "አገኘነው" በማለት ወሬውን ለህዝብ ያሰሙት ወንድማማቾች ከዚያው ወንዝ በዓሳ እንደመጀመሪያው ቀን እንዲጣሉ ተመከረ። ህዝቡም ተደብቆ ማየትና መጠባበቅ ያዘ። ወንድማማቾቹም አንደኛው በራሱ ሌላው በጅራቱ ይዘው እንደመጀመሪያው ቀን በዓሳ መጣላት ጀመሩ። በዚህ ጊዜ ልክ እንደመጀመሪያው ቀን አሹዶ ከባህሩ ወጥቶ ከደረቁ ግንድ ላይ ተቀመጠና "ተው! ምነው 'ራሱን የያዘ የዓሳው ባለቤት ነው' ብዬ አልነገርኳችሁምን? ለምን በድጋሚ ትጣላላችሁ?" አላቸው።

በዚህ ጊዜ ተደብቆ አሹዶን በጉጉት ሲጠባበቅ የነበረው ህዝብ ከየጥሻው ወጥቶ መጣ። አሾዶንም ያዘው። አሾዶም ህዝቡን እንዲለቀው ለመነ። ህዝቡ ግን "እባክህ፥ ፍርድና ህግ አስተምረን። ከእኛ ጋር አብረህ ኑር..." በማለት ለመነው።

እሱም "የእኔ አገር ውሃ ነው። ሚስቶቼ፥ ልጆቼ ወገኖቼና ሀብት ንብረቴ ሁሉ ካባሬ(ውሃ) ውስጥ ናቸው። እነሱን ትቼ ከእናንተ ጋር እንዴት ልቀመጥ እፈቅዳለሁ?" አላቸው።

ህዝቡ ግን አሁንም ተማፀነው። "አንለቅህም" አለው። በዚህ ጊዜ ከመቅጽበት ወደ አንበሳነት ከዚያም ወደ ዝሆንነት ተለወጠ። ወዲያው ዘንዶ ሆነ። ቀጥሎ ነብር ሆነ። ኋላም ግማሽ በሬ ግማሽ ሰው ሆነ። እንደዚህ ወዲያው ወዲያው ሲለዋወጥ ህዝቡ "አንለቅም" ብሎ ይዞ "እንቢ" አለ። ከዚህ በኋላ አሹዶ እንደመጀመሪያው ተመልሶ ሰው ሆነ።

"እሽ! ልትለቁኝ አልፈለጋችሁም። ወደ መኖሪያ መንደራችሁ ውሰዱኝ" አላቸው። እነሱም በጭፈራ፥ በደስታ ወደመኖሪያ መንደራቸው ወሰዱት። በዚያን ዘመን የጎሳ መሪው "ሽዋይ" ይባል ነበር። ህዝቡ የወሰደው ከእርሱ መኖሪያ ሰፈር ነበር። አሾዶም ከአንዲት ጎጆ ውስጥ ገባ። ሆኖም ምግብ አልበላም፥ ውሃ አልጠጣም አለ። በዚህ ጊዜ ህዝቡ መጨነቅ ያዘና ምግብ እንዲበላ፥ ውሃም እንዲጠጣ ለመነው። አሁንም "አልበላም" አለ። ከብዙ ቀናት በኋላ ሽዋይ "ምን ዓይነት ሰው ነው?" ብሎ ሊያየው አስጠራው። ሽዋይ ግን አሾዶን ባየ ጊዜ እንደቄጠማ ተንቀጠቀጠ። ከፊቱ ቀጥ ብሎ መቆም አልቻለም። ተንቀጠቀጠ። ስለዚህ የወንዝ-ጆክ (Naam-jwok) ነው በማለት አመነና ከነብርና ከአንበሳ ምንጣፍ ላይ እንዲቀመጥ ለመነው። አሾዶም እኔ "ከአሮጌ የነብርና የአንበሳ ምንጣፍ ላይ አልቀመጥም፣አዲስ የነብርና የአንበሳ ምንጣፍ ካልሆነ አልቀመጥም" አለ።

ህዝቡም አዲስ የነብርና የአንበሳ ቆዳ አምጥቶ "ተቀመጥልን" በማለት ለመነው። አሾዶም እንደተቀመጠ "አንተ ህግ አስተምረን። የእኛ መሪ ሁን" አሉት። አሾዶም "አልሆንም፤ ወደ ወገኖቼ እመለሳለሁና አልሆንም፤ እነሱን አልክድም። ከእናንተ ጋር የምቆይ ለተወሰነ ጊዜ ነው" በማለት መልስ ሰጠ።

ህዝቡ ግን "ህግ አስተምረን፣ መሪ ሁነን" በማለት አሁንም አስቸገረው። በዚህ ጊዜ ጥያቄ አቀረበላቸው። ጥያቄውም:- "መሪ ብሆናችሁ ከብቶቻችሁን በሙሉ ትሰጡኛላችሁን?" በማለት በመጀመሪያ ጠየቃቸው።

"አዎን!!" አሉ ሁሉም ባንድ ቃል።

"ወንድ ልጆቻችሁንስ ትሰጡኛላችሁን?" አላቸው ቀጥሎ።

ሁሉም "አዎ!!" አሉት።

"እሽ!ሴት ልጆቻችሁንስ ትሰጡኛላችሁን?" በማለት እንደገና ጠየቃቸው።

እነሱም በአንድ ቃል "አዎ!!" አሉት።

"መልካም ፥ ሚስቶቻችሁንስ ትሰጡኛላችሁን?" ሲል ጠየቃቸው።

> በዚህ ጊዜ መልስ የሚሰጥ አንድም ሰው ጠፋ። አሾዶም ደግሞ ጠየቃቸው። አሁንም ከህዝቡ መካከል መልስ የሚሰጥ ጠፋ። አሁንም ደግሞ ጠየቀ። መልስ የሚሰጥ ጠፋ! ሁሉም በዝምታ ተዋጠ።
>
> ኋላ አሹዱ "የዝምታችሁ ትርጉም ይገባኛል። ይህን ጥያቄ ሳቀርብ በዝምታ የተዋጣችሁበት ምክንያት ሚስት ለሰው የማትሰጥ በመሆኗ ነው። ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ የሰው ሚስት የደፈረ በጦር ይገደላል። ከዚህ በቀር ሰው የገደለ፥ የሰው ሀብትም የወሰደ፥ጥፋት የሰራ ሰው መገደል የለበትም። የሰው ሀብት የሰረቀ፣ የቀማም መገደል የለበትም" በማለት ደንብ፥ የ"ክወር" ህግ አስተማረ፡
>
> አሾዶ ኜያ(ንጉሥ) ሆናቸውና የአስተዳደር ስራትንአስተማረ።ኜያ ሆኖ እያስተዳደረ ህግ ሲያስተምር ኡቻሳ ጠሩን ከዲክዊሪው ላይ ያስደግፍ ነበር። ሆኖም "ምግብ አልበላም" ማለቱን ቀጥሏል። ኋላ ሸዋይ "ከሚስቶቼ አንዲቱን ልስጥህን?" አለው። እሱም "ሚስት ለሰው አትሰጥም ብዬ ተናግሬ የለምን?" በማለት መለሰለት። ከዚህ በኋላ ሸዋይ ልጃገረድ ልጁን ኮሬን ውሃና ምግብ ውሰጅለት አሳት። እሷ የወሰደችለትን ውሃ ለመጀመሪያ ጊዜ አሹዶ ተቀብሎ ጠጣ። እሷ ያቀረበችለትን ምግብም ለመጀመሪያ ጊዜ በፊቃዱ ተቀብሎ በላ። ኋላም "አብረሽው እደሪ" አሳት ልጁን-ሸዋይ። አብራው ማደር ጀመረች። ከጊዜ በኋላም አረገዘች። ባረገዘች ጊዜም "እንግዲህ እኔ ወደ ውሃ (ወደ አገሬ) ልመለስ ነው። የምትወልጅው ልጅ ወንድ ነው። ይነግሳል። ስሙም 'ጊሎ' ይባላል። መቀመጫ ዙፋኑ ደረቅ እንጨት 'ሹዶ' ይሁን" አሳትና ሳይታይ በስውር ወደ ውሃ ተመለሰ። ኮሬም ልጇ እስኪያድግ የአገሩ ንግስት ሆነች። ጊሎም ካደገ በኋላ ከአባቱ ከአሹዶ ቀጥሎ ሁለተኛው የአኙዋ ኜያ (ንጉስ) ሆነ። ሸዋይ ግፈኛ፥ አድሎኛ ነበር። … እሱን አስወግዶ የአባቱን የአሹዶን ህጎችም ተከትሎ ክወርን አስፋፋ። እሱም እንደ አባቱ በስውር ሳይታይ ወደ ውሃ ተመለሰ። በምትኩም ልጁ ቻም ንጉስ ሆኖ ተመረጠ። እና ከአሾዶ ጀምሮ በአኙዋ የኜያ የኳሮና የክወር ስርዓት ቀጥሎ እስካሁን ይሰራበታል።[8]

ኳሮ ፊሊፕ አሞድ ኜያየ ስለክወር ህጎች አመጣጥ፥ ስለኜያ ሥርዓት፥ስለባህላዊ የአስተዳደር አመሠራረት በመተረክ ከአሹዶ እስከ አሁን ድረስ የነገሱትን ኜያዎች የዘር ሀረግ ይቆጠራሉ። በአጠቃላይ አኙዋዎች "ሌፊ" ብለው የሚመድቡት ይህ የአሹዶ ታሪክ የአኙዋ ባህላዊ የአስተዳደር ተቋሞች መሠረት፥ የፍትህና የፍልስፍና ምንጭ መሆኑን እንረዳለን። ከዚህ በተጨማሪም አሹዶ የህብረተሰቡ ሥርዓት ተምሳሌት (prototype) ነው። የእርሱን ባህሪይና ስነምግባር ኜያዎችና ኳሮዎች እንዲከተሉ ባህሉ ያስገድዳል። አሹዶ ከባህር ወጥቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሰዎች ሲገለጽ በእጁ ይዟቸው የነበሩ መሳሪያዎችና ጌጣጌጦች የስልጣን ማረጋገጫና ማውረሻ ዕቃዎች (Emblems of Power) ሆነው ዛሬም ይሠራባቸዋል። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፥ የአሹዶ ሚት በህብረተሰቡ ህይወት ውስጥ ሚዛናዊነትን፥ ፀጥታንና ሰላማዊ ኑሮን የሚፃረሩ ድርጊቶች ሁሉ በ"ክወር" አማካይነት መፍትሄ እንዲኖራቸው፥ ለተፈፃሚነታቸውም በተዋረድ ማህበራዊ ተቋሞች እንዲፈጠሩና በሁሉም ዘንድ እንዲከበሩ ወደፊትም እየገለገሉ እንዲቀጥሉ ለማድረግ ከትውልድ ወደ ትውልድ የማስተላለፍና የማስረፅ

---

8 ተራኪ፦ ኳሮ ፊሊፕ አሞድ ኜያየ፥ ኡኩና(አቦቦ ወረዳ)፤ ጥር 26 ቀን፥ 1990

ተግባር ያከናውናል።

በእኙዋ ህብረተሰብ "ሌሬ" ተብለው የሚታወቁት የትረካ ዓይነቶች እጅግ በጣም ብዙ ናቸው። ከፍ ሲል ለማሳየት እንደተሞከረው የእያንዳንዱን "ሌሬ" ይዘትና ተግባር ከህብረተሰቡ ባህላዊና ማህበራዊ ህይወት አውዶች (contexts) ጋር አቆራኝቶ በሙትንተን የእምነት፥ የፍትህና የአመለካከት መሰረቶችን ማመልከት፥ ህብረተሰቡ የሚገኝበትን የአስተሳሰብ ደረጃ መጠቆምና የዕለት ተዕለት ግንኙነቶቹ የሚመሩባቸውን መርሆዎች፥ ደንቦች፥ ተቋሞችና እሴቶች መረዳት ይቻላል። በአጠቃላይ እኙዋዎች "ሌር" ወይም "ሌሬ" በሚል የሚጠቀሙባቸው ትረካዎች ፎክሎሪስቶችና አንትሮፖሎጂስቶች እንዲሁም ሌሎች የህብረተሰብ ጥናት ተመራማሪዎች "ሚት" እና "ሌጀንድ" በሚል የሚያስቀምጡዋቸው የስነቃል ዓይነቶች (genres) ሲሆኑ የሚያተኩሩባቸው ርዕሰ ጉዳዮችም የስነፍጥረት ጥያቄዎች (ontological questions)፥ የትመጣ-ታሪክ፥ ፍትህ፥ እምነትና ሃይማኖት ወዘተ. ናቸው። በእኙዋዎች "ሌሬ" እውነተኛ የአባቶች እውቀትና ታሪክ ሆኖ የሚታይ ብቻ ሳይሆን የእምነት፥ የርእዮተ አለምና የፍልስፍና ማጠንጠኛ ነው ማለት ይቻላል።

ሌሬ የሚያሰርፃቸውና የሚያስተላልፋቸው እምነቶች፥ እሴቶች፥ ደንቦችና ስነምግባራዊ መመሪያዎች የህብረተሰቡን ህይወት እንደሚገዙና ግንኙነቶችንም እንደሚቆጣጠሩ ሁሉ ቀጥሎ በምንመለከታቸው "ዋች"(Waac) ብለው ተናጋሪዎቹ በሚመድቧቸው ሊሎች የተረት ዓይነቶች ደግሞ የገፀባህሪያቱን አስተሳሰቦች፥ ግንኙነቶችና ድርጊቶች ሲወስኑ እናያለን። ለምሳሌ በዋች ውስጥ የሚገኙ ግጭቶችና ቀውሶች የከወር መርሆዎችን (ህጎችን) መሠረት አድርገው እልባት ያገኛሉ። ገፀባህርያቱ (እንስሳትም ይሁኑ ሰዎች) በ"ጆዶንጎ" ጣልቃ ገብነት (mediations) መፍትሄ ላይ ሲደርሱ እንመለከታለን።

1.1.2 **ዋች (Waac):-** "ዋች" ተብሎ የሚታወቀው የእኙዋ ተረት በአብዛኛው ነጠላ ታሪክ ያለው ነው። የሚያተኩርበት ጉዳይም ክፋትን ከደግነት፥ ስስትን ከለጋስነት፥ቂልነትን ከብልጠት፥ ተንኮልን ከቅንነት፥ ጥላቻን ከፍቅር፥ ድክመትን ከጥንካሬ፥ ደካማን ከኃይለኛ፥ ቀጣን ከታጋሽነት፥ ጭካኔን ከርህራሄ በአጠቃላይ የሰውን ልጅ ባህርያት ተቃራኒ መልኮች ውብት ባለው መልክ እያሳቀ፥ እያስገረመ፥ እያዝናና ግን በመልዕክቱ እያስተማረ የሚገኝ አንድ የማህበራዊ ግንኙነት (interaction) ገጽታ ነው። "ዋች"ም እንደ ሌሬ መታደምንና መቼትን ይጠይቃል፤ ጊዜ፥ ቦታና ሁኔታን ይሻል።

ከህብረተሰቡ ግንዛቤ ብንነሳ "ዋች" ከ"ሌሬ" የሚለይበት ባህርይ "የፈጠራ ሥራ":"ውሸት- እውነት"፥ "ሃሳብወለድ" መሆኑ አንዱ ሲሆን፥ ሌላው የመዋቅር (structure) ጉዳይ ነው። ከመዋቅር አኳያ ዋቾች ከሌሬ ሲነፃፀሩ ያጥራሉ። ብዙዎቹ ነጠላ ታሪኮቻቸውን የሚጨርሱት ባልተጠበቀ መንገድ ነው። እነዚህ የትረካ ዓይነቶች ለህይወትም ለዘመንም ግልጽና ቅርብ በመሆናቸው በተለይም በልጆች (በህፃናት) እና በወጣቶች ዘንድ ይበልጥ ተወዳጅነት ያላቸው ይመስላሉ። በጥቅሉ ሲታይ የዋች ዋና ተግባር ማዝናናት፥ ማስተማር፥ ማስገንዘብ፥

መምከር፣ ማስጠንቀቅ፣ የአእምሮ ቅልጥፍናና ንቃት ማስገኘት ሆኖ ነው የሚገኘው። ይህንንም ጥቂት ምሳሌዎችን በመውሰድ መመልከት ይቻላል።

ዝንጀሮና ዓይጥ አብረው በወዳጅነት እርሻ እያረሱ ሲኖሩ አንድ ቀን አይጥ ለዝንጀሮ ሃሳብ አቀረበች። ሃሳቡም "የረሃብ ጊዜ (ክፉ ቀን) ሲመጣ እንዳለፈው ጊዜ እንዳይቸግረን ዛሬ በደህናው ቀን እህል በጎተራ አከማችተን እናስቀምጥ" የሚል ነበር። ዝንጀሮ በዚህ ሀሳብ ተስማማ። አይጥም ዝንጀሮ በሀሳቧ የተስማማ መሆኑን እንዳወቀች "ታዲያ ጎተራው ከማን ጋር ይቀመጥ?" ስትል ጠየቀች። እሱም "ከእኔ ጋር ይቀመጥ" ለማለት ከበደው። ጥቂት አሰበና "ከአንች ጋር ቢቀመጥ ምን ችግር ይኖራል? በእኔ በኩል ካንች ጋር ቢቀመጥ ደስ ይለኛል።" አላት። እሷም "ጥሩ! ሊቀመጥ ይችላል" አለችና እንደገና ሌላ ጥያቄ አቀረበች። ይኸውም "የጎተራውን ቁልፍ ማን ይያዝ?" የሚል ነበር። ዝንጀሮም "አንች ልትይዥው ትችያለሽ። እኔና አንች እንተማመናለን። ስለዚህ ካንች ሆነ ከኔ ምን ለውጥ አለው?" አላት። በዚህ ጊዜ አይጥ ኮስተር ብላ "አይሆንም! ቁልፉ ካንተ እጅ መቀመጥ ይኖርበታል። ምክንያቱም ጎተራው ከእኔ ጋር እንዲሆን ከተስማማን ቁልፉ ከእኔ እጅ እንዲሆን ደግሞ መስማማት የለብንም። ስለዚህ ካንተ እጅ መቀመጥ ይኖርበታል!" አለችው።

ዝንጀሮም "እሺ! እኔ እይዛለሁ" ካለ በኋላ በስምምነታቸው መሰረት ጎተራውን ከአይጥ ጋሮ አስቀመጡ። ለአንድ ዓመት ቀለብ የሚሆናቸውን ያህል በቆሎም በጎተራው ሞልተው ቆለፉና ቁልፉን ዝንጀሮ ይዞ ሄደ። በዚህ ሁኔታ ለክፉ ቀን እንዲሆናቸው እህል በጎተራ አስቀምጠው ሲኖሩ ከዓመታት በኋላ በአገሩ ረሀብ መጣ - የሚላስ የሚቀመስ ጠፋ። በዚህ ጊዜ ዝንጀሮ ቁልፉን ይዞ ወደ ወዳጁ ቤት ወደ አይጥ ሄደ።

ኋላም "እንደምታይው ባገሩ ረሀብ ወርዷል። ልጆቼ በረሀብ ሳይሞቱብኝ ያስቀመጥነውን በቆሎ እንከፋፈል" አላት። እሷም "የዝንድሮው ረሀብ 'ረሀብ' ተብሎ ነው ወይ? ምንም ረሀብ ሊባል አይችልም። የሚበላ ነገር አልጠፋም። ተው - ቆጥበን እህሉን ብናቆየው የሚቀጥለው ዓመት የባሰ ሊሆን ስለሚችል ቀን ልንወጣበት እንችላለን" አለችው። ዝንጀሮ በአነጋገሯ በጣም ተጨነቀ። ተመልሶም ወደ ቤቱ ሄደ። ከቤቱ የሚበላ ነገር አልነበረውም። ስለዚህ ልጆቹ ራባቸውና "ምግብ አምጣ" እያሉ አለቀሱበት። ስለዚህ እንደገና በልጆቹ ሁኔታ በጣም ተጨነቀ። ቢያታልላቸውም ማልቀሳቸውንና "ምግብ አምጣ" እያሉ መጨቅጨቃቸውን ሊተው አልቻሉም። ስለዚህ ዝንጀሮ በጣም ግራ ተጋባ። ከዚህ በኋላ "አሁንስ የፈለገው ይሁን እንጂ ድርሻዬን ተካፍዬ አምጥቼ ልጆቼ በረሀብ ሳያልቁ ማብላት አለብኝ" ብሎ ወደ አይጥ ለመሄድ ወሰነ። በወሰነው መሰረትም ተመልሶ ሄደ። ከዚያም "ወዳጄ አይጥ! በቆሎውን ብንካፈል ይሻላል። ልጆቼ በረሀብ ሊያልቁ ነው። እና መካፈል ይኖርብናል።" በማለት አጥብቆ ለመናት። አይጥ ግን "ተው፣ የዘንድሮ ረሀብ 'ረሀብ' አይባልም፣ ለከርሞ ይቀመጥ..." በማለት ፈቃደኛ ልትሆን አልቻለችም።

ከዚያም "ፋንታህን የሚወስድብህ የለም። ቁልፉም በእጅህ ነው የሚገኝ። እሽ ብትልና ምክሬን ብትቀበለኝ ምን አለበት? ከርሞ የባሰ የረሀብ ዘመን ሊሆን ይችላል። የሚታወቅ ነገር የለም - ያን ጊዜ ምን ትበላለህ? ልጆችህን ምን ታበላለህ? ስለዚህ ማሰብ አለብህ እንጂ መቸኮል አይኖርብህም" አለችው።

እሱም በጣም ተጨንቀና "ለከርሞ ማስቀመጥ የሚቻለው ዛሬ የሚበላ ሲገኝ ነው። 'ልጆቼ እያለቀሱ ነው' እያልኩ እየነገርኩሽ ለምን አይገባሽም? ስለዚህ ዛሬ ተካፍለን ድርሻዬን መውሰድ አለብኝ" አለና አምርሮ ነገራት። አይጥ ግን ፈፅሞ "እሽ" ልትለው አልቻለችም። ስለዚህ ዝንጀሮ በጣም እያዘነና እየተበሳጨ አሁንም ወደቤቱ መመለስ ግድ ሆነበት። ከቤቱ ሲደርስም እንደተለመደው ልጆቹ በረሀብ እየተንጫጩ አገኛቸው። ልጆቹ

እሱን ሲያዩ ጨርሶ ረሀብ እየገረፋቸው "አባባ-አባባ-ምግብ ስጠን" እያሉ ማልቀስ ቀጠሉ::

ዝንጀሮ በዚህ ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለበት ጨርሶ ግራ ተጋባ:: ሁሉም ተቸግሯል:: እህል የሚያበድረው የለም፣ ስለዚህ በጣም እየተጨነቀ ሲያስብ ልጆቹ ደግሞ በሌላ በኩል እያለቀሱ ይጨቀጭቁታል:: በዚህ ሁኔታ ቀኑን ሊያሳልፈው አልቻለም:: ስለዚህ እንደገና ወደ አይጥ ቤት ተመልሶ በመሄድ "ዛሬ በፍፁም ድርሻዬን ይገባ መሄድ አለብኝ!" በማለት በቁጣ ጠየቃት:: እሷም "እምቢ-አይሆንም! ጎተራችን መከፈት የለበትም!" በማለት በጣም ተቆጣች::

እሱም በፍፁም "ድርሻዬን ካልሰጠሽኝ ተመልሼ አልሄድም" አለና አጥብቆ ያዛት:: በዚህ ጊዜ "ምን ትጨቀጭቀኛለህ! ቁልፉ የሚገኝ በእጅህ እኔን ለምን ትጨቀጭቀኛለህ" አለችው:: ኋላ ሄዶ ጎተራውን በቁልፉ ከፈተውና ያስቀመጡትን በቆሎ ቢመለከት አንድ ፍሬ እንኳን ለምልክት ሳያገኝ ይቀራል:: በዚህ ጊዜ ዝንጀሮ ራሱን ይዞ "ኡ!ኡ!ኡ!..." በማለት ጮኸና "በቆሎውን የት አደረስሽው?" አላት::

አይጥም ትስቅበትና እያሾፈች "ቁልፉ ያለው ካንተ እጅ! እንዴት 'የት አደረስሽው?' ብለህ ትጠይቀኛለህ?" አለችና በቁጣ "መጠየቅ ያለበት እኔ ወይስ አንተ?" አለችው::

"እንዴት እንደዚህ ትያለሽ? እኔስ ካለ ዛሬ ይህን ጎተራ ከፍቼ አይቸውም አላውቅ" በማለት ዝንጀሮ እንደገና ኡኡታውን አቀለጠው::

አይጥም "ቁልፉን በእጅህ ይዘህ 'በላችው' እያልክ ስሜን ልታጠፋ ነው?" በማለት ደነፋች:: ከዚህ በኋላ "ዝንጀሮ ለክፉ ቀን ይሆናል ብለን በጋራ ያስቀመጥነውን አንድ ጎተራ ሙሉ በቆሎ ክዶኝ በላ" በማለት ለእንስሳት "ጆ - ዶንጎ" (ለእንስሳት ጉባኤ) አመለከተች:: ከሰሰችው::

የእንስሳት ጆ-ዶንጎም አይጥ ያቀረበችውን ክስ ፍሬ ነገር አዳምጦ ምርመራ ቀጠለ:: ሆኖም ፍርድ ለመስጠት በጣም ተቸገረ:: ጆ-ደንጎ ፍርድ ለመስጠት የተቸገረበት ምክንያት "ምንም እንኳን ቁልፉ በዝንጀሮ እጅ ቢሆንም አይጥም ውስጥ ለውስጥ ጉድጓድ ቆፍራ ከጎተራው ውስጥ በመግባት በቆሎውን ልትበላው ትችላለች" በሚል ነበር:: በመጨረሻም፣ በዚህ ምክንያት፣ ጆ-ደንጎው ጥፋተኛውን ለመለየት መቸገሩን ለዝንጀሮና ለአይጥ ገለጠላቸው::

በዚህ ጊዜ አይጥ በፍጥነት "ጆ-ደንጎ በዚህ ምክንያት ጥፋተኛውን መለየት ካልቻለ ሁለታችንም ከጎተራው እንግባና እሳት ይንደድብን:: ከሁለታችን በህይወት የተረፈ ንፁህ ነው ማለት ነው" የሚል ሀሳብ አቀረበች:: "ዝንጀሮም ጥሩ ሀሳብ ነው፣ እስማማበታለሁ" አለ:: ከዚህ በኋላ ጆ-ዶንጎው ሁለቱን፣ አይጥና ዝንጀሮን፣ ከጎተራው ውስጥ አስገብቶ እሳቱን አያያዘው:: ግን እሳቱ እንደተያያዘ ወዲያው ኃይለኛ ዝናብ ወረደ:: አይጥም እሳቱ እንደተያያዘ በጎተራው ስር ቆፍራ በቆሎውን በበላችበት ጉድጓድ ሾልካ ገባች:: እሷ ወደ ጉድጓድ ስትገባ ዝናቡ እሳቱን ባንድ ጊዜ አጠፋው:: ዝንጀሮም በዝናቡ ኃይል እሳት ሳያገኘው ተረፈ:: አይጥ ግን በጉድጓዱ ሾልካ ልትወጣ አልቻለችም- አገሩን ያጥለቀለቀው ጎርፍ በጉድጓዱ ውስጥ ገባና ውሃ ጠጥታ ሞተች ይባላል:: (ተራኪ:- አጄሉ አባንግ፣ ፉኚዶ፣ ነሀሴ 4 ቀን፣1991)

የዚህ "ዋች" ትኩረት በእምነትና ክህደት ባህርይ ላይ ነው:: የተረቱ ባለታሪኮችም እንስሳት ናቸው:: ነገር ግን እነሱም ድርጊታቸውም በጥበብ ወክለው የቀረቡት የፈጣሪያቸውን የሰውን ልጅና ድርጊቱን ነው:: ከትረካው እንደምንረዳው ባለታሪኮቹ በመካከላቸው እምነትን ፈጥረው በወዳጅነት የሚኖሩ ነበሩ:: ያለፈውን የህይወት ዘመን በመረዳዳት እንዳሳለፉ ሁሉ፣ መጭውን አሳሳቢ ጊዜም በመተሳሰብ ሊቋቋሙ አቅደው ይዘጋጃሉ:: ይህ አሳሳቢ የሆነው የጋራ

ችግርም ባልታሰበ ጊዜ የሚደርስ ድርቅና ረሀብ ነው። "እንዳለፈው እንዳይቸግረን.." እያለች አይጥ ወዳጇን (ዝንጀሮን) ስትመክር እንደምናየው፥ በጥጋብ ዘመን በቅንጦት የሚባክነውን በመቆጠብ ለወደፊቱ ተዘጋጅተው ለመጠበቅ የሚስማሙትም ያለፈ ገጠመኛቸውን መሰረት በማድረግ ነበር። ምክሩ ተቀባይነት አለው፤ ስለሆነም አይጥ ያመነጨችው ሀሳብ የዝንጀሮን ልብ ይነካል። በህይወቱ ውስጥ ያለፈበት የረሃብ ፈተና ይታሰበዋልና። በመሆኑም በአይጥ ሀሳብ ተስማምቶ የሚመጣውን ክፉ ቀን ለመቋቋም እህል በጋራ ያስቀምጣሉ።

ነገር ግን አይጥ ወዳጇ ዝንጀሮ ሞኛ-ሞኝ፥ የዋህ፥ ተላላና በእሷ ላይ ሙሉን እምነት ያሳደረ ገራገር መሆኑን በሚገባ የምታውቅ ሆና እናያታለን። "ጎተራው ከማን ጓሮ ይቀመጥ?" በማለት ስትጠይቀውም ሊመልስ የሚችለውን አስቀድማ ገምታለች። "ካንች ጓሮ ቢሆን ደስ ይለኛል" ብሎ ሲመልስም "ጥሩ!" እንጂ ለትዝብት ያህል እንኳን "አይሆንም!" በማለት አታቅማማም። ድብቅ ዓላማዋ ጎተራው ከጓሮዋ እንዲቀመጥ ነበር። ይህን ካረጋገጠች በኋላ የጥርሟ ምንጭ ከሰሩ ይደርቅ ዘንድ ለእሱ ቁልፍ ታስይዘዋለች። አይጥም ይህን ሁሉ የምታደርገው ቀድሞ በነበረው የእምነት ከለላ ነው። ቁልፍ ካስያዘችው በኋላ ከቤቷ ወደ ጎተራው እየተመላለሰች የምትጠቀምበትን ጉድጓድ በትጋት ትምሳለች። በጊዜ ብዛት የተከማቸውን እህል እንደጨረሰችም የተፈራው የረሀብ ዘመን ይመጣል፥ ያንገላብባል። ድርጊቷን ጉድጓድ እንደደበቀው ሁሉ ዝንጀሮ "ተካድኩ" የሚል እሮሮና ብሶት ቢያሰማ በእጁ ባስያዘችው ቁልፍ አፉን ሊዘጋ እንደሚችል አስቀድማ ስለተዘጋጀች፥ ረሀቡ እየከፋ ሲሄድ፥ እሱ ያስቀመጠውን እህል ተስፋ አድርጎ ድርሻውን ለመውሰድ ሲወተውት፥ አይጥም ጎተራው እንዳይከፈት ልዩ ልዩ ሰበቦች ስታቀርብ ከቆዩ በኋላ "ቁልፉ ያለው ካንተ እጅ፤ እንዴት የት አደረስሽው ብለህ ትጠይቀኛለህ?... መጠየቅ ያለበት እኔ ወይስ አንተ!?" በማለት ትሳለቅበታለች። ወዲያውም ለ"ጆ-ዶንጎ" (ለእንስሳት ጉባኤ) በክህደት ወንጀል ትከሰዋለች።

ይህ በእንስሳቱ ተመስሎ የቀረበው ድርጊት በዕለት ተዕለት የሰው ልጆች ማህበራዊ ግንኙነት ሂደት ውስጥ የሚፈፀም (የምናየው) እውነታ ነው። እንዲህ ባሉ "ቀኞች" እኙዋዎችም እምነት ክህደትን እንዴት እንደሚመለከቱት ዝንጀሮ ከሞት ባመለጠበትና በአይጥ ላይ በደረሰው የመጨረሻ ዕጣ አማካይነት መረዳት ይቻላል። ዕጣውም ከአይጥ ባህርይና ድርጊት የመነጨ ነው። የእንስሳቱ ጆ-ዶንጎም ለፍርድ የሚቸገረው ከዚሁ ከአይጥ ባህርይና ድርጊት በመነሳት ይሆናል። እንደምናየው አይጥ የዝንጀሮን ችሎታና እውቀት ብቻ አይደለም ቀድማ የሄደችው-የመላውን እንስሳት ጉባኤ አስተሳሰብ ጭምር እንጂ! የእንስሳቱ ጉባኤ ልታደርግ የምትችለውን ጉድጓድ የመማስ ሥራ ባህርይዋን ከመማለጹ በፊት በእሳት መፈተንን እንደመፍትሄ ሀሳብ በራሷ አነሳሽነት በፍጥነት ስታቀርብ ግፉ ቢል እሳት ዝንጀሮን እንጂ እሷን ሰለባ ሊያደርግ እንደማይችል በልቧ በማረጋገጥ ነው። ሁለቱ ግብተው እሳቱ ሲያያዝ፥ እሷ በጎተራው ስር በቀደደችው ጉድጓድ ውስጥ አፈትልካ እንደምታመልጥ ይታያት ነበር። አይጥ እንደምታመልጥ እርግጠኛ ነበረች። ሆኖም በእኙዋዎች የህይወት አተረጓጎም ተፈጥሮም በቀውስ ውስጥ ባልቃ ገብታ የራሷን ሚና ትጫወታለች። ትበይናለች። ስለዚህ ዝናብ በቅጽበት ወርዶ፥ እሳቱ ጠፍቶ፥

ዝንጀሮ ከሞት ተርፎ፥ አይጥ በቆፈረችው ጉድጓድ በኩል በገባ ጎርፍ ዶፍ ተውጣና፥ ውሃ ጠጥታ ትሞታለች። ዝንጀሮን ግን ተፈጥሮ የምትክሰው፥ ሊደጋየው እንደነበረው እሳት ሁሉ ድርቁንም አብራ በዝናብ በማጥፋት የወደፊት ዕድሉን በማቃናት፥ ተስፋውንም በማለምለም ጭምር ነው።

ስለዚህ ከላይ ከቀረበው ትረካ የምንረዳው የባህሉ ባለቤቶች በእምነትና በክህደት ላይ ያላቸውን ግልጽ አመለካከት ይሆናል። እናም እምነት ድንቅ የሆነ የህብረተሰቡ ስነምግባር ሆኖ ሲቀርብ ታማኞች ደግሞ ከብዙ ፈተናና ችግር ሊያመልጡ እንደሚችሉ ያስገነዝባል። በተቃራኒውም ክህደት ውድቀት፥ ጥፋትና ሞት መሆኑን ያስተምራል።

ቀጥለን ደግሞ የምንመለከተው የ"አቾክ"ን ታሪክ ይሆናል። በአኙዋ ባህል ውስጥ አቾክ የማይናቅ ሚና እንዳለው ይገመታል። አቾክ እንደ አረቡ ነስረዲን በስሙ ብዙ ቀቾች ይተረካሉ። የሚወክለውም ተንኮልን፥ ክፋትን፥ ሳቅን፥ ማዝናናትን... ነው። በአጠቃላይ የቃሉ ትርጉም "ተንኮለኛ" ማለት ሲሆን በእርግጥም በብዙዎቹ ታሪኮች ውስጥ እንደሚታየው አቾክ በባህሪው እጅግ በጣም ቀልጣፋና ብልጥ ነው። የሚደርስበትና የሚጨብጠው የለም። እሱን የሚመለከቱ በርካታ ታሪኮች እንደሚያሳዩን "አቾክ" የፈጠራ ችሎታው እጅግ በጣም የሚደነቅ፥ በሰዎች ላይ ተንኮል በመስራት ደስታና ሀሴትን የሚገበይ ፍጡር ነው። ሰዎችን በማሞኘት የሚደሰተውን ያህል መልሶ ይከፋል። ነገር ግን በመከፋት ስሜቱ ተነሳስቶ ሌላ የተንኮል ወጥመድ ይዘረጋል። የሚከተለውን "ቀች" እንመልከት።

> አቾክና ሌሮ አብረው ይኖሩ ነበር። አንድ ቀን አቾክ ሌሮን "ወይ የአንተ እናት ወይም የእኔ እናት አንዷቸው ች-ጆክ ናቸው እየተባለ በአገሩ ይታማሉ። ነገሩ እውነት ከሆነ ለኔም ለአንተም አሳፋሪ ነገር ነው። ስለዚህ "ች ጆክ" ከውሃ ሲጥሉት ይዘግጣል። "ች-ጆክ" ያልሆነ ደግሞ ይንሳፈፋልና አንተም የራስክን እናት እኔም የራሴን እናት በቆዳ ጠቅልለን፡ አስረን፥ ተሸክመን፥ ወስደን ባህር ላይ እንጣላቸው። ከዚያ የምትንሳፈፍዋ ንፁህ ናት ማለት ነው" ይለዋል።
>
> ሌሮም በድንጋጤ "ች-ጆክ ናቸው እየተባለ ይታማሉ! በጣም የሚገርም ነገር ነው። እኔ የት ሰምቼ! የሚያሳዝን ነገር ነው! በል እንግዲያው አንተ እንዳልከው ወስደን ጥለን ቁርጡን ማወቅ አለብን" በማለት በአቾክ ሀሳብ ይስማማል። ከዚያም አቾክና ሌሮ እናቶቻቸውን በቆዳ ጠቅልለው፥ በገመድ አስረው፥ ባህር ላይ ጥለዋቸው ተመለሱ። ወዲያው አቾክ "በል እኔ እቾኩሳለሁ" በማለት አቅጣጫውን ቀይሮ እየሮጠ ሄደ። ሌሮም ወደቤቱ ጉዞውን ቀጠለ።
>
> አቾክ እናቱ እንድትንሳፈፍ አድርጎ ከቀላል ደረቅ እንቋ ግንድ ጋር አስሮ ነበር ከባህር የጣላት። ስለዚህ ከሌሮ ከተለየ በኋላ ተመልሶ ወደ ውሃው በችኮላ ተመለከተ። የሌሮ እናት ዘቅጣለች። የእርሱ እናት ግን በደረቁ እንቋ እማካይነት ትንሳፈፋለች። ምንም አልሆነችም። ስለዚህ እየዋኘ ወደ ውሃው ገብቶ አወጣትና ሌሮ ከማያውቀው ስውር ቦታ እንድትኖር አደረገ።
>
> ሌሮ እናቱን ወደ ውሃው ከጣለበት ቀን አንስቶ ረሀብ ያዘው። ምግብ የሚሰጠው የለም። እሱ ሲቸገርና ሲርበው አቾክ ግን እናቱ እየመገበችው እያማረበትና እየታደሰ መኖር ቀጠለ። በዚህ ጊዜ አቾክ ደስተኛ የመሆኑ ምክንያት ያልገባው ሌሮ "አንተ ራበኝ ስትል ሰምቼ አላውቅም። እያማረብህ ነው። እኔ ግን በረሀብ ልሞት ነኝ። ምግብ

> ማን ይሰጥሃል? የት ነው የምታገኘው?" እያለ እዘውትሮ መጠየቅ ጀመረ። አቾክም "ፍራፍሬና ስራስር እየለቀምኩ እበላለሁ። አንተስ ለምን እንደኔ እየለቀምክ አትበላም?" በማለት መለሰለት። ፍራፍሬና ስራስር ግን የት እንደሚገኝ ሊነግረው አልፈለገም ነበር። ስለዚህ ሌሮ "ከእንግዲህ ከአንተ አልለይም። ከምትሄድበት ቦታ ሁሉ አብሬ እየዞርኩ ከምትበላው እበላለሁ እንጂ እኔ ምግብ ሳገኝ አልቻልኩም" ይለዋል።
>
> ከዚህ በኋላ ሌሮ አቾክን እየተከተለ ሊለቀው አልቻለም። አንድ ቀን ከመንታ መንገድ ላይ ሲደርሱ አቾክ አንደኛውን አቅጣጫ ይዞ ሄደ። ሌሮም ተከተለው። የአቾክ ውሻ ግን ሌላውን መንታ መንገድ ይዞ መሄዱን ቀጠለ። አቾክም ውሻውን ቢጠራው-ቢጠራው ዝም ብሎ መንገዱን ቀጠለ። በዚህ ጊዜ ሌሮ ይጠራጠራል። ጥርጣሬውም "አቾክ ሁልጊዜ እየሄደ ምግብ የሚያገኝበት መንገድ አሁን ውሻው የሄደበት መንገድ መሆን አለበት እንጂ ውሻው ከጌታው ተነጥሎ አይሄድም ነበር" የሚል ነው። ስለዚህ ሌሮ ውሻውን ተከተለና ደረሰበት። ውሻው እየመራ እሱ እየተከተለ ሲሄድ-ሲሄድ የአቾክ እናት ካለችበት ስውር ቦታ ደረሰ። በዚህ ጊዜ ሌሮ በጣም ተናደደ። "ለካስ የእኔ እናት እንድትሞት በመፈለግ ኖሯል 'ች-ጆክ' ናቸው እናቶቻችንን ከውሃ እንጣላቸው ያለኝ" አለና በመናደድ የአቾክን እናት በዘንዘና ራሷን መታት። ሞተች። እሱም በሁለት እጇ ዱቄት አስጨብጧት ጠፋ።---[9]

ታሪኩ ረጅም ነው። በመሆኑም ሌሮ የአቾክን እናት ገድሎ እንደሄደ አቾክ ይመጣል። በመጀመሪያ እናቱን እንቅልፍ የወሰዳት እንጂ የሞተች አልመሰለውም ነበር። ስለዚህ ምግብ እንድትሰጠው ሲጠራትና መልስ አላገኝ ሲል ሲነካካት እናያለን። በመጨረሻ መሞቷን ያረጋግጣል። መሞቷን ቢያረጋግጥም አያለቅስም። ይልቁንም አቾክን የምናየው የሞተችው እናቱ በእጇ የጨበጠችውን ዱቄት እየቃመ ሌላ ተንኮል ሲያውጠነጥን ነው። ይኸውም የእናቱን አስከሬን ህዝብ ወደሚተላለፍበት መንታ መንገድ ወስዶ፥ ከግንድ አስደግፎ በማቆም፥ ሰዎችን በገዳይነት በመክሰስ "በክወር" ካሳ የሚያገኝበትን ሁኔታ መዘየድ ነው። አቾክ ባቀደው መሰረት የእናቱን አስከሬን ከመንታ መንገድ ዳር ከሚገኝ አንድ ግንድ አስደግፎ በማቆም ሲጠባበቅ ከሩቅ ሁለት ልጃገረዶች በቅል ውሃ ቀድተው ተሸክመው ሲመጡ ያያል። ኋላም ልጃገረዶችን ግንዱን "ተደግፋ ለቆመችው" አሮጊት ውሃ እንዲሰጧት በትህትና ይጠይቃቸዋል። ኮረዳዎቹ "ለሴትዮዋ" ውሃ ለመስጠት እንደቀረቡ "ጆሮዋ አይሰማም!" ይሏቸዋል። በዚህ ጊዜ "ውሃ ጠጪ" እያሉ ሲነኳት ከተደገፈችበት ግንድ ተንሸራታ ትወድቃለች። ከዚህ በኋላ "እናቴን ገደሏት" በማለት ለጆ-ደንጎ ክስ ያቀርባል። ከዚያም ልጃገረዶቹ እንደ ገዳይ ተቆጥረው በ"ክወር" ህግ፥ በካሳ መልክ፥ ለአቾክ አገልጋዮች እንዲሆኑ ሲፈረድባቸውና በመጨረሻም ከሌሮ ጋር ሰማነው ተሰፋ ሲያስቀርጡት፥ ሲበቀሉት፥ ታሪኩ ያሳየናል።

ከዚህ "ዋች" የምንገነዘባቸው በርካታ ባህላዊ ጉዳዮችና ማህበራዊ ቁምነገሮች አሉ። አንዱ የተረሳ መነሻ የሆነው የእምነትና የአመለካከት ጉዳይ ነው። ይኸውም "ች-ጆክ" የሚለው

---

9 ተራኪ ኒግዎ ጊራ፥ ለደጫ 87፥ ጋምቤላ፥ የካቲት፥ 1990

እምነት አንዱ ነው። በአኙዋ ህብረተሰብ "ች-ጆክ" እጅግ በጣም የሚፈራ የእምነት ገጽታ መሆኑን ታሪኩም ይነግረናል። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የቃሉ ፍች "የጆክ ማስት" ማለት ነው። በአኙዋች እምነትና አስተሳሰብ "ች-ጆክ" የህመም፥ የችግር፥ የድህነት፥ የአብደት፥ የስርቆት፥ የውሸት፥ በአጠቃላይም የሞትና የጥፋት ምንጭ ተደርጎ ይታያል። አንድ ሰው በበሽታ ከተያዘ "ች-ጆክ" ይዞት ነው ይባላል። አንድ የህብረተሰቡ አባል "ች-ጆክ" ሆኗል ሲባል ደግሞ ሰዎችን ይገድላል፥ ያሳምማል፥ ያሳብዳል፥... ማለት ነው። በዚህ ምክንያት ህብረተሰቡ የራሱን የመከላከያ ልማዳዊ ዘዴ የዘረጋ ይመስላል። አቸክ ሌሮን በታሪኩ መነሻ ላይ የሚነግረው "ወይ የአንተ እናት ወይም የእኔ እናት ከሁለቱ አንዳቸው 'ች-ጆክ' ናቸው እየተባለ በአገሩ ይታማሉ።" በሚል ሲሆን ሌሮም ሲያቅማማ እናየውም። እናም "እሺ!" በማለት ወዲያው በድንጋጤ እናቱን ወደ ውሃ ይጥላል። በእርግጥ ድርጊቱ ከባህሉ ውጭ ላለ ሰው ቀላል ሊመስል ይችላል። ለአኙዋዎች ግን ከእምነትና ከአመለካከት የመነጨ ከባድ ቁምነገርን ያዘለ ነው። አቸክም ይህን በህብረተሰቡ ውስጥ ስር የሰደደ ልማዳዊ ዘዴ ነው ሲጠቀምበት የምናገኘው። የተረቱ ስነጥበባዊ ዋጋም የተመሰረተው በዚሁ በህብረተሰቡ የቆየ እምነት፥ አስተሳሰብና አሠራር ላይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ልማዳዊ በሆነው በህብረተሰቡ የ"ክወር" ህግ መሠረት አቸክ ሁለት ልጃገረዶችን ካሳ ሲቀበል እናያለን። "ክወር" በዚህ "ዋች" ውስጥ ብቻ አይደለም ተጠቅሶ የምናገኘው። በጣም በርካታ በሆኑ በተለያዩ የአኙዋ ተረቶች ውስጥም የተለያዩ ግጭቶችን ለማስወገድ በተለያዩ ገፀ ባህርያት ሲታቀድ፥ ሲከሽፍና ሲሳካ እናያለን።

እንደ ማንኛውም ተረቶች የአኙዋ ተረቶችም የእንስሳት ገፀ ባህርያት አሏቸው። እንስሳቱ እንደ ሰው ያስባሉ። እንደ ሰው ይግባባሉ። ያቅዳሉ። ይጣላሉ። ይስማማሉ።... የእንስሳት ባህሪ ይዘው ከሚቀርቡ ከእነዚህ የአኙዋ ተረቶች መካከል አብዛኞቹ "ዋች" ሲሆኑ በግዙፍነት፥ በአስፈሪነትና በኃይለኛነት የሚታወቁትን እንደ አንበሳ ያሉትን የዱር አራዊት እንደ አይጥና እንደ እንቁራሪት ያሉ ደካማ ፍጡራን ሲፈታተኗቸው፥ ሲያሸንፏቸውና፥ ሲቀልዱባቸው እናያለን። ምንም እንኳን ታሪኮቹ በእንስሶች ድልና ሽንፈት ይመሰሉ እንጂ አፈጣጠራቸው፥ ዘልውናቸውና አገልግሎታቸው ለማህበረሰብ ብቻ የተወሰነ ነው። በእርግጥ ሰዎች እንስሳትን በፈጠራ ቅንጅት ውስጥ የሚጠቀሙባቸው መሠረታዊ የሆኑ ውጫዊና ውስጣዊ ምክንያቶች ይኖራሉ። ከእነዚህ መካከል አንዱ የሰው ልጅ ገጠመኝና ፍላጎት በፈጠራ አማካይነት ቅርጽና ውበት ይዞ ሲቀርብ የሚያበረክተው መንፈሳዊ እሴት ዋጋው ከፍተኛ ሆኖ ስለሚገኝና ስለሚመረጥ ሊሆን ይችላል። የአኙዋ ዋቾችም እንዲህ ያሉ ሆነው በተምሳሌያዊነት ህይወትን የማሳየት ኃይላቸው ከፍ ያለ ሆኖ ይገኛል። ለምሳሌ "የፍሮንና የአንበሳን" ታሪክ እንመልከት።

> አንበሳና ፍሮ በአንድ መንደር ይኖሩ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን አንበሳ የፍሮን ቤት "የእኔ ነው እና ልቀቂልኝ" ይላታል። ፍሮም "እንቢ!" እንዳትል አቅሟ አይፈቅድላትም። "እሺ!" እንዳትል መጠለያ የላትም። ቤቱም የእርሷ እንጂ የአንበሳ እንዳልሆነ ታውቃለች። ስለዚህ ምን መልስ መስጠት እንዳለባት እያወላወለች ከቆየች በኋላ "ለምን ጆ-ዶንጎ አይፈርድልንም?" አለችው። እሱም "እሺ! ይፈረድ ጆ ዶንጎ"

በማለት ወደ ጆ-ዶንጎ ይሄዳሉ።

ጆ-ዶንጎም ቤቱ የፍሮ መሆኑን ያውቃል። ግን "ቤቱ የፍሮ ነው" ብሎ እንዳይፈርድ አንበሳን ፈራና በነገ ዛሬ ቀጠሮ ከነገሩ መራቅ ፈለገ። በነገ ዛሬ ቀጠሮ ጉዳዩ ውሳኔ ሊሰጠው አልቻለምና ነገሩ ፍሮን አሳዘናት። ምክንያቱ ገብቷታል። ስለዚህ "ምን ባደርግ ይሻለኛል?" እያለች ስታስብ፣ ስታወጣ ስታወርድ ከቆየች በኋላ አንድ ዘዴ ብልጭ አለላት። ዘዴውንም ለአንበሳ ልትነግረው አሰበች። በኋላም "አንበሳ! ጆ-ዶንጎ አንተን ያህል ታላቅ ጀግና ይኸውና እያጉላላ ነው። ይሰጠው ወይም አይሰጠው ብሎ እንኳን መፍረድ አልቻለም። ከዚህ ሁሉ በነገ ዛሬ ቀጠሮ ከመጉላላት ለምን በደኑ ውስጥ ባለው ደረቅ ሳር ውስጥ ገብተን እሳት ለቀንበት ወይም ከእኔ ወይ ካንተ ከእሳቱ ቃጠሎ በህይወት የተረፈ ቤቱን አይወስድም?" አለችው። አንበሳም በአንድ ጊዜ ፍሮን እሳቱ እርር-ኩምትር ሲያደርጋት ታየውና በሀሳቧ ተስማማ። ከደኑ ውስጥ ገብተውም እሳቱን አያያዙት። በዚህ ጊዜ ፍሮ ለካስ አስቀድማ ጉድጓድ ጭራ ኖሮ ከጉድጓዷ ውስጥ ገብታለች። አንበሳ ግን ዙሪያውን በተያያዘ ቃያ ተለብልቦ ሞተ። ፍሮም ከቤቷ ውስጥ ገብታ በሰላም ኖረች ይባላል።

እንደምናየው የተረቱ ዋነኛ ትኩረት "ሰውን ትንሽ ነው ብለህ አትናቅ" ወይም "ናቂ ወዳቂ" በሚለው በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ በሚያጋጥም ተመሳሳይ እውነታ ላይ ነው። ብርቱ ደካማውን፣ ባለጊዜው "ጊዜ ባለፉ" ባዩን ይበድላሉ። በአንፃሩም እውቀት፣ ዘዴና ብልሃት በማይጠበቅ ሁኔታ በተፈጥሮም ይሁን በተገብሮ የመጣን "ብረታት" ና "ገናንነት" ሲያሟሽሹት መታየቱ የእውነተኛው ዓለም ክስተቶች ብቻ ሳይሆኑ ምስክሮችም ናቸው። ታዲያ እነዚህ የፈናጀርቱ እውነታዎች (incongruities) በሰው ልጅ የፈጠራ ኃይል የእንስሳት ባህርይ ወርሰው ወይም ተመስለው ቀርበዋል። በመሆኑም አንበሳ በአንባገነንነት ፍሮን ከቤቷ እንድትለቅ ይጠይቃል። ፍሮ አንበሳን በጉልበት የምትወጣው አይደለችም። ግን ተፈጥሮ ለእርሱ የነሳቸውን ለእርሷ ለግሳለች። ይኸውም ዕውቀት ነው። በቅድሚያ ፍሮ የህግን ጥላ ታስባለች። ሆኖም አንበሳ በነገሰበት ዓለም ህግ ከእርሷ ጎን ሊቆም አይችልም። ይህን ስላወቀች "ለችግሩ እኛው መላ እንምታ" ትላለች። አንበሳ አላመነታም። ፍሮ እንደተገነዘበችው ሁሉ ፍላጎቱ በጉልበቱ ይረጋገጣል። የእርሱ "ዕውቀት" ይህ ነውና። ስለዚህ ፍሮ "ጉዳዩን ህግ ይመልከተው" ወይም "ከእሳቱ የተረፈ ቤቱን ይውሰድ" ስትል አንበሳ ህጉ ሊያዘነብል ቢችል በእርሷ፣ እሳቱም ሊፈጅ ቢችል እርሷን እንጂ በእርሱ ላይ ሊሆን እንደማይችል በሙሉ ልብ ይተማመናል። እንዲሁም ፍሮ የጉድጓድ ጠቢብ መሆኗን "የብርታቱ" መጠን አይደርስበትም። በመጨረሻም እርሷ በዘየደችው መንገድ ስታመልጥ እርሱ በግብዝነቱ የእሳት ሰለባ ይሆናል።

በአጠቃላይ በአኙዋዎች አመለካከት አካላዊ ጥንካሬና ግዝፈት የአእምሮ ብስለትንና የእውቀት ችሎታን የሚያመለክቱ አይመስሉም። ለምሳሌ ከላይ የተመለከትነው "የአንበሳና የፍሮ" ታሪክ በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጥሎ በቀረበው "የዝሆንና የእንቁራሪት" ውርርድም እንደዚሁ በሰው ልጆች መካከል ሊኖር የሚችልን፣ በአካል ግዝፈትና በመንፈስ ጥንካሬ መካከል ያለን ልዩነት መሠረት ያደረገን የአኙዋዎች አመለካከት አጉልቶ የሚያስረዳ ነው።

ከዕለታት አንድ ቀን ዝሆንና እንቁራሪት ከወንዝ ዳር ይገናኛሉ። ዝሆን ውሃ ጠምቶት እየተራመደ ወደ ወንዝ ሲጠጋ በእግሩ ሊጨፈልቃት ሲል እንቁራሪት ዘልላ ትሸሽና "ምነው አቶ ዝሆን? ምንም እንደ አንተ ተራራ ባላክል በችሎታ ልበልጥህ እችል ይሆናል። ልትረግጠኝ አይገባህም" አለችው።

እሱም በአነጋገሯ በጣም ተገርሞና በግዙፍነቱ ኩራት እየተሰማው አዘቅዝቆ እያየ "በችሎታ ልበልጥህ እችላለሁ አልሽ?" በማለት ሳቀባት።

እርሷም "አዎ! በችሎታ ቀርቶ በአካልም ቢሆን እንደምበልጥህ መረዳት አለብህ" አለችው። በዚህ ጊዜ ዝሆን ተናደደ። "ምንድነው የምትቀባጥሪው?! አቅምሽን እንኳን አታውቂም? እኔና አንቺ በምን መመዘኛ እንወዳደራለን?" አላት። ኋላም "በይ - በይ አሁን ከፊቴ ጥፊ! ጠምቶኛል፤ ውሃዬን ልጠጣበት!" ይልና ሊጠጣ ወደ ውሃው ሲጠጋ "እንግዲያው በአካልም ሆነ በእውቀት ከእኔና ከአንተ ማን እንደሚበልጥ ለማወቅ ከፈለግህ እሁኑኑ እንወራረድ" አለችው። ዝሆንም "ጤነኛ አይደለሽም እንዴ? እኔና አንቺ በምን መመዘኛ ልንወራረድ እንችላለን?" አላት ይበልጥ በመናደድ።

እሷም "ቀላል ነው። ይልቅስ አትናደድ። በዚህ ውሃ እንወራረድ። ከእኔና ከአንተ ውሃ ጠጥቶ ቀድሞ የጠገበ ተሸናፊ ይሆናል ማለት ነው። እኔ አስቀድሜ ከጠገብኩ እኔ እውነትም ከአንተ ያነስኩ ደካማ ፍጡር ነኝ ማለት ነው። አንተ አስቀድመህ ከጠገብክ ከእኔ አንተ ደካማ ፍጡር ነህ ማለት ነው። ስለዚህ ሩቅ ሳንሄድ ውሃ በመጠጣት ችሎታ እንኳን አሁኑኑ ተወዳድረን ልንፈታተን እንችላለን።" አለችው።

ዝሆንም "እረ ተይ! በውሃ ተተርትረሽ ትሞቻለሽ። የእኔ ሆድ የሚቋጥረውን የአንቺ ሆድ እንዴት ትችላለች? አበድሽ እንዴ?" ይላታል። እንቁራሪትም "እረ-እረ!! ያበድክስ አንተ ነህ! 'ግዙፍ ነኝ' ብለህ ራስህን ስለምትገምት ነው'ኮ እንዲህ በማለት ንቀት የምታበዛ! ደግሞስ እኔ ከአንተ እንደማንስ ወይም እንደማላንስ ማወቅ የምትችለው ስንወራረድ ብቻ ነው። ይልቅ መጠጣት እንጀምር!" አለች።

በመጨረሻ ሁለቱም ውሃውን መጠጣት ጀመሩ። ዝሆን ውሃውን ሲጨልጥ እንቁራሪት ግን በሰፊ ቅድ አፏ መልሳ እያፈሰሰች የምትጠጣ መስላ የዝሆንን ሁኔታ በጎሪጥ ታያለች። ዝሆንም ካፈርኩ አይመልሰኝ በማለት ውሃውን ከአቅሙ በላይ በመጠጣት ተተርትሮ ሞተ ይባላል።

የተረቱ ቁምነገር ለራስ ያልሆነ ግምት መስጠት ግብዝነትና ከንቱነት መሆኑን በመጠቆሙ ላይ ነው። ለራስ የሚሰጥ ከንቱ ግምት በእውነታው ዓለም የሚታይ የሰው ልጅ ደካማ ባህርይ በመሆኑ እኙዋዎችም እነዚህን በመሳሰሉ በርካታ ሆቾች ይቆጣጠሩታል ማለት ነው።

1.1.3 **እንጋዴ፡-** ከላይ ከተጠቀሱት ከ"ሌሬ" እና ከ"ዋች" በተጨማሪ እኙዋዎች "እንጋዴ" (Angade) በሚል የሚጠቀሙበት የትረካ ዓይነት መኖሩ ከመነሻው ላይ ተጠቅሟል። "እንጋዴ" ብዙ ቁጥርን ያመለክታል። መሰረታዊ ቃሉ "እንጋዶ" (Angado) ነው። "እንጋዶ" "ሀሳብን በምሳሌ ማቅረብ" እንደማለት ነው። ከቃሉ ፍች መረዳት እንደሚቻለው "እንጋዶ" ቢያንስ ሁለት ነገሮችን አጣምሮ ያቀርባል - አንዱ "ሀሳብ" ተብሎ የተጠቀሰው ሲሆን ሁለተኛው በኢርቱዕም ሆነ በርቱዕ መንገድ ያን ሀሳብ ለመግለፅ ተያይዞ የሚነገረው "ምሳሌ" ነው። ምሳሌዎቹ

ለርዕሶቹ አስረጅነት ያላቸው ተመሳሳይ ገጠመኞች ናቸው፡፡ ቅርፃቸውም የተረት ሆኖ ይገኛል፡፡ በእርግጥ በቅርጽ ረገድ በአብዛኛው አጫጭር ናቸው፡፡ ከማጠራቸው ሌላ ርዕሶቻቸው ከ"ሴሬ" እና ከ"ዋች" የተለዩ ናቸው፡፡ የአንጋዱን ርዕሶች ልዩ የሚያደርጋቸው ምሳሌያዊ አነጋገር (proverbs) የመሆናቸው ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ የምሳሌው አጭር አስረጅ ትረካ ተነግሮ ሲያበቃ በአብዛኛው መደምደም ያለበት እንደገና ርዕስ ሆነው በእነዚሁ በቀረቡት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ነው፡፡ በምሳሌነት አንድን ዋና የመነጋገሪያ ነጥብ ወይም ሀሳብ ለመግለጽ የሚቀርቡት እነዚህ "አንጋዴ" ተብለው በአኙዋዎች የሚታወቁት አጫጭር ተረቶች እንደ ተረትነታቸው "ከእለታት አንድ ቀን"፣ "በድሮ ዘመን"፣ ...ወዘተ በሚል ትረካ ይጀምራሉ፤ ገጸ ባህሪያትን (እንስሳትን ወይም ሰዎችን) ያሳያሉ፣ ድርጊት (ሴራ) አላቸው፣ ታሪኩንም ዳይዳክቲቭ በሆነ መንገድ ያቀርቡታል፡፡ ስለዚህ አንጋዴዎች ርዕሶቻቸውና መዝጊያቸው ምሳሌያዊ አነጋገር÷ ባህርያቸው ደግሞ ተረት የሆነና በተወሰነ የግንኙነት አጋጣሚ የሚነሱ ትረካዎች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ "አንጋዶ" ምሳሌያዊ አነጋገርን ከተረት አዋህደው እንደሚያቀርቡ ሁሉ "ሴሬ" እና "ዋች" የሚያተኩሩባቸውን ባህላዊ፣ ታሪካዊና ማህበራዊ ጉዳዮችንም ጠምረው ያንፀባርቃሉ፤ ታሪክን ያስታውሳሉ፤ እምነትንና ልማድን ያነሳሉ፣ የዕለት ተዕለት ግንኙነትን ይጠቅሳሉ፡፡ በዚህ ረገድም በህብረተሰቡ ውስጥ የወል ሚና ይዘው ይጫወታሉ ማለት ነው፡፡ ይኸውም እንደ "ሴሬ" ባህልን ይጠብቃሉ፤ ያስርፃሉ፤ ታሪክንና ልማድን ያስተምራሉ፤ እንደ "ዋች" ደግሞ ክፉውን ከደግ ያሳያሉ፣ ምግባርን ይቆጣጠራሉ፣ ያዝናናሉም፡፡ እንደ "ሴሬ" ሁሉ አንጋዴን ለመተርጎም ባህላዊና ማህበራዊ አውዱን ገባ ብሎ መረዳትን ይጠይቃሉ፡፡ ይህን ከሚከተሉት ጥቂት ምሳሌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

"አኬኖ አቶው ኮ አማሪ" (Akeeno Athow Ko Omari) ይህ የአንጋዶው ርዕስ ምሳሌያዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ "አኬኖ ከእንጀራ እናቷ ልጅ ጋር ተቀበረች" እንደማለት ነው፡፡ ከዚህ ርዕስ ቀጥሎ ተረቱ እንደሚከተለው እጅግ በጣም በአጭሩ ይነገራል፡፡

በድሮ ዘመን አኬኖ የምትባል ወጣት ነበረች፡፡

አኬኖ የእንጀራ እናቷን ልጅ ወደደችና ሲታመም

ታመመች፤ ሲሞትም አብራው ተቀበረች፡፡ "አኬኖ ከእንጀራ እናቷ ልጅ ጋር ተቀበረች" እንደተባለ ሁሉ ..." በሚል ተናጋሪው መጀመሪያ ወደተነሳበት ነጥብ ይመለሳል፡፡ በእርግጥ ከባህሉ ውጭ ለሆነ አዳማጭ "አንጋዶ"ው የሚሰጠው ስሜት ደብዛዛ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ከአኙዋዎች ባህል ጋር ትውውቅ ላለው ወይም አውዱን ለተረዳ ሰው ትርጓሜው ግልጽ ነው፡፡ የህብረተሰቡን ህይወት ነው በጥልቀት የሚነካው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው አንድ አኙዋ በርካታ ሚስቶች(Cowives)ይኖሩታል፡፡ በዚህ መሰረት አኬኖ ከአንደኛዋ ሚስት የተወለደች ስትሆን የወደደችውና አብራው ሙታ አብራው የተቀበረችለት የአባቷ ልጅ ግማሽ ወንድሟ "አማሪ" (omari) ነው ማለት ነው፡፡ ይህን ዓይነቱን የአኬኖን ድርጊት ባህሉ አይቀበለውም፡፡ ከእናቷ ባይወለድም እንኳን የእንጀራ እናቷ ልጅ አብሮ አደጓ ወንድሟ ነው÷ በአኙዋዎች ስነምግባር፡፡ የአንጋዶው ማህበራዊ ዋጋም ይህን ልማድና ስነምግባር ማስጠበቅና

ከአኬና ባህርይ ጋር ተዛማጅ ሆኖ የሚታይን ድክመት ሁሉ መንቀፍ ይሆናል:: አንጋዶ በምሳሌያዊ አነጋገርነቱና በተረትነቱ በአኙዋዎች ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያለው መስሎ ነው የሚታየው:: ምክንያቱም ባህሉ የማይፈቅዳቸውን አፈንጋጭ አዝማሚያዎችና ድርጊቶች ይገስፃል፤ የሚደግፋቸውን በአርአያነት ያሞግሳል፤ ልዩነቶችንም (ቅራኔዎችን) ለመፍታት ይገለገልባቸዋል:: አንጋዶ ምፀት፥ ሽሙጥና ወዲያውነት አለው:: ሰበብም የግድ ይፈልጋል:: "ያለበት ይበንበት" እንደሚባለው ይኮረኩማል፤ ይነካል፤ ይገፋፋልም:: የሚከተለውን እንደ ምሳሌ በተጨማሪ ልንመለከት እንችላለን::

"ወፍ የአምሳ እግርን ዓይኖች ወስዳ ቀረች"

ወፍና አምሳ-እግር በጣም ይዋደዱ ነበር:: ከዕለታት አንድ ቀን ወፍ ወደ አግዋጋ (የኚያ የንጉሥ-ግብር) ልትሄድ ትፈልጋለች:: ወደ አግዋጋ ለመሄድ ልቧ ሲያስብ የወዳጇን የአምሳ-እግርን ዓይን "አሁን ምነው የኔ በሆነ" በማለት በጣም ትቀናለች:: ኋላ "አምሳ እግር ÷ እባክሽን እነዚህን እንደ ከዋክብት የሚፈልቁ ዓይኖችሽን ለሶስት ቀን አውሺኝ:: መቸም አንቺን ፈጣሪ አድሎሻል:: በዚህ ዓለም ያንቺን ዓይኖች የያዘ ማንም-ማንም የለም! ግን ምን ያደርጋል? እንዴት እንደሚፈልቁ፥ እንዴት እንደሚያምሩ ለአንች አይታዩሽም::" ትላታለች:: አምሳ-እግርም ደነቃትና "ዓይንን አውጥቶ ማዋስ እኮ ከባድ ነገር ነው:: እኔ ጨለማ ውስጥ መውደቄ ይጠፋሻል እንዴ! በበኩሌ የአንች ዓይኖችም ጥሩ ናቸው:: የእኔ ዓይኖች ምን ለውጥ ያመጡልሻል?" በማለት ትመልሳለች::

ወፍም "የእሱ ዓይኖች እንዳንቺ ዓይኖች በፍጹም አያምሩም:: ምን አለበት አሁን ለሶስት ቀን ብቻ ብታውሽኝና ባጌጥባቸው? አየሽ! የኔ አይኖች ለአግዋጋ ዳንስ አይሆኑም:: ክድን ግልጥ÷ ክድን ግልጥ÷ ስልምልምልም... እያሉ ከቡሉ (ከከበሮው) ድምጽ÷ ከክራሩና ከቶሙ ቃና ጋር አይሄዱልኝም:: የአንች ዓይኖች ግን ለዳንስ የተሰሩ ናቸው:: እና እባክሽን፤ ልክ አግዋጋው እንዳበቃ በርሬ መጥቼ እሰጥሻለሁ አውሽኝ" አለቻት:: አምሳ-እግርም "እሺ! ግን አደራሽን÷አግዋጋው እንዳበቃ እንድትመልሽልኝ:: በቀር ለዘላለም በጨለማ ተውጬ መቅረቴ ነው::" ብላ አስጠንቅቃ ዓይኖቿን ሰጠቻት:: ወፍ ግን በዚያው ክዳት ቀረች:: አምሳ እግርም ምንም ባለአምሳ እግር ብትሆን ዛሬ አሿራ ሳሿራ እንደ ተንከባለለች፤ እነደዳኸች ቀረች:: "አሁንም ወፍ የአምሳ-እግርን ዓይኖች ወስዳ ቀረች ነውና..." በሚል ተናጋሪው ወደተነሳበት ፍሬ ነገር ይመለሳል::

አንጋዶው በእምነትና በክህደት መካከል በየእለቱ በሚፈጠር ችግር ላይ የሚያተኩር ሆኖ በመልካም ግንኙነት፥ በፍቅርና በወዳጅነት መካከል በደል የሚፈፅሙትን ሰዎች ሁሉ ክፉኛ ይቆነጥጣል:: በድርጊቱ ህሊናው ሊቆስል የሚችልና በትረታው የሚስቅ ታዳሚም በአንድ ቅጽበት ይፈጥራል:: እንደገናም የድርጊቱን ድግግም ማቀቡን ይቀጥላል:: በሌላ በኩልም አኙዋዎች በመካከላቸው የሚፈጠርን ቅሬታ የሚያስታምሙበት የግንኙነትና የቋንቋ ስልት ምን እንደሚመስል የሚያመለክት ይሆናል::

"ተረቶች የአንድ ህዝብ ስነጽሁፋዊ ቅርስ መከሰቻ ብቻ አይደሉም:: በትክክለኛው አገላለጽ የህዝቡን ማንነት÷ የኑሮውን ስዕል÷ በጥልቀት ያሳያሉ:: ባህሉን ለማወቅ ያስችላሉ:: የተረሱ÷ የቆዩ ልማዶችንም ሆነ ያለፉ ድርጊቶችን÷ ባህላዊ እሴቶችን÷ ደንቦችንና ግቦችን

ጭምር ያሳያሉ " (Bascom 1965: 284-285)። የአኙዋ ትረካዎችም በአገልግሎታቸው ከዚህ የተለዩ አይደሉም። የህብረተሰቡን የቆየ ልማድና የታሪክ አሻራዎች እንዲሁም የሚከተላቸውን ደንቦችና ስነምግባሮች በሰፊው ይገልፃሉ። ድንቅ ይሏቸው የነበሩ፥ ዛሬም የሚሏቸውን እሴቶችና ተምሳሌዎች (archetypes) ያመለክታሉ። የሚቀጥለው አንጋዶ ያተኮረበት ይዘትና የሚያሳየው ድርጊት ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ይሆናል።

ርዕሱ "አዶክ ከፎከረ በኋላ ከሞት ሸሸ ተብሏል" የሚለውን ስሜት የሚሰጥ ሲሆን ትረካው የሚከተለውን ይመስላል።

> ጥንት የአኙዋ ኘያዎችና ኳሮዎች ሲሞቱ አብሯቸው ወደ ውሃ የሚመለስ አጎት "ናም" (Nam) በስርዓተ ሹመታቸው ቀን መርጠው ሳም ይሸልሙ ነበር። አንድ ቀን አዶክ የሚባል ሰው ከኘያው ጋር አብሮ ሊቀበር ተመረጠ። ሽልማቱንም በህዝብ ፊት በኘያው ስርዓተ ሹመት ቀን ተቀበለ። ሽልማቱን ተቀብሎ በደስታ ሲኖር፥ ሲኖር ኘያው(ንጉሡ) ሞተ። ኘያው እንደሞተ አዶክ ቢፈለግ፥ ቢፈለግ ጠፋ። እሱ ካልተገኘ ኘያው ሊቀበር አይችልም። ስለዚህ ያገሩ ሰው ሁሉ አዶክን በየስፍራው ተሰማርቶ ሲፈልግ ተደብቆ ተገኘ። ከዚያም "ከኘያው ጋር አብረህ ልትቀበር ተመርጠህ፥ በስርዓት ተሸልመህ ስታበቃ አሁን እርሱ ሲሞት እንዴት ያለ ነውርና አሳፋሪ ስራ ትሰራለህ? በልና!" ብለው ይዘውት ሲሄዱ አዶክ ያዩቶቹንና ያባቶቹን የቡል ስም (የፈረስ ስም) እየጠራ ፎከረ፥ ፎከረ፥ ፎከረ… ከዚያም ትንሽ ከበሮ እና "ጋሬ" (ከሳባ የሚሰራ የወግ ልብስ) "ስጡኝ" አለ። ጋሬውንም ተቀበለና ለብሶ ከበሮውን እየመታ፥ እጁን፥ እግሩን፥ ተቆርጦ ከመረጠውና ከሸለመው ከኘያው ጋር አብሮ ለመቀበር ዝግጁ መሆኑን በቃከራ እየተንጎራደደ ገለፀ። ከወዲያ ወዲህ እየዘለለ እየተወራጨ ሲፎክር "ፈሪና ነውረኛ ነው" ብሎ በፊት ንቆትና ስቆበት የነበረው ሰው ሁሉ ፈዝዞ ይመለከተው ጀመር። ፈዝዞ ሁኔታውን ሲያይ አዶክ ጋሬውን አውልቆ ጥሎ ከበሮውን ወርውሮ ሩጦ ከሞት አመለጠ። በዚህ ምክንያት "አዶክ ፎክሮ ሞትን ሸሽቶ አመለጠ" ይባላል።[10]

አንጋዶውን ከርዕሱ ጀምረን ይዘቱንና ማህበራዊ ፋይዳውን ከባህላዊ ስራቱ ጋር ለመመልከት ስንሞክር፥ ርዕሱ ምሳሌያዊ አነጋገር ሆኖ የስላቅና የመገረም ስሜትን ይዞ እናገኛለን። ይህም "ከሞት ማምለጥ እንዴት መሳለቂያ ሊያደርግ ይችላል?" የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። ነገር ግን እንዲህ ላለው ጥያቄ መልሱ እንደ ባህሉ የሚወሰን ነው (Beals, et. al. 1965:269)። በመሆኑም አዶክ ከፎከረ በኋላ ሞትን ሸሽቶ የማምለጡ ድርጊት በባህሉ ባለቤቶች ዘንድ የነቀፌታና የስላቅ ስሜትን ሊፈጥር የቻለው ራሱ ባህላዊ ሥርዓቱ ይሆናል ማለት ነው። በታሪኩ ላይ እንደተገለፀው አዶክ በኘያው ሥርዓተ ሹመት ላይ በህዝብ ፊት ተመርጦ በልማዱ መሠረት ላም ተሸልሟል። ሽልማቱ በውጫዊ ገጽታው፥ በቁሳዊ ጥቅሙ፥ የሚወሰን ሳይሆን ለአኙዋዎች ተምሳሌያዊ (symbolic) ትርጓሜ አለው። ይኸውም ተሸላሚው ሸላሚው ሲሞት አብሮ በህይወት ሊቀበር በወገኖቹ ፊት በቃል ኪዳን መታሰሩንና ስጦውን በውዴታ ግዴታ መቀበሉን የሚያረጋግጥ ነው። ቁርጠኝነቱም ሆነ ድርጊቱ ባህላዊ መሰረቶች

---

10 ተራኪ፡ ቄስ አኳይ ኦሹዶ፥ ጋምቤላ፥ ነሃሴ፥ 1990።

አሉት። ይኸውም ኜያ ወይም ኳሮ ብቻውን አይቀበርም፤ ከአሳቶቹ አንዱ ወይም ሁለቱ አብረውት በህይወት ከምግብ ጋር መቀበር በአኙዋዎች አገላለጽ "ወደ ውሃ መመለስ" አለበት። ይሀ ካልሆነ በአኙዋዎች ዕምነት የአባቶች መናፍስት ቁጣ ይሰነዘራል-እርግማን፡ "አችዬኒ" (acieni) በአገሩ ላይ ይወርዳል። ይህ ከሆነ በሽታ ይስፋፋል፤ ሰላም ይጠፋል፤ ረሀብና ድርቅ ይታዘዛል፣ እልቂት ይመጣል። ስለዚህ የመሪዎቹ አስከሬን በህይወት ካለ በቁሙ በህዝብ ፊት ከመረጠው "ናም" (አሳቱ) ጋር መቀበር አለበት። በእርግጥ ድርጊቱ ዘግናኝ ነው። ዳሩ ግን ይህን የመሰለውን ድርጊት እምነት እንደሚመራው፥ እንደሚገዛው ሁሉ በውስጡ ለሚኖር ዘግናኝነቱን ይከፍል ይሆናል። ደግሞም አኙዋዎች ለህይወት ያላቸው አመለካከት ሁለት ጽንፎች አሉት። ተራው ህዝብ (ዋቶንግ) ለዘለዓለም ይሞታል። እና ከሥጋው ጋር ህይወቱ (ነፍሱ) አብራ ትከስማለች። ሁለተኛው ጽንፍ ደግሞ የነጋሲያንን፡ የባላባቶችንና የመኳንንትን ዘር ህይወት የሚመለከት ነው። የእነርሱ ህይወት (ነፍስ) ከሞት በኋላ ትኖራለች። ዘለዓለማዊ ነች። ወደ ውሃ ተመልሳ ከአባቶቿ መናፍስት ጋር ትቀላቀላለች - በአኙዋዎች አመለካከት። በቀርም እንዳሻት ቅርጿን ወደ እንስሳ ቀይራ፡ በቀሪ፥ ወገኖቿ ዘንድ እየተመለሰች ለምንጊዜም ትኖራለች።

በአኙዋዎች ልማድ "ዋቶንግ" ሲሞት ይለቀሳል፤ እንደ አዶክ ያለ የነጋሲ ዘር ግን ነፍሱ ከስጋው ስትለያይ ይደገሳል፤ ይጨፈራል፤ ይዘፈናል። "ሞተ" አይባልም፥ "ወደ ውሃ ተመለሰ" እንጂ፤ በመሆኑም አይለቀስም። አይታዘንም። በባህሉ የተከለከለ ነውር ነውና (ፈሊፕ አጥየው፥ የካቲት 21፡1991 ዓ.ም. ፥ ቃለ መጠይቅ)። እንግዲህ የአዶክን አፈንጋጭነት (ከፎከረ ወዲያ ሞትን የመሸሸቱን ድርጊት) ልንረዳው የሚገባ ከዚህ አንፃር ይሆናል። እንደ ተጠቀሰው እጁ ተቆርጦ፡ ጉልበቱ ታጥፎ በህይወት ቀብር ውስጥ መግባት አስፈሪና አሰቃቂ ድርጊት ነው። ግን በአኙዋዎች አስተያየት አዶክ የነጋሲ ዘር ነው። ስጋው ቢፈርስም ነፍሱ (ህይወቱ) ዘለዓለማዊ ነች። ስለዚህ ወደ ውሃ ተመልሶ ከደመቀው መንደር ከአባቶቹ መናፍስት ጋር፥ በቀርም ወደ ቀጭኔነት፥ ወደ ነብርነት ወይም ወደ አንበሳነት... ተቀይሮ በጎሳው ዘንድ ተመልሶ ይኖራል። ከዚህ በተጨማሪ የኜያው "ናም" ነው። ዕጣውን በወገኖቹ ፊት ወዶ ተቀብሏል። የሽልማቱ አብነት ቃል ኪዳን በመሆኑ ህብረተሰቡ፥ ባህሉ፡ ልማዱና ስርዓቱ ኜያው ሲሞት አዶክ አብሮ መቀበር እንደሚገባው ይጠብቀዋል። ስለዚህ ኜያው እንደ "ሞተ" ፈጥኖ መድረስ የአዶክ ግዴታ ሆኖ ሳለ በተቃራኒው ጠፍቶ መደበቁን እንረዳለን። የኜያው አስከሬን ያለ አዶክ አጃቢነት ወደ ውሃ ሊመለስ አይችልምና ከገባበት ተፈልጎ መገኘቱንም እንገነዘባለን። አዶክ ተፈልጎ ከተገኘ በኋላ ወደ ስርዓተ-ቀብሩ ሲመጣ የአባቶቹን የ"ቡል" ስም (የጀግንነት፥ የፈረስ ስም) እየጠራ እየፎከረ ነበር።

> "ኜያው ወይም ኳሮው የመረጠውና የሸለመው ናም እጁና እግሩ ተሰብሮ፥ ታጥፎ ከአስከሬኑ ጋር በህይወት ወደ ቀብር ለመግባት መቁረጡን፡ ዝግጁ መሆኑን፥ በቀብር ስርዓት ላይ በወገኖቹ ፊት የሚያረጋግጠው በአባቶች ቡል ስም ፉከራ በማድረግ ነው። ድፍረቱን፥ መቁረጡን፥

ጀግንነቱን በማሳየት ከወገኖቹ የሚሰናበተው በፉከራ ነው"።[11]

እንደ ተጠቀሰው ፉከራ የሥርዓተ-ቀብር (ኮኒ) አንድ ገጽታ ሲሆን፥ አስፈላጊነቱም ስንብቱን ማከናወን ነው። አዶከም ለስርዓቱ አስፈላጊ የሆነውን "ጋሬ" ለብሶ፥ ከበሮ እየመታ፥ ወዲያ ወዲህ እየተመላለሰና እየተወራጨ፥ የአባቶቹን የ"ቡል-ስም" እየዘረዘረ፥ ከኙያው አስከሬን ጋር አብሮ በህይወት ወደ ውሃ ለመመለስ ቁርጠኛ መሆኑን እየተናገረ፥ የህብረተሰቡን ፍላጎት ለመፈፀም መቅረቡን እየገለፀ፥ ስንብቱን ስሜት በሚነካ አኳኋን እያከናወነ፥ ስውነቱን ካሟሟቀ በኋላ ባህሉን ጥሶ በርሮ ሲጠፋና ሲያመልጥ እነሆ በአኙዋዎች ዘንድ መገረምን፥ የመደነቅንና የመሰለቅን አሻራ ጥሎ በማለፍ "አዶክ ከፎከረ በኋላ ከሞት ሸሸ" የሚል አንጋዶ (ምሳሌያዊ አነጋገር) ከነትረካው ይዞ እናገኛለን። አንጋዶው መልሶ የሚያሳየን በዘመን እርቀት አኙዋዎች ተፈበመ የሚሉትን ድርጊት ሲሆን፥ ያለፈው የዛሬውን ተመሳሳይ ሁኔታ እየገለፀ ይታያል። የሚታየውም ከባህላዊ ትርጓሜውና ከስነጽሁፋዊ ዋጋው ብቻ ሳይሆን የቆየውን የአኙዋ የኙያ ስርዓት ባህርይና አሰራር በመመዝገብ በታሪካዊ መረጃነቱ ጭምር ይሆናል ማለት ነው።

የአኙዋ ህብረተሰብ እንደ ሌሎቹ የኢትዮጵያ ናይሎ ስሀራ ህብረተሰቦች፥ የስነቃል ህብረተሰብ (Oral Socicty) ነው። ይሁን እንጂ ታሪኩ፥ ባህሉና ማህበራዊ ህይወቱ በጽሁፍ ገና አልሰፈረም። የረዥም ዘመናት ውጣ ውረዱ፥ ድሉም ሆነ ሽንፈቱ፥ ግንኙነቱ፥ እምነቱ፥ አመለካከቱ፥ ልምዱና እውቀቱ... ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፈ የሚገኘው በስነቃል አማካይነት ነው።

በዚህ ጥናት ውስጥ እንደ ምሳሌ የቀረቡት ጥቂት ትረካዎች የአኙዋ ወግና ልማድ ታሪክና ማህበራዊ ግንኙነት ምን እንደሚመስል መጠነኛ ግንዛቤ ይሰጣሉ። አኙዋዎች ስለዓለም አፈጣጠር፥ ስለሰው ልጅ አመጣጥ፥ የሰው ልጅ ከፈጣሪውና ከአካባቢው ጋር ስላለው ግንኙነት እንዴት እንደሚገነዘቡ ይጠቀማሉ። ታሪክን ያስታውሳሉ። የህልውናና የህብረተሰብ ዋስትና የሆኑ ህጎች፥ ደንቦችና የፍትህ መሰረቶች እንዴት እንደተፈጠሩና አኙዋዎች በምን መልክ እየተገለገሉባቸው እንደሚገኙ ትረካዎቹ በሰፊው ያመለክታሉ። የህብረተሰቡ የእስተሳሰብና የፈጠራ ስልቶች፥ የዕለት ተዕለት ግንኙነቶችና ድርጊቶች በትረካዎቹ መዋቅሮች፥ ድርጊቶችና መልዕክቶች ውስጥም ይገኛሉ። የቆየው የኙያ ሥርዓት፥ ባህላዊና ማህበራዊ ተቋሞች፥ የህብረተሰቡ አከፋፈልና አኗኗር በአጠቃላይም መንፈሳዊውና ቁሳዊው ባህሎች በትረካዎቹ ውስጥ ይንፀባረቃሉ። ህብረተሰቡ የሚወደውን ከሚጠላው፥ የሚቀርበውን ከሚሸሸው፥ የሚደግፈውን ከሚነቅፈው ለመለየትም ይረዳሉ። እንደሚታወቀው ዕድገት ገዐበረከት አይደለም። ስለዚህ ዕድገት ባህልን፥ አገር በቀል የረጅም ዘመናት ልምድንና እውቀትን መሰረት አድርጎ መነሳትና መስረጽ ይኖርበታል። ለዚህም የተለያዩ የአገሪቱን ክፍሎች ፎክሎር፥ በአጠቃላይ ባህል

11

ከቱስ አኳይ አሹዱ ጋር የተካሄደ ቃለ መጠይቅ፥ ነሀሴ 29 ቀን፥ 1990

ለትምህርት መስፋፋትና ለዕድገት በሚበጅ ሁኔታ ጥናት ማካሄድ እንደሚያስፈልግ ጨምረው ያስገነዝባሉ::

References

የኢትዮጵያ መጽሀፍ ቅዱስ ማህበር፥ 1980:: **መጽሀፍ ቅዱስ:: አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት::**

Bahiru Zewde, 1976. **Relation Between the Sudan on the Western Ethiopian Frontier: 1895-1935.** Thesis Submitted for the Degree of Doctor of Philosophy, University of London.

Bascom, William, 1965. *" Four Functions of Folkolore" , in* **The Study of Folklore .** Dundes (ed.) California: Berkley, Prince Hall Inc., 277-298.

Beals, Ralph L. and Hoider, Harry,1965. **An Introduction to Anthropology.** New York: The Macmillan Company.

Caam, Adhom, 1996. **The Anyuae Poletical Organizations** (unpublished). Gambella: Bureau of Education and Culture: Group Division for Study.

Courlander, Harold, 1977. **A Treasury of African Folklore:** (The Oral Literature, Traditions, Myths, Legends, Epics, Tales, Recollections, Wisdom, Sayings and Humour of Africa). New York: Crown Publishing, Inc.

Evans -Pritchard, E.E., 1941. **The Political System of the Anuak of the Anglo-Egyptian Sudan,** Monographs on Social Anthropology. London.

Kurimoto, Essei, 1996. *People of the River: Subsistence Economy of the Anywaa (Anuak) of Western Ethiopia,* **Senri Ethnological Studies** (No. 43), Essays in North East African Studies. Osaka: National Museum of Ethnology, 29-57.

Lusted, Marrie, 1976. *Anywa*, (Bender, ed.) in **The Non-Semetic Languages of Ethiopia** Michigan: East Lansing, Michigan University Press, 495-512.

Malinowski, Bronislaw, 1926. **Myth in Primitive Psychology.** Connecticut: Westport, Negro University Press.

P'Bitek, Okot, 1974. **Horn of My Love.** London: Heinmann Education Books Ltd.,

Peacock, James L., 1969. *Society as Narrative,* R.F. Spencer, (ed.), **in Forms of Symbolic Action:** Proceedings of the 1969 Anual Spring Meeting of the American Ethnographic Society, University of Washington Press, 167-177.

Petner, Conradin, 1991. **Short Grammar and Dictionary Proceeded by and Essay on the Role Played by Language in Anyuaa Society,** (Vol. I). Connecticut, Newhaven: Human Relations Area Files, Inc.

Reh, Mechthild, 1996. **Anyuaa Language: Descriptions and Internal Constructions.** Koln: Koppe.

ማረሚያ ERRATA

ባለፈው ቁጥር 1 እትም ውስጥ ከፊደል ግድፈቶች ሌላ ለነበሩ ስህተቶች ይቅርታ እየጠየቅን ስህተቶቹ እንደሚከተለው ታርመው እንዲነበቡ እናሳስባለን።

We apologize for errors made in the previous issue (No.1) and we request readers to consider the following corrections.

1) <u>በሽፋን ገጽ</u>፣ ሐምሌ <u>፲፱፺፩</u> የተባለው <u>፲፱፻፺፩</u> ተብሎ እንዲነበብ፤
በአርማው ላይ <u>ኢቋጦተ</u> ተብሎ የተመለከተው <u>ኢቋጥማ</u> ተብሎ ይነበብ፤

<u>Cover Page</u>:- June 1999 should be read as July 1999;

2) <u>በገጽ 26 ግርጌ የሚከተለው ክፍል ይቀጥላል፣</u>

". . .ቀን 1964 በትዕዛዝ ቁጥር 79/ 1964 በወጣው ነጋሪት ጋዜጣ ይፋ ሆነ (ነጋሪት ጋዜጣ፣ 1964) ።

2. ብሄራዊ የአማርኛ መርሐ ልሳን /አካዴሚ/

" . . .መርሐ ልሳን እየተባለ የሚጠራ አንድ ብሄራዊ የአማርኛ መርሐ ልሳን በሕግ እንደ ሰው ተቆጥሮ ራሱን የቻለ የመንግስት መስሪያ ቤት በመሆን . . . ተቋቁሟል " (ነጋሪት ጋዜጣ ፣ 1964፣ ገፅ 1) በማለት በአዋጅ ህጋዊ ህልውና የተሰጠው መርሐ ልሳን አላማ በጊዜው የኦፊሴል ቋንቋነት ደረጃ የነበረውን የአማርኛ ቋንቋ . . ."

3) በገጽ 25፤ "ምንም እንኳ በዚህ መልክ ...." ብሎ በመጀመር እስከ ገጽ 26 ተሻግሮ" ....የሚመሰክሩ ናቸው። " ተብሎ የሰፈረው አንቀጽ በድጋሚ የተጻፈ ስለሆነ እንዲታለፍ፤

እናመሰግናለን

ባለፉት ዓመታት በማዕከሉ ተዘጋጅተው የታተሙ ሥራዎች

የመፅሐፉ ርእስ	ዋጋ
1. የግዕዝ ቅኔያት የስነጥበብ ቅርስ፣1980	15.00 (በገበያ ላይ የሌለ)
2. የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ 1982	7.00 (በገበያ ላይ የሌለ)
3. A Concise Dictionary English - Amharic, 1990	—— (በገበያ ላይ የሌለ)
4. የግዕዝ ቅኔያት የስነጥበብ ቅርስ (ሁለተኛ ክፍል)፣ 1984	15.00 (በገበያ ላይ የሚገኝ)
5. ምስላታት የትግርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ 1985	13.00 (በገበያ ላይ የሚገኝ)
6. ምሳይተቶ ሴምሱዋ (የወላይትኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች)፣1987	15.00 (በገበያ ላይ የሚገኝ)
7. የሳይንስና ቴክኖሎጂ መዝገበ ቃላት (እንግሊዝኛ-አማርኛ)፣ 1989	13.00 (በገበያ ላይ የሚገኝ)
8. መዝገበ ቃላት ትግርኛ ብትግርኛ፣ 1989	35.00 (በገበያ ላይ የሚገኝ)
9. Glamee Jechoota Afaan Oromoo፣ 1996 (የኦሮምኛ መሰስተኛ አጠቃላይ መዝገበ ቃላት፣ 1988)፣	25.00 (በገበያ ላይ የሚገኝ)
10. Sidaamu Afii Maammashasha ፣1990 (የሲዳምኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች)	13.00 (በገበያ ላይ የሚገኝ)
11. Wolayttatto Qaalatu Amaaratto Birshshettaa, 1991 (የወላይትኛ አማርኛ መዝገበ ቃላት)፣	15. 00 (በገበያ ላይ የሚገኝ)
12. የቤተ ጉራጌ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ 1991	20.00 (በገበያ ላይ የሚገኝ)